26 ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን እኔን ፥ ካህኑን ሳዶ
ቅን ፥ በናያንና ሰሎሞንን ወደ ግብዣው አልጠ
ራንም ፤ 27 ንጉሥ ሆይ! ከአንተ በኋላ የሚነግ
ሠውን ለባለሟሎችህ እንኳ ሳታስታውቅ ይህ
ሁሉ እንዲሆን ፈቅደሃልን?”

28 ንጉሥ ዳዊትም “ተመልሳ እንድትመጣ
ቤርሳቤህን ጥሩ” ብሎ አዘዘ ፤ እርስዋም መጥታ
በፊቱ ቆመች ፤ 29 በዚህም ጊዜ እንዲህ አላት ፥
“ከደረሰብኝ መከራ ሁሉ በታደገኝ በሕያው
እግዚአብሔር ስም ቃል እገባልሻለሁ ፤ 30 ይኸ
ውም ልጅሽ ሰሎሞን በእኔ እግር ተተክቶ እን
ደሚነግሥ የእስራኤል አምላክ በሆነው በእግዚ
አብሔር ስም ከዚህ በፊት የገባሁልሽን ቃል
በዛሬው ዕለት የምፈጽም መሆኔን አረጋግጥልሻ
ለሁ ።”

31 ቤርሳቤህም ወደ መሬት ለጥ ብላ እጅ
በመንሣት “ጌታዬ ንጉሥ ዳዊት ለዘላለም በሕ
ይወት ይኑር!” አለች ።

32 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ዳዊት ሳዶቅን ፥ ናታ
ንና በናያን አስጠራ ፤ እነርሱም ገብተው ወደ
እርሱ በቀረቡ ጊዜ ፥ 33 እንዲህ አላቸው ፥
“በቤተ መንግሥቴ ከሚገኙት ባለሟሎቼ ጋር
አብራችሁ ሂዱ ፤ ልጄን ሰሎሞንንም እኔ በምቀ
መጥባት በቅሎ አስቀምጡትና አጅባችሁት
ወደ ግዮን ምንጭ ውረዱ ፤ 34 በዚያም ካህኑ
ሳዶቅና ነቢዩ ናታን ቀብተው በእስራኤል ላይ
ያንግሡት ፤ ከዚህ በኋላ ቀንደ መለከት በመን
ፋት ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ‘ንጉሥ ሰሎ
ሞን ለዘላለም ይኑር!’ በሉ ። 35 በዙፋኔ ላይ
ስመቀመጥ ወደዚህ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ
አጅባችሁት ኑ ፤ የእስራኤልና የይሁዳ ንጉሥ
ገዥ እንዲሆን የመረጥሁት ስለሆነ እርሱ ከእኔ
በኋላ ይነግሣል ።”

36 በናያም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ሁሉም
ነገር በትእዛዝህ መሠረት ይፈጸማል ፤ ይህን
ንም አምላክህ እግዚአብሔር ይፈጽምልህ ፤
37 ንጉሥ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንተ ጋር
እንደሆነ ሁሉ ከሰሎሞንም ጋር ይሁን ፤ መን
ግሥቱንም በዘመንህ ከነበረው የበለጠ ታላቅ
ያድርገው ።”

38 ስለዚህ ሳዶቅ ፥ ናታን ፥ በናያና የንጉሡ
ክብር ዘበኞች ሰሎሞንን ዳዊት በሚቀመጥባት
በቅሎ ላይ በማስቀመጥ ወደ ግዮን ምንጭ
ወረዱ ፤ 39 ካህኑ ሳዶቅም እግዚአብሔር ከሚ
መለክበት ድንኳን ይዞት የመጣውን የቅባት
ዘይት መያዣያ ቀንድ ወስዶ ሰሎሞንን
ቀባው ፤ በዚህን ጊዜ ቀንደ መለከት ነፉ ፤
ሕዝቡም ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው
“ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!” አሉ ፤
40 በሚመለሰበትም ጊዜ አጅበው ተከተሉት ፤
ከድምፃቸው ከፍተኛነት የተነሣ ምድር እስከ
ትናወጥ ድረስ እምቢልታ በመንፋት እየጮኹ
ደስታቸውን ገለጡ ።

41 አዶንያስና የጠራቸው ተጋባዦች ሁሉ
ግብዣውን በማገባደድ ላይ ሳሉ የሁካታ ድምፅ
ሰሙ ፤ ኢዮአብም የመለከት ድምፅ በሰማ ጊዜ
“ይህ በከተማው ውስጥ የሚሰማው የሁካታ
ድምፅ ሁሉ ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ ፤
42 እርሱ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ የካህኑ የአብያ
ታር ልጅ ዮናታን ድንገት ደረሰ ፤ አዶንያስም
“እስቲ ና ግባ! አንተ ጥሩ ሰው ስለሆንክ መል
ካም ዜና ይዘህ ሳትመጣ አትቀርም” አለው ።

43 ዮናታንም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ደኅና
ወሬስ ይገኝ አልመጣሁም ፤ ግርማዊው ንጉሥ
ዳዊት ሰሎሞንን አንግሦታል ፤ 44 እርሱንም
ያጀቡት ዘንድ ሳዶቅን ፥ ናታንን ፥ በናያንና
የቤተ መንግሥቱን ክብር ዘበኞች ልኮአል ፤ እነ
ርሱም ንጉሡ በሚቀመጥባት በቅሎ ላይ እንዲ
ቀመጥ አድርገው ፥ 45 ሳዶቅና ናታን በግዮን
ምንጭ አጠገብ ቀብተው አንግሠውታል ፤ ከዚ
ህም በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በደስታ ተሞልተው በእ
ልልታና በሆታ ድምፃቸው እያስተጋባ ወደ
ከተማ ተመልሰዋል ፤ አሁን የምትሰሙትም
ድምፅ ይኸው ነው ፤ 46 እነሆ ሰሎሞን ነግሦ
በንጉሣዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦአል ፤ 47 ከዚህም
በላይ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ባለሟሎች
ሁሉ ወደ ንጉሥ ዳዊት ቀርበው ‘አምላክህ እግ
ዚአብሔር ሰሎሞንን ከአንተ ይበልጥ ዝናው የገ
ነነ ፥ መንግሥቱንም ይበልጥ ታላቅ ያድር
ገው!’ ሲሉ አክብሮታቸውን ገልጠዋል ፤ ከዚህ
በኋላ ንጉሥ ዳዊት በአልጋው ላይ ሳለ ለእግዚ
አብሔር በመስገድ ፥ 48 ‘ዛሬ ከእኔ ዘሮች መካ
ከል አንዱ በእኔ እግር ተተክቶ እንዲነግሥ ያደ
ረገና ይህንን ለማየት ያበቃኝ የእስራኤል አም
ላክ የሆነ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን!’
ሲል ጸለየ ።”

49 አዶንያስ የጠራቸው ተጋባዦች ሁሉ
ይህን በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ ፤ ሁሉም ተነሡ ፤
እያንዳንዱም በየፊናው እየተሹለከለከ ሄደ ፤
50 አዶንያስም ሰሎሞንን እጅግ ስለፈራ እግዚአ
ብሔር ወደሚመለክበት ድንኳን ገብቶ የመሠዊ
ያውን ቀንዶች በመያዝ ተማጠነ ። 51 ሰዎቹም
ሰሎሞንን “አዶንያስ አንተን ከመፍራቱ የተነሣ
የመሠዊያውን ቀንዶች ይዞ ‘ከሁሉ በፊት
ንጉሥ ሰሎሞን የማይገድለኝ መሆኑን በማረጋ
ገጥ በመሐላ ቃል ይግባልኝ’ በማለት እየተማ
ጠነ ነው” ሲሉ ነገሩት ።

52 ንጉሥ ሰሎሞንም “እርሱ ታማኝ ሆኖ
ከተገኘ ሌላው ቀርቶ ከራስ ጠጕሩ አንዲት
እንኳ አትነካበትም ፤ ታማኝ ሆኖ ካልተገኘ ግን
ይሞታል” ሲል መለሰ ፤ 53 ከዚህ በኋላ ንጉሥ
ሰሎሞን አዶንያስን ከመሠዊያው አውርደው
ያመጡት ዘንድ መልእክተኞች ላከ ፤ አዶንያ
ስም ወደ ንጉሡ ፊት በመቅረብ ወደ መሬት
ለጥ ብሎ እጅ ነሣ ፤ ንጉሡም “ወደ ቤትህ
መሄድ ትችላለህ” አለው ።

## ምዕራፍ 3

### ንጉሥ ሰሎሞን ጥበብ ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነ
(2 ዜ.መ. 1፥3-12)

1 ሰሎሞን የግብጽን ንጉሥ ሴት ልጅ በማግ
ባት ከንጉሡ ጋር ወዳጅነት መሠረተ፤ እርስዋ
ንም አምጥቶ ቤተ መንግሥቱን፥ ቤተ መቅደሱ
ንና የኢየሩሳሌምን ከተማ ዙሪያ ቅጽር ሠርቶ
እስኪጨርስ በዳዊት ከተማ አኖራት። 2 በዚያን
ጊዜ እግዚአብሔር የሚመለክበት ቤተ መቅደስ
ገና አልተሠራም ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በየኮረ
ብታው መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። 3 ሰሎሞን
እግዚአብሔርን ይወድ ነበር፤ የአባቱንም የዳዊ
ትን መመሪያ ይጠብቅ ነበር፤ ይሁን እንጂ እን
ስሶችን እያረደ በተለያዩ ኮረብታዎች ላይ መሥ
ዋዕት ያቀርብ፥ ዕጣንም ያጥን ነበር።
4 ከሁሉ የሚበልጠው ታላቅ መሠዊያ የሚገ
ኘው በገባዖን ስለነበር አንድ ቀን ሰሎሞን
መሥዋዕት ለማቅረብ ወደዚያ ሄደ፤ ከዚህም
በፊት በዚያ መሠዊያ ላይ በብዙ መቶ የሚቈ
ጠሩ እንስሳት የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ
አቅርቦአል፤ 5 በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር
ለሰሎሞን በሕልም ተገለጠለትና "ምን እንድሰ
ጥህ ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀው።
6 ሰሎሞንም እንዲህ ሲል መለሰ፥ "አገልጋ
ይህ የነበረው አባቴ ዳዊት ደግ፥ ታማኝና ቅን
ሰው በመሆኑ ጽኑ ፍቅርህን ስታሳየው ኖረሃል፤
ዛሬም በእርሱ እግር ተተክቶ የሚገዛ ልጅ በመ
ስጠት ታላቅና ጽኑ የሆነውን የማያቋርጥ ፍቅር
ህን ገልጠህለታል፥ 7 እግዚአብሔር አምላክ
ሆይ! እነሆ እኔ በዕድሜ አነስተኛ ነኝ፤ የአመ
ራር ልምድም የለኝም፤ አንተ ግን በአባቴ
እግር ተተክቼ እንድነግሥ ፈቃድህ ሆኖአል፤
8 እነሆ እኔ የአንተ እንዲሆን በመረጥከውና ከብ
ዛቱ የተነሣ ሊቈጠር በማይችል ሕዝብ መካከል
እገኛለሁ፤ 9 ስለዚህ ክፉውንና በጎውን በመለ
የት ሕዝብህን በትክክለኛ ፍትሕ ለመምራት
የሚያስችለኝን ጥበብ ስጠኝ፤ ይህ ካልሆነ ግን
ታላቅ ሕዝብህን እንዴት ልመራ እችላለሁ?"
10 ሰሎሞን ይህን በመጠየቁ እግዚአብሔርን
ደስ አሰኘው፤ 11 እግዚአብሔርም እንዲህ
አለው፥ "ለራስህ ረዥም ዕድሜ ወይም ሀብት
ለማግኘት ወይም ጠላቶችህ እንዲጠፉልህ መመ
ኘት ሳይሆን በትክክለኛ ፍትሕ ማስተዳደር
የምትችልበትን ጥበብ ስለጠየቅህ፥ 12 እነሆ የጠ
የቅኸውን አደርጋለሁ፤ እንዲያውም ማንም
ሰው ከዚህ በፊት ካገኘውና ወደ ፊትም ሊያገ
ኘው ከሚችለው የሚበልጥ ጥበብንና አስተዋይ
ነትን እሰጥሃለሁ፤ 13 ከዚህም በላይ አንተ ያል
ጠየቅኸውንም ሁሉ ጨምሬ እሰጥሃለሁ፤ ይኸ
ውም በዘመንህ ማንኛውም ሌላ ንጉሥ ያላገኘ
ውን ብልጽግናና ክብር እበዛልሃለሁ። 14 አባ
ትህ ዳዊት እንዳደረገው ለእኔ ብትታዘዝ፥ ሕጌ
ንና ሥርዓቱንም ብትፈጽም ረዥም ዕድሜ እሰ
ጥሃለሁ።"
15 ሰሎሞን ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ እግዚአብ
ሔር በሕልም ተገልጦ ያነጋገረው መሆኑን ተገ
ነዘበ፤ ከዚህ በኋላ ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም
ተመልሶ ሄደ፤ በእግዚአብሔርም የቃል ኪዳን
ታቦት ፊት ቆሞ የሚቃጠል መሥዋዕትና ለደኅ
ንነት የሚሆነውን የኅብረት መሥዋዕት ለእግዚ
አብሔር አቀረበ፤ ከዚህም በኋላ ባለሟሎቹ
ለሆኑ ባለሥልጣኖች ሁሉ ግብዣ አደረገ።

### ጥበብ የሞላበት የሰሎሞን ፍትሕ

16 አንድ ቀን ሁለት ጋለሞታዎች መጥተው
በሰሎሞን ፊት ቀረቡ፤ 17 ከእነርሱም አንደኛ
ይቱ እንዲህ አለች፥ "ንጉሥ ሆይ! ይህች
ሴትና እኔ በአንድ ቤት አብረን ስንኖር በዚያው
በምንኖርበት ቤት ወንድ ልጅ ወለድሁ፤ 18 እኔ
በወለድሁ በሦስተኛው ቀን እርስዋም ወንድ
ልጅ ወለደች፤ በዚያ ቤት ውስጥ ከሁለታችን
በቀር ሌላ ማንም አልነበረም። 19 ከዕለታት
አንድ ቀን ሌሊት በላዩ ላይ ተኝታበት ስለታ
ፈነ ልጁ ሞተ፤ 20 እኔ ተኝቼ ሳለሁ ሌሊት
ተነሥታ ታቅፌው የተኛሁትን ልጄን ወስዳ
በእርስዋ አልጋ ላይ ካስተኛች በኋላ የሞተውን
ልጅዋን አምጥታ በእኔ አልጋ ላይ በጐኔ አስተ
ኛችው። 21 በማግሥቱ ማለዳ ተነሥቼ ልጄን
ለማጥባት ስዘጋጅ የሞተ ሆኖ አገኘሁት፤
ትኲር ብዬ ስመለከተው እኔ የወለድሁት ልጅ
አለመሆኑን ተገነዘብሁ።"
22 ሁለተኛይቱ ሴት ግን፥ "አይደለም! በሕ
ይወት ያለው ልጅ የእኔ ነው፤ የሞተው ግን
የአንቺ ነው!" አለች።
የመጀመሪያይቱ ሴት "አይደለም! የሞተው
የአንቺ ልጅ ነው፤ በሕይወት ያለው ግን የእኔ
ልጅ ነው" አለች።
በዚህም ዐይነት ሁኔታ በንጉሡ ፊት ተከራ
ከሩ።
23 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን "አንደኛዋ
'በሕይወት ያለው ልጅ የእኔ ነው፤ የሞተው
ግን የአንቺ ነው!' ትላለች፤ ሌላይቱ ደግሞ
'አይደለም! የአንቺ ልጅ ሞቶአል፤ የእኔ ልጅ
በሕይወት ያለው ነው!' ትላታለች።" 24 ንጉ
ሡም ሰይፍ እንዲያመጡለት አዘዘ፤ ሰይፍ ባመ
ጡለት ጊዜም፥ 25 "በሉ እንግዲህ በሕይወት
ያለውን ልጅ ለሁለት ቈርጡና ለእያንዳንዲ
ቱ ግማሽ አካሉን ስጡ" ሲል አዘዘ።
26 እውነተኛይቱ እናት ግን ለልጅዋ በመራ
ራት አዝና፥ "ንጉሥ ሆይ! እባክህ ልጁን አት
ግደለው! ለእርስዋ ይስጣት!" አለች።
ሌላይቱ ሴት ግን "ለእኔም ለእርስዋም አይ
ሁን! ለሁለት ይቈረጥ!" አለች።

10 በዚህ ዐይነት ኪራም ለሰሎሞን የሚያስፈ
ልገውን የዝግባና የጥድ ግንድ ሁሉ አቀረበ
ለት ፤ 11 ሰሎሞንም በበኩሉ በኪራም ቤተ መን
ግሥት ውስጥ ላሉት ሰዎች ቀለብ የሚሆን
ሁለት ሺ ቶን ስንዴና አራት መቶ ሺ ሊትር
ንጹሕ የወይራ ዘይት በየዓመቱ ይሰጥ ነበር ።
12 እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠውን የተ
ስፋ ቃል በመጠበቅ ለሰሎሞን ጥበብን ሰጠው ፤
በኪራምና በሰሎሞን መካከል ሰላም ስለነበረ
ሁለቱም የጋራ ስምምነት ውል አደረጉ ።
13 ንጉሥ ሰሎሞን ከመላው እስራኤል ሠላሳ
ሺ የግዳጅ ሠራተኞችን አስመረጠ ፤ 14 በእነርሱ
ላይ አዶኒራም የተባለውን ሰው ኀላፊ አድርጎ
ሾመ ፤ ሠራተኞቹንም ዐሥር ዐሥር ሺ አድርጎ
በሦስት ቡድን በመከፈል እያንዳንዱ ቡድን
ፈረቃ ገብቶ አንድ ወር በሊባኖስ እንዲሠራ ፥
ሁለት ወር ደግሞ በቤቱ እንዲያርፍ ወሰነ ።
15 ንጉሥ ሰሎሞን በኰረብታማው አገር ድንጋይ
የሚፈልጡ ሰማኒያ ሺ ፥ የተፈለጠውን ድንጋይ
ተሸክመው የሚያመጡ ሰባ ሺ ሰዎች መደበ ፤
16 የእነዚህ ሠራተኞች የበላይ ሆነው ሥራውን
የሚቈጣጠሩ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ሰዎችን አዘ
ጋጀ ፤ 17 በዚህ ዐይነት ሠራተኞቹ በንጉሥ ሰሎ
ሞን ትእዛዝ ለቤተ መቅደሱ መሠረት የሚሆን
ታላላቅ ድንጋዮችን ፈለጡ ። 18 የሰሎሞንና የኪ
ራም ጥበበኞች ሠራተኞችና እንዲሁም የቢብ
ሎስ ሰዎች ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የሚያስ
ችላቸውን ድንጋይና እንጨት ሁሉ አዘጋጁ ።

## ምዕራፍ 6

### ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመረ

1 የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር ከወጡ
ከአራት መቶ ሰማኒያ ዓመት በኋላ ሰሎሞን በእ
ስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ፥ ዚፍ
ተብሎ በሚጠራው በሁለተኛው ወር የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመረ ፤
2 ቤተ መቅደሱ በውስጥ በኩል ርዝመቱ ሃያ
ሰባት ሜትር ፥ ወርዱ ዘጠኝ ሜትር ፥ ርዝመቱ
ዐሥራ ሦስት ሜትር ተኩል ነበር ፤ 3 በመግቢ
ያው በር የሚገኘው በረንዳ ቁመቱ አራት
ሜትር ተኩል ፥ ወርዱ ልክ እንደ ቤተ መቅ
ደሱ ዘጠኝ ሜትር ነበር ። 4 ለቤተ መቅደሱም
ሕንጻ ከውስጥ ሰፋ ፥ ከውጭ ጠበብ ያሉ መስኮ
ቶች ነበሩት ፤ 5 በስተውጭ በኩል በግንቡ
ዙሪያ ከዋናው የቤተ መቅደስ ሕንጻ አስጠግቶ
ባለ ሦስት ፎቅ ግንብ በተጨማሪ ሠራ ፤ የእያን
ዳንዱም ፎቅ ቁመት ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ
ሜትር ነበር ፤ 6 የታችኛው ፎቅ ክፍል ወርዱ
ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር ፥ የሁለተኛው
ፎቅ ክፍል ወርድ ሁለት ሜትር ከሰባ ሳንቲ
ሜትር ፥ የመጨረሻው ፎቅ ክፍል ወርድ
ሦስት ሜትር ከዐሥር ሳንቲ ሜትር ነበር ፤ የእ
ያንዳንዱ ወለል ግንብ ከታች በኩል ካለው የወ
ለል ግንብ የሳሳ ነበር ፤ ይህም የሆነበት ምክን
ያት የክፍሎቹ አውታሮች ወደ ግድግዳው ዘል
ቀው ሳይገቡ በመቅረታቸው ነው ።
7 ቤተ መቅደሱ የታነጸባቸው ድንጋዮች
ተጠርበው የተዘጋጁት ፤ በዚያው በተፈለጡበት
ቦታ ነበር ፤ ስለዚህም ቤተ መቅደሱ በሚሠራ
በት ጊዜ የመዶሻ ፥ የመጥረቢያ ወይም የሌላ
ብረት ነክ መሣሪያ ድምፅ አይሰማም ነበር ።
8 ተጨማሪ ሆኖ የተሠራው ሕንጻ የታችኛው
ፎቅ መግቢያ በር የሚገኘው ከቤተ መቅደሱ
በስተደቡብ በኩል ነበር ፤ እርሱም ከሁለተኛ
ውና ከሦስተኛው ፎቅ ጋር የሚያገናኙት ደረጃ
ዎች ነበሩት ። 9 በዚህ አኳኋን ሰሎሞን የቤተ
መቅደሱን ሕንጻ ሥራ ፈጸመ ፤ ጣራውንም
ከውስጥ በኩል ከዝግባ እንጨት በተሠራ እግ
ዳሚ ሠረገላና ጠርብ ለበደው ። 10 የእያንዳንዱ
ፎቅ ቁመት ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር
ሆኖ ከውጭ በኩል ወደ ቤተ መቅደሱ ተጠግቶ
የተሠራው ባለ ሦስት ፎቅ ተጨማሪ ሕንጻ ከዋ
ናው ሕንጻዎች ከዝግባ በተሠሩት እግዳሚ ሠረ
ገላዎች የተያያዘ ነበር ።
11 እግዚአብሔር ሰሎሞንን እንዲህ አለው ፥
12-13 “ሕግጋቴንና ትእዛዛቴን ሁሉ ብትጠ
ብቅ ፥ ለአባትህ ለዳዊት የሰጠሁትን የተስፋ
ቃል ለአንተ አጸናለሁ ፤ በሕዝቤ በእስራኤል
መካከል ሆኜ አንተ በምትሠራው በዚህ ቤተ
መቅደስ ውስጥ እኖራለሁ ። ከቶም አልለያቸ
ውም ።”
14 በዚህ ዐይነት ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን
ሠርቶ ፈጸመ ።

### የቤተ መቅደሱ ውስጣዊ አሠራር
(2 ዜ.መ. 3፥8-14)

15 የቤተ መቅደሱ ግንብ ከውስጥ በኩል ከወ
ለሉ እስከ ጣራው ድረስ ከዝግባ እንጨት ተጠ
ርበው በተሠሩ ሳንቃዎች ተለበደ ፤ የወለሉም
ጣውላ ከጥድ እንጨት የተሠራ ነበር ። 16 ቅድ
ስተ ቅድሳት ተብሎ የሚጠራ አንድ ውስጣዊ
ክፍል ከቤተ መቅደሱ በስተ ኋላ ገባ ብሎ
ተሠራ ፤ የእርሱም ርዝመት ዘጠኝ ሜትር
ሲሆን ከወለሉ እስከ ጣራው ድረስ ከዝግባ እን
ጨት ተጠርቦ በተሠራ ሳንቃ የተከፈለ ነበር ፤
17 ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት የሚገኘውም
ክፍል ርዝመት ዐሥራ ስምንት ሜትር ነበር ፤
18 የዝግባውም እንጨት ሳንቃዎች በአበባ እንቡ
ጦችና በፈኩ አበባዎች ቅርጽ አጊጠው ነበር ፤
ውስጡም ሁሉ ከዝግባ እንጨት ተጠርቦ በተ
ሠራ ሳንቃ ስለተለበደ የግንቡ ድንጋዮች አይታ
ዩም ነበር ።

5፥14 ፦ 1ነገ. 12፥18 ። 6፥16 ፦ ዘጸ. 26፥33-34 ።

19 ክቤተ መቅደሱ ውስጥ በስተ ኋላ በኩል
የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት የሚቀመጥ
በት ውስጣዊ ክፍል ተሠራ ። 20 ይህም ውስጣዊ
ክፍል ርዝመቱ ዘጠኝ ሜትር ፥ ወርዱ ዘጠኝ
ሜትር ፥ ቁመቱ ዘጠኝ ሜትር ፥ ሲሆን በሙሉ
በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ነበር ፤ መሠዊያውም
ከዝግባ እንጨት ተጠርቦ በተሠራ ሳንቃ የተለ
በደ ነበር ። 21 ቤተ መቅደሱ በውስጥ በኩል
በወርቅ የተለበጠ ነበር ፤ በወርቅ በተለበጠው
ውስጠኛ ክፍል መግቢያ በር ክፈፍም በተሸጋ
ገሩ የወርቅ ሰንሰለቶች አጊጦ ነበር ። 22 በቅድ
ስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የሚገኘው መሠዊያ ጭምር
መላው ቤተ መቅደስ ክውስጥ በኩል በወርቅ
ተለብጦ ነበር ።

23 የእያንዳንዳቸው ቁመት አራት ሜትር
ከአርባ ሳንቲ ሜትር የሆነ ፥ ከወይራ እንጨት
የተሠሩ ፥ በሁለት ኪሩቤል አምሳል የተቀረጹ
ሥዕሎች በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ነበሩ ።
24-26 የሁለቱም ኪሩቤል ቅርጽና መጠን ተመሳ
ሳይ ነበር ፤ እያንዳንዱም ኪሩቤል ሁለት ክን
ፎች ነበሩት ፤ የእያንዳንዱ ክንፍ ርዝመት
ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ፥ ከአ
ንዱ ክንፍ ጫፍ እስከ ሌላው ክንፍ ጫፍ ድረስ
ያለው ርዝመት አራት ሜትር ከአርባ ሳንቲ
ሜትር ነበር ፤ 27 ኪሩቤሉም በቅድስተ ቅዱሳኑ
ውስጥ ጐን ለጐን እንዲቆሙ ተደረገ ፤ ስለዚ
ህም የተዘረጉ ሁለቱ ክንፎቻቸው በክፍሉ መካ
ከለኛ ቦታ ላይ ተገናኝተው ሌሎቹ ሁለቱ ክን
ፎቻቸው ደግሞ በተዘረጉበት አቅጣጫ ግንቦ
ቹን ይነኩ ነበር ። 28 ሁለቱም ኪሩቤል በወርቅ
የተለበጡ ነበሩ ።

29 የዋናው ክፍልና የውስጠኛው ክፍል ግን
ቦች በሙሉ በኪሩቤል ፥ በዘንባባ ዛፎችና በፈኩ
የአበባ ቅርጾች አጊጠው ነበር ፤ 30 ከውስጥና
ከውጭ በኩል ያሉት ክፍሎች ወለል እንኳ
በወርቅ ተለብጦ ነበር ።

31 ከወይራ እንጨት የተሠራ ሁለት ተከፋች
በር በቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ እንዲቆም ተደ
ረገ ፤ በሩም አምስት ማእዘን ያለው ሆኖ አናቱ
ላይ ቀጥ ብሎ የተሠራ ቅስት ነበር ። 32 በሮቹ
በኪሩቤል ፥ በዘንባባ ዛፎችና በፈኩ የአበባ ቅር
ጾች አጊጠው ነበር ፤ በሮቹ ፥ ኪሩቤሉ ፥ የዘን
ባባ ዛፎቹ ፥ ቅርጾችም በወርቅ ተለብጠው
ነበር ። 33 እንዲሁም ወደ ዋናው ክፍል ለሚያ
ደርሰው መግቢያ በር ከወይራ እንጨት የተሠራ
ባለ አራት ማእዘን ክፈፍ ተበጅቶለት ነበር ።
34 ከጥድ እንጨት የተሠሩ ሁለት ታጣፊ በሮ
ችም ነበሩት ፤ 35 እነርሱም ሙሉ በሙሉ በወ
ርቅ በተለበጡ በኪሩቤል ፥ በዘንባባ ዛፎችና
በፈኩ የአበባ ቅርጾች አጊጠው ነበር ።

36 በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት አንድ የውስጥ
አደባባይ ተሠራ ፤ በዚህም አደባባይ ዙሪያ በየ
ሦስቱ ዙር የድንጋይ ረድፍ አንድ የዝግባ ሠረ
ገላ የተጋደመበት ግንብ ነበር ።

37 ይህም ቤተ መቅደስ መሠረቱ የተጣለው
ሰሎሞን በነገሠ በአራተኛው ዓመት ፥ ዚፍ
ተብሎ በሚጠራው በሁለተኛው ወር ነበር ።
38 ሰሎሞን በነገሠ በዐሥራ አንደኛ ዓመቱ ፥
ቡል ተብሎ በሚጠራው በስምንተኛው ወር
ላይ የቤተ መቅደሱ ሥራ ልክ በታቀደው መሠ
ረት ሙሉ በሙሉ ተጠናቀቀ ፤ ሰሎሞን ቤተ
መቅደሱን ለመሥራት የፈጀበት ጊዜ ሰባት
ዓመት ነበር ።

## ምዕራፍ 7

### ሰሎሞን ቤተ መንግሥቱን ሠራ

1 ሰሎሞን ለራሱ የሚሆን ቤተ መንግሥት
ሠራ ፤ ቤተ መንግሥቱንም ለመሥራት ዐሥራ
ሦስት ዓመት ፈጀበት ፤ 2-3 "የሊባኖስ ደን"
ተብሎ የተጠራው አዳራሽ ርዝመቱ አርባ
አራት ሜትር ፥ ወርዱ ሃያ ሁለት ሜትር ፥
ቁመቱ ዐሥራ ሦስት ሜትር ተኩል ነበር ፤ አዳ
ራሹም በእያንዳንዱ ረድፍ ሀሥራ አምስት
ሆነው በሦስት ረድፍ የቆሙ አርባ አምስት
ምሰሶዎች ነበሩት ፤ በምሰሶዎቹም ላይ የተጋ
ደሙ ፥ ከዝግባ እንጨት የተሠሩ ሠረገላዎች
ነበሩ ፤ ከእነርሱም በላይ በምሰሶዎቹ የተደገፉ
ዕቃ ቤቶች ነበሩ ፤ የእነዚህም ዕቃ ቤቶች ጣራ
ከዝግባ እንጨት የተሠራ ነበር ፤ 4 ትይዩ የሆ
ኑት የሕንጻው ሁለት ግንቦች እያንዳንዳቸው
በመደዳ ሦስት ሦስት መስኮቶች ነበሩአቸው ።
5 በሮቹና መስኮቶቹ ሁሉ ባለአራት ማእዘን
መቃኖች ነበሩአቸው ፤ ለእያንዳንዱ ግንብ በረ
ድፍ የተሠሩ ሦስት ሦስት መስኮቶች ነበሩት ፤
የእያንዳንዱ ግንብ መስኮቶች ከሌላው ግንብ
መስኮቶች ጋር ትይዩ ነበሩ ።

6 "ባለ ብዙ ምሰሶ" ተብሎ የተጠራው አዳ
ራሽ ርዝመቱ ሃያ ሁለት ሜትር ፥ ወርዱ
ሀሥራ ሦስት ሜትር ተኩል ነበር ፤ በብዙ ምሰ
ሶዎች የተደገፈና ጣራ የተሠራለት መመላለሻ
ታዛም ነበረው ።

7 ሰሎሞን ችሎት ተቀምጦ የፍርድ ውሳኔ
የሚሰጥበትም የዙፋን አዳራሽ ከወለሉ እስከ
ጣራው ድረስ ከዝግባ እንጨት በተሠራ ሳንቃ
የተለበደ ነበር ።

8 ከችሎቱም አዳራሽ በስተ ኋላ በሚገኘው
ሌላ አደባባይ ሰሎሞን የሚኖርበት ሕንጻ እንደ
ሌሎቹ ሕንጻዎች ሆኖ ተሠራ ፤ የግብጽ ንጉሥ
ልጅ ለነበረችው ሚስቱም ተመሳሳይ መኖሪያ
ቤት አሠራላት ።

6፥22 ፡- ዘጸ. 30፥1-3 ።  6፥23-28 ፡- ዘጸ. 25፥18-20 ።  7፥8 ፡- 1ነገ. 3፥1 ።

9 እነዚህ ሁሉ ሕንጻዎችና ታላቁ አደባባይ
ጭምር ከመሠረታቸው እስከ ድምድማቸው
በጥሩ ታላላቅ ድንጋዮች አጊጠው የተሠሩ
ነበሩ፤ ድንጋዮቹ በዚያም በድንጋይ መፍለጫ
ስፍራ በፊትም በኋላም በልክ ተጠርበውና ተከ
ርክመው የመጡ ነበሩ። 10 መሠረቱም የተሠ
ራው በዚያው በድንጋይ መፍለጫ ስፍራ ተዘጋ
ጅተው በመጡ ታላላቅ ድንጋዮች ነበር፤ ከታላ
ላቆቹም ድንጋዮች ውስጥ የአንዳንዱ ጥርብ
ድንጋይ ርዝመት ሦስት ሦስት ሜትር ተኩል
ሲሆን፥ የሌሎቹ ደግሞ አራት ሜትር ነበር።
11 በእነዚህም ታላላቅ ድንጋዮች ላይ በልክ የተ
ሠሩ ሌሎች ድንጋዮችና ከዝግባ እንጨት የተ
ሠሩ አግዳሚ ሠረገላዎች ነበሩ። 12 የቤተ መን
ግሥቱ አደባባይ፥ የቤተ መቅደሱ ውስጣዊ አደ
ባባይና ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያስገባው በር
በእያንዳንዱ ባለ ሦስት ረድፍ የጥርብ ድንጋይ
ሕንጻ ላይ አንዳንድ ረድፍ የዝግባ እንጨት ሠረ
ገላ የተጋደመባቸው ግንቦች ነበሩ።

### ለሑራም የተመደበለት ሥራ

13 ሰሎሞንም ሑራም የተባለውን ሰው ከጢ
ሮስ ከተማ አስጠራ፤ 14 ሑራም ነሐስ አቅልጦ
በመሥራት ጥበብ የሠለጠነ ባለሞያ ነበር፤
ቀደም ብሎ የሞተው የሑራም አባትም የጢ
ሮስ ተወላጅ ሲሆን እርሱም ነሐስ አቅልጦ
በመሥራት ጥበብ የሠለጠነ ባለሞያ ነበር፤ የሑ
ራም እናት የንፍታሌም ነገድ ተወላጅ ነበረች፤
ሑራም በእጅ ጥበብ ብዙ ልምድ ያለው ብልህ
ሰው ነበር፤ ከንጉሥ ሰሎሞን በተደረገለት ጥሪ
መሠረት መጥቶ በተመደበለት የነሐስ ሥራ
ሁሉ ላይ ኀላፊ ሆነ።

### ከነሐስ የተሠሩት ሁለት ምሰሶዎች
(2 ዜ.መ. 3፥15-17)

15 ሑራም የእያንዳንዳቸው ቁመት ስምንት
ሜትር፥ የዙሪያ ስፋታቸው አምስት ሜትር ከሠ
ላሳ ሳንቲ ሜትር የሆነ ሁለት የነሐስ ምሰሶዎችን
ሠርቶ በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ላይ አቆማ
ቸው፤ 16 እንዲሁም በምሰሶዎቹ ላይ የሚቆሙ
የእያንዳንዳቸው ቁመት ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ
ሜትር የሆነ ሁለት የነሐስ ጉልላቶችን ሠራ።
17 የእያንዳንዱን ምሰሶ ጫፍ የመረብ ቅርጽ ባላ
ቸው ሰንሰለቶችና፥ 18 ከነሐስ የተሠሩ፥ በሁለት
ረድፍ በተደረደሩ የሮማን ቅርጾች አስጌጠ።
19 በመመላለሻው ምሰሶዎች አናት ላይ
ያሉት ጉልላቶች ቁመታቸው አንድ ሜትር ከሰ
ማኒያ ሳንቲ ሜትር ሲሆን የጽዋ ቅርጽ ያለው
አበባ ይመስሉ ነበር፤ 20 እነርሱም ከሰንሰለቶቹ
ቅርጽ በላይ ባለው ክብ ስፍራ እንዲቆሙ ተደ
ረገ፤ በእያንዳንዱም ጉልላት ዙሪያ በሁለት
ረድፍ የተደረደሩ ሁለት መቶ የሮማን ቅርጾች
ነበሩ።
21 ሑራም ከነሐስ የተሠሩትን ሁለት ምሰሶ
ዎች በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ፊት ለፊት
አቆማቸው፤ ከቤተ መቅደሱ መግቢያ በር
በስተ ደቡብ በኩል የቆመው ምሰሶ ያኪን[2*]
ተብሎ ተጠራ፤ በስተ ሰሜን በኩል የቆመው
ምሰሶ ደግሞ ቦዔዝ[3*] ተባለ። 22 በምሰሶዎቹ
ጫፍ ላይ የጽዋ ቅርጽ ያላቸው አበባዎች የሚ
መስሉ ከነሐስ የተሠሩ ጉልላቶች ነበሩ።
የምሰሶዎቹም ሥራ በዚህ ዐይነት ተፈጸመ።

### ከነሐስ የተሠራ በርሜል
(2 ዜ.መ. 4፥2-5)

23 ሑራም ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር
ጥልቀት፥ አራት ሜትር ከአርባ ሳንቲ ሜትር
የክብ ማእከል ርዝመት፤ ዐሥራ ሦስት ሜትር
ከሃያ ሳንቲ ሜትር ዙሪያ ያለው አንድ ክብ በር
ሜል ከነሐስ ሠራ። 24 የበርሜሉ አፍ ውጫዊ
ከፈፍ ሁሉ ከበርሜሉ ጋር አንድ ወጥ ሆነው
በቅል አምሳል ከነሐስ የተሠሩና በሁለት ረድፍ
የተደረደሩ፥ ቅርጾች ነበሩት። 25 በርሜሉም
ከነሐስ በተሠሩ ዐሥራ ሁለት የኮርማዎች ምስ
ሎች ጀርባ ላይ ተቀመጠ፤ ኮርማዎቹም በየአቅ
ጣጫው ፊታቸውን ወደ ውጭ መልሰው ሦስቱ
ወደ ሰሜን፥ ሦስቱ ወደ ደቡብ፥ ሦስቱ ወደ
ምሥራቅ ሦስቱ ወደ ምዕራብ የሚመለከቱ
ይመስሉ ነበር። 26 የበርሜሉ ጐኖች ውፍረት
ሰባ አምስት ሚሊ ሜትር ነበር፤ የጽዋ ቅርጽ
ያለው አበባ የሚመስል የአፉ ከፈፍ ወደ ውጭ
ተቀልብሶ የታጠፈ ነበር፤ ይህም በርሜል አርባ
ሺ ሊትር ያህል ውሃ የሚይዝ ነበር።

### ከነሐስ የተሠሩ ባለመንኰራኲር
### የዕቃ ማስቀመጫ

27 ሑራም የእያንዳንዱ ርዝመት አንድ
ሜትር ከሰማኒያ ሳንቲ ሜትር፥ ወርዱ አንድ
ሜትር ከሰማኒያ ሳንቲ ሜትር፥ ቁመቱ አንድ
ሜትር ከሠላሳ ሳንቲ ሜትር የሆነ ዐሥር ባለ
መንኰራኲር የዕቃ ማስቀመጫዎች ከነሐስ
ሠራ። 28 የዕቃ መቀመጫዎቹም የተሠሩት በአ
ውታር ከተያያዙና እኩል ከሆኑ ከባለ አራት
ማእዘን ጠፍጣፋ ነሐሶች ነበር። 29 በጠፍጣፋ
ዎቹም ነሐሶች ላይ በአንበሶች፥ በኮርማዎችና
በኪሩቤል አምሳል የተቀረጹ ሥዕሎች ነበሩ፤
ከአንበሶቹ፥ ከኮርማዎቹና ከኪሩቤሉ ቅርጾች
የራስጌና የግርጌ አውታሮችም ላይ የአበባ ጉን
ጉን የሚመስሉ ቅርጾች ነበሩ፤ 30 እያንዳንዱ
የዕቃ ማስቀመጫ ከነሐስ የተሠሩ አራት

2* 7፥21 ያኪን፦ በዕብራይስጥ “እግዚአብሔር ያቆማል” ማለት ነው።
3* 7፥21 ቦዔዝ፦ በዕብራይስጥ “በእግዚአብሔር ኀይል” ማለት ነው።

መንኰራኵሮችና መንኰራኵሮቹ የሚሽከረከሩ
በት የነሐስ ወስከምቶች ነበራቸው፤ እንዲሁም
በአራቱ ማእዘኖች የመታጠቢያ ገንዳ መደገፊያ
ዎች ነበሩ፤ መደገፊያዎቹም የአበባ ጕንጕን
በሚመስሉ ቅርጾች አጊጠው ነበር። 31 የመታጠ
ቢያ ገንዳውም መደገፊያ ጫፍ ክብ ክፈፍ ነበ
ረው፤ ክፈፉም ከዕቃ ማስቀመጫው ጫፍ ወደ
ላይ ከፍ ብሎ አርባ አምስት ሳንቲ ሜትር፥ ወደ
ታች ደግሞ ዐሥራ ስምንት ሳንቲ ሜትር ወረድ
ብሎ የተሠራ ነበር፤ ዙሪያውም በቅርጽ ያጌጠ
ነበር። 32 የመንኰራኵሮቹም ቁመት ስልሳ ስድ
ስት ሳንቲ ሜትር ነበር፤ መንኰራኵሮቹም
በዕቃ ማስቀመጫው ጠፍጣፋ ነሐስ ሥር ነበሩ፤
የመንኰራኵሮችም ወስከምቶች ከዕቃ ማስቀመ
ጫዎቹ ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ፤
33 መንኰራኵሮቹም የሠረገላ መንኰራኵሮችን
ይመስሉ ነበር፤ ወስከምቶቻቸው፥ ማገናኛ ሽቦ
ዎቻቸውና አቃፊዎቻቸው ሁሉም ከነሐስ የተ
ሠሩ ነበሩ። 34 የእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ
አራት ማእዘኖች በየግርጌአቸው ከእነርሱው ጋር
አንድ ወጥ ሆነው ከነሐስ የተሠሩ አራት መደገ
ፊያዎች ነበሩአቸው። 35 በእያንዳንዱ የዕቃ ማስ
ቀመጫ ጫፍ ዙሪያ ክፈፍ ላይ ሃያ ሁለት ሳንቲ
ሜትር ርዝመት ያለው አንድ ክብ ቅርጽ ነበር፤
መደገፊያዎቹና ጠፍጣፋ ነሐሶቹ ከዕቃ ማስቀ
መጫው ጋር አንድ ወጥ ሆነው የተሠሩ ነበሩ።
36 እነዚሁ መደገፊያዎችና ጠፍጣፋ ነሐሶች
መካከል ባለው ክፍት ቦታ ሁሉ በኪሩቤል፥ በአ
ንበሶችና በዘንባባ ዛፎች አምሳል በተሠሩ ቅርጾች
አጊጠው ነበር፤ እንዲሁም ዙሪያቸው የአበባ
ጕንጕን በሚመስሉ ቅርጾች አጊጠው ነበር።
37 እንግዲህ ዐሥሩ ባለመንኰራኵር የዕቃ ማስቀ
መጫዎች የተሠሩት በዚህ ዐይነት ሁኔታ ነበር።
መጠናቸውና ቅርጻቸው እኩል ስለሆነ ሁሉም
ተመሳሳይ ነበሩ።

38 ሑራም ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ
ዐሥር መታጠቢያ ገንዳዎች ሠራ፤ እያንዳንዱ
ገንዳ ዙሪያ አጋማሽ ስፋት አንድ ሜትር ከሰማ
ኒያ ሳንቲ ሜትር ያህል ሲሆን፥ ስምንት መቶ
ሊትር ያህል ውሃ ይይዝ ነበር፤ 39 ሑራምም
አምስቱን የዕቃ ማስቀመጫዎች ከቤተ መቅደሱ
በስተደቡብ፥ የቀሩትንም አምስቱን በቤተ መቅ
ደሱ በስተ ሰሜን በኩል አቆመ፤ በርሜሉን
ደግሞ በቤተ መቅደሱ ደቡባዊ ምሥራቅ ማእ
ዘን ላይ አቆመው።

### የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች ዝርዝር ባጭሩ
### (2 ዜ.መ. 4፥11–5፥1)

40 ሑራም ምንቸቶችን፥ መጫሪያዎችንና
ድስቶችን ሠራ፤ በዚህ ዐይነት ሁኔታም ለን
ጉሥ ሰሎሞን ሊሠራለት የጀመረውን የእግዚ
አብሔርን መቅደስ ሥራ ፈጸመ፤ ከሠራቸ
ውም ነገሮች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት
ናቸው፦

41 ሁለቱ ምሰሶዎች፥
በምሰሶዎቹ ጫፍ ላይ በኩብ ቅርጽ
የተሠሩ ሁለት ጕልላቶች፥
42 በእያንዳንዱ ጕልላት ላይ በመረብ
አምሳል የተሠሩት ሰንሰለቶች፥
በእያንዳንዱ ጕልላት ቅርጽ ላይ በሁለት
ረድፍ አንዳንድ መቶ ዙር የሆኑ፥
ከነሐስ የተሠሩ አራት መቶ የሮማን
ቅርጾች፥
43 ዐሥሩ ባለመንኰራኵር የዕቃ
ማስቀመጫዎች፥
ዐሥሩ የመታጠቢያ ገንዳዎች፥
44 ውሃ ማጠራቀሚያ በርሜል፥
በርሜሉን ደግፈው የሚይዙ የዐሥራ
ሁለቱ ኮርማዎች ቅርጾች፥
45 ድስቶቹ፥ መጫሪያዎቹና ጐድጓዳ
ሳሕኖቹ፤

ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት ይውሉ ዘንድ
ሑራም እነዚህን ሁሉ ዕቃዎች ለሰሎሞን የሠራ
ለት ከተወለወለ ንጹሕ ነሐስ ነበር። 46 ንጉሥ
ሰሎሞን እነዚህን ሁሉ ያሠራው በዮርዳኖስ
ሸለቆ በሱኮትና ጻርታን መካከል በሚገኘው
በብረት ማቅለጫ ስፍራ ነበር። 47 ከነሐስ የተሠ
ራው ይህ ሁሉ ዕቃ እጅግ ብዙ ስለነበር፥ ሰሎ
ሞን በሚዛን እንዲለካ አላደረገውም፤ ስለዚህ
ክብደቱ ምን ያህል እንደሆነ ተወስኖ አልታወ
ቀም።

48 ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት ይውሉ ዘንድ
ሰሎሞን የሚከተሉትን ዕቃዎች ከንጹሕ ወርቅ
አሠራ፤ እነርሱም መሠዊያው፥ ለእግዚአብሔር
የሚቀርበው ኅብስት ማኖሪያ ጠረጴዛ፥ 49 በቅ
ድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት አምስቱ በስተደ
ቡብ፥ አምስቱ ደግሞ በስተ ሰሜን የሚቀመ
ጡት ዐሥሩ መቅረዞች፥ አበባዎች፥ የመብራት
ቀንዲሎች፥ የእሳት መቆስቆሺያዎች፥ 50 ጽዋ
ዎች፥ የመብራት መኰስተሪያዎች፥ ድስቶች፥
የዕጣን ማቅረቢያ ዕቃ፥ የእሳት መጫሪያ ዕቃ፥
ለቅድስተ ቅዱሳን በሮችና ለቤተ መቅደሱ
ውጫዊ በሮች የሚያገለግሉ ማጠፊያዎች
ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ዕቃዎች ከወርቅ የተሠሩ
ናቸው።

51 ንጉሥ ሰሎሞን የቤተ መቅደሱን ሥራ
ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ ዳዊት ለእግዚአብ
ሔር ቤት አገልግሎት እንዲውል የለየውን
ብሩን፥ ወርቁንና ሌላውንም ዕቃ በሙሉ በቤተ
መቅደሱ ግምጃ ቤት ውስጥ አኖረው።

7፥38 ፦ ዘጸ. 30፥17-21። 7፥48 ፦ ዘጸ. 25፥23-30፤ 30፥1-3። 7፥49 ፦ ዘጸ. 25፥31-40። 7፥51 ፦ 2ሳሙ. 8፥11፤
1ዜ.መ. 18፥11።

ሁሉ እነሆ ዛሬ ተፈጽሞአል፤ 25 እሁንም የእስ
ራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ለአባቴ ለዳ
ዊት የገባኸውን ሌላውንም ቃል ኪዳን ፈጽም፤
ይኸውም ‘አንተ ታደርግ በነበረው ዐይነት ልጆ
ችህ ታዛዥዎች ቢሆኑና በፊቴም በቅንነት ቢመ
ላለሱ ሁል ጊዜ ከዘርህ በእስራኤል ዙፋን ላይ
በፊቴ የሚነግሥ ልጅ አላላጣህም’ ስትል የተና
ገርከው የተሰፋ ቃል ነው። 26 እንግዲህ የእስራ
ኤል አምላክ ሆይ! አገልጋይህ ለነበረው ለአባቴ
ለዳዊት የሰጠኸው የተስፋ ቃል ሁሉ እንዲፈ
ጸም አድርግ።

27 “እምላክ ሆይ! በእውነት ምድር የአንተ
መኖሪያ ለመሆን ትበቃለችን? እነሆ ሰማየ ሰማ
ያት እንኳ የማይበቃህ ሆኖ ሳለ፥ ይህች እኔ
የሠራኋት ቤተ መቅደስማ የአንተ መኖሪያ ለመ
ሆን እንዴት ልትበቃ ትችላለች? 28 እግዚአብ
ሔር አምላኬ ሆይ! እነሆ እኔ አገልጋይህ ነኝ፤
ስለዚህ ጸሎቴን ሰምተህ ዛሬ የምለምንህን
ስጠኝ። 29 አንተ ልትመለክበት በመረጥከው
ቦታ የተሠራውንም ቤተ መቅደስ ቀንና ሌሊት
ጠብቀው፤ ፊቴን ወደዚህ ቤተ መቅደስ መልሼ
በምጸልይበት ጊዜ ልመናዬን ስማ፤ 30 ፊታች
ንን ወደዚህ ቤተ መቅደስ መልሰን በምንጸልይ
በት ጊዜ የእኔንና የሕዝብህን ጸሎት ስማ፤ መኖ
ሪያህ በሆነው በሰማይ ሆነህ ስማን፤ ይቅርም
በለን።

31 “አንድ ሰው ባልንጀራውን መበደሉን
የሚገልጥ ክስ ቀርቦበት በዚህ ቤተ መቅደስ
ውስጥ ወደሚገኘው መሠዊያ እምጥተዉት ከበ
ደል ንጹሕ መሆኑን በመሐላ በሚያረጋግጥበት
ጊዜ፥ 32 እግዚአብሔር ሆይ! በሰማይ ሆነህ
ስማ፤ ለአገልጋዮችህም ፍርድን ስጥ፤ ይኸውም
በደል የሠራው ሰው በጥፋቱ መጠን እንዲ
ቀጣ፥ ንጹሑም ነፃ እንዲወጣ አድርግ።

33 “ሕዝብህ እስራኤል በደል ሠርተው አን
ተን በማሳዘናቸው ምክንያት በጠላቶቻቸው
ድል ሲሆኑ ተጸጽተውም ወደ አንተ በመመለስ
ወደዚህ ቤተ መቅደስ ቢመጡና የአንተን ይቅ
ርታ ለማግኘት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በትሕ
ትና ቢለምኑህ፥ 34 አንተ በሰማይ ሆነህ ጸሎታ
ቸውን ስማ፤ በምርኮ የሚገኙትንም ሕዝብህን
ኃጢአት ይቅር በማለት ለቀድሞ አባቶቻቸው
ወደሰጠሃቸው ምድር መልሰህ አግባቸው።

35 “ሕዝብህ በደል ሠርተው አንተን በማሳዘ
ናቸው ምክንያት ዝናም እንዳይዘንምላቸው
አድርገህ በምትቀጣቸው ጊዜ፥ በፈጸሙት
በደል በመጸጸት ፊታቸውን ወደዚህ ቤተ መቅ
ደስ መልሰው በትሕትና ቢለምኑህ፥ 36 አንተ
በሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውን ስማ፤ የንጉሡንና
የእስራኤልንም ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል፤
ቅን የሆነውንም ነገር ማድረግ ይችሉ ዘንድ አስ
ተምራቸው፤ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር
ሆይ! ለዘላለም ርስት አድርገህ ለሕዝብህ በሰጠ
ሃቸው በዚህች ምድር ዝናም እንዲዘንም አድ
ርግ።

37 “በምድሪቱ ላይ ረሀብ ወይም አባር ቸነ
ፈር በሚመጣበት ጊዜ፥ እንዲሁም የእህሉ
ሰብል በሚያቃጥል ነፋስ፥ በዋግና በአንበጣ
መንጋ በሚወድምበት ጊዜ፥ ወይም ጠላቶቻ
ቸው በሕዝብ ላይ አደጋ በሚጥሉበት ጊዜ፥
ወይም በሕዝብህ ላይ ልዩ በሽታና ደዌ በሚደ
ርስባቸው ጊዜ፥ 38 ጸሎታቸውን ስማ፤ በሕዝ
ብህ በእስራኤል መካከል ልብን የሚያሸብር
መራር ሐዘን ደርሶባቸው እጃቸውን ወደዚህ
ቤተ መቅደስ በመዘርጋት በሚጸልዩበት ጊዜ፥
39 ጸሎታቸውን ስማ፤ በምትኖርበት በሰማይ
ሆነህ ጸሎታቸውን በመስማት በደላቸውን
ይቅር በላቸው፤ ዕርዳቸውም፤ በሰው ልብና
አእምሮ ያለውን አሳብ ሁሉ መርምረህ የምታ
ውቅ አንተ ብቻ ነህ፤ ስለዚህ ለእያንዳንዱ ሰው
እንደሥራው መጠን የሚገባውን ዋጋ ስጠው፤
40 በዚህም ዐይነት ሕዝብህ ለቀድሞ አባቶቻችን
ርስት አድርገህ በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩበት
ዘመን ሁሉ ለአንተ ታዛዥዎች እንዲሆኑና እን
ዲያከብሩህ አድርግ።

41-42 “በሩቅ አገር የሚኖር የውጭ አገር
ሰው የስምህን ገናናነትና ለሕዝብህ ያደረግኸ
ውን ድንቅ ነገር ሁሉ ሰምቶ፥ በዚህ ቤተ
መቅደስ ሊያመልክህና ሊጸልይ ቢመጣ፥
43 አንተ ጸሎቱን ስማ፤ ሕዝብህ እስራኤል
እንደሚያደርጉት በመላው ዓለም የሚኖሩ
ሕዝቦች አንተን በማወቅ እንዲታዘዙህና እንዲ
ያከብሩህ አድርግ፥ በምትኖርበት በሰማይ
ሆነህ የዚህን ሰው ጸሎት ስማ፤ እንድታደርግ
ለት የሚለምንህንም ሁሉ ፈጽምለት፤ ይህም
በሚሆንበት ጊዜ ይህ እኔ የሠራሁት ቤተ
መቅደስ አንተ የምትመለክበት ስፍራ መሆኑን
ያውቃሉ።

44 “ጠላቶቻቸውን ለመውጋት እንዲዘምቱ
ሕዝብህን በምታዝዝበት ጊዜ በየትኛውም
ስፍራ ሆነው ወደዚህች ወደመረጥሃት ከተማና
እኔ ለአንተ ወደ ሠራሁት ወደዚህ ቤተ መቅ
ደስ ፊታቸውን መልሰው በሚጸልዩበት ጊዜ፥
45 በሰማይም ሆነህ ጸሎታቸውንና ልመናቸውን
በመስማት ድልን አቀዳጃቸው።

46 “መቼም በደል የማይሠራ የለምና ሕዝ
ብህ ኃጢአት በመሥራት አንተን ሲያሳዝኑህ፥
አንተም ተቈጥተህ ጠላቶቻቸው ድል እንዲነሡ
እቸውና ወደ ሌላ አገር ማርከው እንዲወስዱእ
ቸው በምትፈቅድበት ጊዜ፥ ምንም እንኳ ያ
አገር ሩቅ ቢሆን፥ 47 ምርኮኞች ሆነው በሚኖ
ሩበት በዚያች አገር ሳሉ ‘ኃጢአት ሠርተናል፤

8፥25 ፡- 1ነገ. 2፥4። 8፥27 ፡- 2ዜ.መ. 2፥6። 8፥29 ፡- ዘዳ. 12፥11።

በድለናል፤ ዐምፀናልም’ ብለው በመናዘዝ ተጸ
ጽተው ንስሓ ቢገቡ፥ እግዚአብሔር ሆይ! ጸሎ
ታቸውን ስማ፤ 48 ማርከው በወሰዱአቸው በጠላ
ቶቻቸው አገር ሳሉ በፍጹም ልባቸው በእውነ
ትና በቅን መንፈስ ተጸጽተው ንስሓ በመግባት
አንተን ለቀድሞ አባቶቻችን ወደሰጠሃቸው ወደ
ዚህች ምድር፥ አንተም ወደመረጥሃት ወደዚ
ህች ከተማና እኔ ለአንተ ወደ ሠራሁት ወደዚህ
ቤተ መቅደስ ፊታቸውን መልሰው ቢጸልዩ፥
49 በመኖሪያህ በሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውን በመስ
ማት ፍረድላቸው፤ 50 ኃጢአታቸውንና አንተን
ያሳዘኑበትን ዐመፅ ሁሉ ይቅር በል፤ ጠላቶቻቸ
ውም እንዲራሩላቸው አድርግ፤ 51 እነርሱ እኮ
እንደ እቶን እሳት ከምታቃጥል ከግብጽ ምድር
ያወጣሃቸው ሕዝብህ ናቸው።

52 “ሕዝብህ እስራኤልና ንጉሣቸው ዘወትር
በፊትህሞገስ እንዲኖራቸው አድርግ፤ የአንተ
ንም ዕርዳታ በሚጠይቁበት ጊዜ ሁሉ ጸሎታቸ
ውን ስማ፤ 53 ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! የቀ
ድሞ አባቶቻችንን ከግብጽ ምድር ባወጣህ ጊዜ
በአገልጋይህ በሙሴ አማካይነት እንደተናገርህ
ሁሉ ለአንተ የተለዩ ሕዝብ እድርገህ ከሌሎች
ሕዝቦች መካከል የመረጥካቸው መሆኑን
አስብ።”

### የጸሎቱ መደምደሚያ

54 ሰሎሞን ጸሎቱን ከፈጸመ በኋላ እጆቹን
እንደዘረጋ ተንበርክኮ ከነበረበት መሠዊያ ፊት
ተነሥቶ ቆመ። 55 ድምፁንም ከፍ በማድረግ
በዚያ ተሰብስቦ በነበረው ሕዝብ ሁሉ ላይ የእግ
ዚአብሔር በረከት እንዲወርድ እንዲህ ሲል
ጸለየ፥ 56 “በገባው የተስፋ ቃል መሠረት ለሕ
ዝቡ ሰላምን የሰጠ እግዚአብሔር ይመስገን፤ በአ
ገልጋዩ በሙሴ አማካይነት የሰጠውን መልካም
የተስፋ ቃል ሁሉ ጠብቆአል፤ 57 አምላካችን
እግዚአብሔር ከቀድሞ አባቶቻችን ጋር እንደነ
በረ ሁሉ ከእኛ ጋርም ይኑር፤ ምንጊዜም አይለ
የን፤ አይተወንም፤ 58 ለቀድሞ አባቶቻችን የሰጠ
ውን ሕግና ትእዛዝ በመጠበቅ እንደ እርሱ
ፈቃድ መኖር እንድንችል ለእርሱ ታዛዦች እን
ድንሆን ያድርገን። 59 አምላካችን እግዚአብሔር
ይህን የመማጠኛ ጸሎቴን ሁሉ በማሰብ ለእስራ
ኤል ሕዝብና ለንጉሣቸው እንደየዕለታዊ ችግራ
ቸው ምሕረቱንና ዕርዳታውን አያርቅባቸው።
60 በዚህ ዐይነት ሁኔታ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እግ
ዚአብሔር ብቻ አምላክ መሆኑንና ያለ እርሱም
ሌላ አምላክ አለመኖሩን ያውቃሉ፤ 61 እናንተ
የእርሱ ሕዝብ የሆናችሁ ዛሬ እንዳደረጋችሁት
ሁሉ ሕጎጋቱንና ትእዛዛቱን በመጠበቅ ለአምላካ
ችን ለእግዚአብሔር ዘወትር ታማኞች ሁኑ።”

### የቤተ መቅደሱ መመረቅ
(2 ዜ.መ. 7፥4-10)

62 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞንና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋ
ዕት አቀረቡ፤ 63 ሰሎሞንም ሃያ ሁለት ሺ የቀ
ንድ ከብቶችንና አንድ መቶ ሃያ ሺ በጎችን ለደ
ኅንነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት አድርጎ
አቀረበ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ ንጉሥ ሰሎሞ
ንና ሕዝቡ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር የተ
ለየ እንዲሆን አደረጉ። 64 እንዲሁም በዚያኑ
ቀን ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ያለውን አደባ
ባይ መካከለኛ ክፍል ለእግዚአብሔር የተለየ
እንዲሆን አደረገ፤ ቀጥሎም በሙሉ የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕት፥ የእህል ቊርባንና ለደኅንነት
መሥዋዕት የሚሆነውን የእንስሳት ስብ ሁሉ
ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ይህንንም ያደረገበት
ምክንያት ከነሐስ የተሠራው መሠዊያ ይህን
ሁሉ መሥዋዕት መያዝ ስለማይችል ነው።

65 በዚያም በቤተ መቅደሱ ሰሎሞንና የእስ
ራኤል ሕዝብ ሁሉ ሰባት ቀን** ሙሉ የዳስ
በዓል አከብረው ሰነበቱ፤ በሰተ ሰሜን ከሐማት
መተላለፊያ እንሥቶ በስተ ደቡብ እስከ ግብጽ
ድንበር ድረስ ካለው ምድር ሁሉ የመጣው
ሕዝብ እጅግ ብዙ ነበር፤ 66 በስምንተኛው ቀን
ሰሎሞን ወደሚኖርበት ስፍራ እንዲሄድ ሕዝ
ቡን ሁሉ አሰናበተ፤ ሁሉም ሰሎሞንን አመስ
ገኑ፤ እግዚአብሔር ለአገልጋዩ ለዳዊትና ለሕ
ዝቡ ለእስራኤል ስለሰጠውም በረከት ደስ ብሎ
አቸው ወደየቤታቸው ሄዱ።

## ምዕራፍ 9

### እግዚአብሔር ለሰሎሞን እንደገና ተገለጠለት
(2 ዜ.መ. 7፥11-22)

1 ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን፥ ቤተ
መንግሥቱንና ሊሠራው የፈለገውን ሌላውንም
ሁሉ ከፈጸመ በኋላ፥ 2 እግዚአብሔር ከዚህ
በፊት በገባዖን እንደተገለጠለት አሁንም እንደ
ገና ተገለጠለት። 3 እንዲህም አለው፥ “የመማ
ጠኛ ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እኔ እመለክበት
ዘንድ የሠራኸውን ይህን ቤተ መቅደስ ስሜ ለዘ
ላለም በእርሱ እንዲኖርበት አድርጌ ቀድሼዋ
ለሁ፤ ዘወትርም በመከባከብ እጠብቀዋለሁ።
4 አባትህ ዳዊት እንዳደረገው በቅንነትና በታማ
ኝነት እኔን ብታገለግል፥ የእኔን ሕግና ሥርዓት
ብትጠብቅ፥ ያዘዝኩህንም ሁሉ ብትፈጽም፥
5 ለአባትህ ለዳዊት ‘ከዘሮችህ በእስራኤል ዙፋን
ላይ የሚነግሥ ልጅ አላሳጣህም’ በማለት የሰጠ
ሁትን የተስፋ ቃል በመጠበቅ፥ ዙፋንህ በእስ
ራኤል ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር አደርጋለሁ።

** 8፡65 ሰባት ቀን ፦ በዕብራይስጥ “ዐሥራ አራት ቀን” ሲል፥ አንድ የጥንት ትርጒ “ሰባት ቀን” ይላል።

8፡56 ፦ ዘዳ. 12፥10፤ ኢያሱ 21፥44-45። 9፡2 ፦ 1ነገ. 3፥5፤ 2ዜ.መ. 1፥7። 9፡5 ፦ 1ነገ. 2፥4።

## ምዕራፍ 10

### የንግሥተ ሳባ ጉብኝት በኢየሩሳሌም
(2 ዜ.መ. 9፥1-12)

1 ንግሥተ ሳባ እግዚአብሔር ለሰሎሞን ስለሰ
ጠው እስደናቂ ጥበብ የሚነገረውን ሁሉ
ሰማች፤ ስለዚህ አስቸጋሪ በሆኑ የእንቆቅልሽ
ጥያቄዎች ልትፈትነው ወደ ኢየሩሳሌም
መጣች። 2 ብዙ የክብር አጀቢዎችን በማስከተል
በግመሎች የተጫነ ሽቶ፥ የከበረ ዕንቊና ብዙ
ወርቅ ይዛ መጣች፤ ከሰሎሞንም ጋር በተገናኙ
ጊዜ በልብዋ ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበችለት፤
3 እርሱም ላቀረበችለት ጥያቄ ሁሉ መልስ
ሰጠ፤ ሊተረጉምላት የተሳነውና ከእርሱ የተሰ
ወረ ምንም ዐይነት እንቆቅልሽ አልነበረም።
4 ንግሥተ ሳባ ጥበብ የተሞላበትን የሰሎሞንን
አነጋገር አዳመጠች፤ የሠራውንም ቤተ መንግ
ሥት አየች፤ 5 በሰሎሞን ገበታ ላይ የሚቀርበ
ውን የምግብ ዐይነት፥ የመኳንንቱን መኖሪያ
አካባቢዎች፥ የቤተ መንግሥቱን ሠራተኞች
የሥራ አደረጃጀት፥ የደንብ ልብሳቸውንም ዐይ
ነት፥ በግብዣ ጊዜ የሚያገለግሉትን አሳላፊዎ
ችና በቤተ መቅደስም የሚያቀርባቸውን መሥ
ዋዕቶችን ሁሉ ተመለከተች፤ በዚህም ሁሉ የተ
ሰማት አድናቆት ከጠበቀችው በላይ ነበር።
6 ንጉሥ ሰሎሞንንም እንዲህ አለችው፥ “ስለ
አንተና ስለ ጥበብህ ታላቅነት በአገሬ ሳለሁ የሰ
ማሁት ሁሉ እውነት ነው፤ 7 ነገር ግን እዚህ
ድረስ መጥቼ በዐይኔ እስካየው ድረስ የተነገረ
ኝን ሁሉ ለማመን አልቻልኩም ነበር፤ ታዲያ
በጆሮ የሰማሁት በዐይኔ ያየሁትን እኩሌታ
እንኳ አይሆንም፤ በእርግጥም ጥበብህና ሀብትህ
በአገሬ ሳለሁ ከተነገረኝ በጣም ይበልጣል።
8 በፊትህ ሁልጊዜ በመገኘት ጥበብ የሞላበት
ንግግርህን የሚሰሙ ሰዎችህና ባለሟሎችህ እን
ዴት የታደሉ ናቸው! 9 አምላክህ እግዚአብ
ሔር ይመስገን! እርሱ አንተን መርጦ የእስራ
ኤል ንጉሥ በማድረግ በአንተ መደሰቱን ገልጦ
ልሃል፤ ለእስራኤል ያለውም ፍቅር ዘላለማዊ
ስለሆነ ሕግና ፍትሕ ጸንቶ እንዲኖር ታደርግ
ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ አድርጎሃል።”
10 ንግሥተ ሳባ ያመጣችለትን ስጦታ ሁሉ
ለንጉሥ ሰሎሞን አበረከተችለት፤ ይኸውም ከአ
ራት ሺ ኪሎ የሚበልጥ ወርቅ፥ እጅግ ብዙ
ሽቶና የከበረ ዕንቊ ነበር፤ እርስዋ ለሰሎሞን
ያበረከተችው የሽቶ ብዛት በማንኛውም ጊዜ
ከቀረበለት የሽቶ ገጸ በረከት ሁሉ እጅግ የሚበ
ልጥ ነበር።
(11 ከኦፊር ወርቅ ያመጡለት የኪራም መር
ከቦች ከዚያው ከኦፊር ብዙ የጥድ እንጨትና
የከበረ ዕንቊ አምጥተውለት ነበር። 12 ሰሎሞን
ከዚሁ ከጥድ እንጨት የቤተ መቅደሱንና የቤተ
መንግሥቱን መከታዎች፥ መዘምራን የሚያገለ
ግሉባቸውን በገናዎችና መሰንቆዎች አሠራ፤
ይህም የጥድ እንጨት ወደ እስራኤል አገር
ከመጣው የጥድ እንጨት ሁሉ የሚበልጥ
ነበር፤ ከዚያም በኋላ ይህን የመሰለ የጥድ እን
ጨት ከቶ ታይቶ አያውቅም።)
13 ንጉሥ ሰሎሞን ከተለመደው የልግሥና
ስጦታው ጋር የሳባ ንግሥት የጠየቀችውን ሁሉ
ሰጣት፤ ከዚህ በኋላ ንግሥተ ሳባ ከክብር አጀቢ
ዎችዋ ጋር ወደ አገርዋ ተመልሳ ሄደች።

### የንጉሥ ሰሎሞን ሀብት ብዛት
(2 ዜ.መ. 9፥13-29)

14 ንጉሥ ሰሎሞን በየዓመቱ ሃያ ሦስት ሺ
ኪሎ ያህል የሚመዝን ወርቅ ያገኝ ነበር፤
15 ይህም ሁሉ ነጋዴዎች ከሚከፍሉት ቀረጥ፥
ከንግድ ከሚገኘው ትርፍ፥ እንዲሁም ከዐረብ
ነገሥታትና ከእስራኤል ክፍላተ ሀገር አስተዳዳ
ሪዎች ከሚገባለት ግብር ጋር ተጨማሪ ነበር።
16 ሰሎሞን ሁለት መቶ ታላላቅ ጋሻዎችን
አሠርቶ እያንዳንዱን ጋሻ በሰባት ኪሎ ያህል
ወርቅ አስለበጠው፤ 17 እንዲሁም ሦስት መቶ
ታናናሽ ጋሻዎችን አሠርቶ እያንዳንዱን በሁለት
ኪሎ ያህል ወርቅ አስለበጠው፤ እነዚህንም
ሁሉ “የሊባኖስ ደን” ተብሎ በሚጠራው አዳ
ራሽ ውስጥ አኖራቸው።
18 እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞን ከዝሆን ጥርስ
አንድ ትልቅ ዙፋን አሠርቶ በንጹሕ ወርቅ አስ
ለበጠው፤ 19-20 ዙፋኑም ከታች ወደ ላይ መወ
ጣጫ የሆኑ ስድስት ደረጃዎች ነበሩት፤ በእያን
ዳንዱም ደረጃ ጫፍ በግራና በቀኝ አንዳንድ
የአንበሳ ምስል ሲኖር በድምሩ የተቀረጹት የአ
ንበሳ ምስሎች ዐሥራ ሁለት ነበሩ፤ ከዙፋኑ
በስተ ጀርባ የኮርማ ራስ ምስል ነበር፤ በሁለቱ
የክንድ መደገፊያ ጫፎችም ላይ አንዳንድ የአን
በሳ ምስል ነበር፤ ይህን የመሰለ ዙፋን በሌላ
በየትኛውም አገር መንግሥት ከቶ አልነበረም።
21 ሰሎሞን የሚጠጣባቸው ዋንጫዎች
ሁሉና “የሊባኖስ ደን” ተብሎ በሚጠራው
አዳራሽ ውስጥ የሚገኙት ዕቃዎች በሙሉ ከን
ጹሕ ወርቅ እንጂ ከብር አልተሠሩም፤ ምክንያ
ቱም በሰሎሞን ዘመን ብር ምንም ዋጋ አልነበረ
ውም፤ 22 ሰሎሞን ከኪራም መርከቦች ጋር
በውቅያኖስ ላይ የሚጓዙ ሌሎች መርከቦችም
ነበሩት፤ እነርሱም በየሦስት ዓመት ወርቅን፥
ብርን፥ የዝሆን ጥርስን፥ ጦጣዎችንና ዝንጀሮ
ዎችን ያመጡለት ነበር።
23 ንጉሥ ሰሎሞን ከሌሎች ነገሥታት ሁሉ
የሚበልጥ ሀብታምና ጥበበኛ ነበር፤ 24 በመላው

---

10፥1-10 ፦ ማቴ. 12፥42፤ ሉቃ. 11፥31።

### ኢዮርብዓም ፊቱን ከእግዚአብሔር ወደሌላ መለሰ

25 የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በኮረብታ
ማው በኤፍሬም አገር የምትገኘውን የሴኬምን
ከተማ ምሽግ አድርጎ በቢያ ለጥቂት ጊዜ ቈየ ፤
ከዚያም በመነሣት የፐኑኤልን ከተማ ምሽግ
አድርጎ ሠራ ፤ 26-27 በአሳቡም "ይህ ሁሉ ነገር
እንዲህ ሆኖ ሳለ ፥ የእኔ ሕዝብ ወደ ኢየሩሳ
ሌም በመሄድ በቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር
መሥዋዕት ማቅረባቸው የሚቀጥል ከሆነ ፥ ለይ
ሁዳ ንጉሥ ለሮብዓም ታማኞች በመሆን ወደ
እርሱ ዞረው እኔን ይገድሉኛል ፤ መንግሥቱም
ወደ ዳዊት ቤት ይመለሳል" አለ ።
28 በዚህም ጉዳይ ከመከረበት በኋላ የሁለት
ኮርማዎችን ምስል ከወርቅ አሠርቶ ለሕዝቡ
"ከዚህ በፊት ታደርጉት በነበረው ዐይነት ለመ
ስገድ እስከ ኢየሩሳሌም መሄድ ይርቅባችኋል ፤
የእስራኤል ሕዝብ ሆይ! ከግብጽ ምድር ያወጡ
አችሁ አማልክቶቻችሁ እነሆ እነዚህ ናቸው"
አላቸው ። 29 ከዚህም በኋላ ከወርቅ የተሠሩት
ሁለት የኮርማ ምስሎች አንዱን በቤትኤል ፥
ሁለተኛውንም በዳን አቆመ ፤ 30 ሕዝቡም እስከ
ዳን ድረስ በጣዖቱ ፊት ተሰልፈው ሄዱ ፤ በዚ
ህም ሁኔታ ጣዖትን በማምለክ ኃጢአት ሠሩ ፤
31 እንዲሁም ኢዮርብዓም በኮረብታዎች ላይ
የማምለኪያ ስፍራዎችን አዘጋጅቶ የሌዊ ነገድ
ካልሆኑ ቤተሰቦች መካከል ማንኛውንም ሰው
ካህን አድርጎ ሾመ ።

### በቤትኤል የተጀመረው የጣዖት አምልኮ ተወገዘ

32 ኢዮርብዓም በይሁዳ በሚደረገው የሃይማ
ኖት በዓል ዐይነት ስምንተኛ ወር በገባ በዐሥራ
አምስተኛው ቀን የባዕድ አምልኮ በዓል እንዲደ
ረግ ወሰነ ፤ ከወርቅ ካሠራቸውም ምስሎች በቤ
ትኤል በሚገኘው መሠዊያ ላይ መሥዋዕት አቀ
ረበ ፤ በዚያም በቤትኤል ለማምለኪያ ባሠራ
ቸው ስፍራዎች የሚያገለግሉ ካህናትን መደበ ፤
33 በዓል እንዲሆን እርሱ ራሱ በወሰነው ስምን
ተኛ ወር በገባ በዐሥራ አምስተኛው ቀን ወደ
ቤትኤል ሄደ ፤ በዚያም ለእስራኤል በወሰነላ
ቸው መሠረት በዓል ለማክበር በመሠዊያው ላይ
መሥዋዕት አቀረበ ።

## ምዕራፍ 13

1 ኢዮርብዓም ዕጣን ለማጠን በመሠዊያው
አጠገብ ቆሞ ሳለ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተ
ላከ አንድ ነቢይ እነሆ ከይሁዳ መጥቶ እዚያ
ደረሰ ፤ 2 ነቢዩም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠ
ረት ያንን መሠዊያ በመቃወም እንዲህ ሲል
የትንቢት ቃል ተናገረበት ፥ "መሠዊያ! መሠ
ዊያ ሆይ! እግዚአብሔር ስለ አንተ የሚለው
ቃል ይህ ነው ፥ 'እነሆ ለዳዊት ቤተሰብ ኢዮስ
ያስ ተብሎ የሚጠራ ልጅ ይወለዳል ፤ እርሱም
በኮረብታ ላይ ለተሠራው ለአረማውያን መሠ
ዊያ አገልጋዮች ሆነው ዕጣን የሚያጥኑብህን
ካህናት በአንተው ላይ ያርዳቸዋል ፤ የሰዎችንም
አጥንት በአንተ ላይ ያቃጥላል ።'" 3 ነቢዩም
የሚናገረውን የትንቢት ቃል በመቀጠል "እግዚ
አብሔር ይህን ምልክት ይሰጣል ፤ ይህ መሠዊያ
ተሰባብሮ ይወድቃል ፤ በእርሱ ላይ ያለውም
ዐመድ ይበተናል ፤ ይህንንም የትንቢት ቃል
በእኔ አማካይነት የተናገረው ራሱ እግዚአብሔር
መሆኑን ይህ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ትገነዘባ
ለህ" አለ ።
4 ንጉሥ ኢዮርብዓምም ይህን በሰማ ጊዜ
እጁን እንሥቶ ወደ ነቢዩ በማመልከት ፥
"ያዙት!" የሚል ትእዛዝ ሰጠ ፤ የንጉሡም
ክንድ ወዲያውኑ ድርቅ ብሎ ሽባ ስለሆነ የዘረ
ጋውን እጁን መመለስ አልቻለም ። 5 ነቢዩም
በእግዚአብሔር ስም በተናገረው የትንቢት ቃል
መሠረት በእግዚአብሔር የተሰጠውም ምልክት
ተፈጸመ ፤ መሠዊያው ወዲያውኑ ተሰባብሮ
ወደቀ ፤ ዐመዱም መሬት ላይ ፈሰሰ ። 6 ንጉሡ
ኢዮርብዓም "እባክህ እጄን ያድንልኝ ዘንድ
ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልኝ"
ሲል ነቢዩን ለመነ ።
ነቢዩም ወደ እግዚአብሔር ጸለዮለት የን
ጉሡ እጅ ዳነች ። 7 ከዚህም በኋላ ንጉሡ ነቢ
ዩን "ና ከእኔ ጋር አብረህ ወደ ቤቴ ግባ ፤
እህል ውሃም ቅመስ ፤ ስላደረግህልኝም መል
ካም ነገር ወሮታህን እከፍላለሁ" አለው ።
8 ነቢዩ ግን "የሀብትህን እኩሌታ ብትሰጠኝ
እንኳ ወደቤትህ አልሄድም ፤ ከአንተ ጋር እህል
ውሃም አልቀምስም ። 9 ምክንያቱም ምንም ዐይ
ነት እህል ውሃ እንዳልቀምስና ወደቤቴ ስመለ
ስም በመጣሁበት መንገድ እንኳ እንዳልሄድ
እግዚአብሔር አዝዞኛል" ሲል መለሰለት ።
10 ስለዚህም ያ ነቢይ የመጣበትን መንገድ በመ
ተው በሌላ መንገድ ተመልሶ ሄደ ።

### ሽማግሌው የቤትኤል ነቢይ

11 በዚያን ጊዜ በቤትኤል የሚኖር አንድ
ሽማግሌ ነቢይ ነበር ፤ ወንዶች ልጆቹ ወደ
እርሱ ቀርበው ፥ ከይሁዳ የመጣው ነቢይ በቤት
ኤል ስላደረገውና በንጉሥ ኢዮርብዓምም ላይ
ስለተናገረው ቃል ሁሉ አወሩለት ፤ 12 ሽማግሌ
ውም ነቢይ "ታዲያ ነቢዩ ከዚያ ተነሥቶ በየት
ኛው መንገድ ሄደ" ሲል ጠየቃቸው ፤ እነር
ሱም የሄደበትን መንገድ በማመልከት አሳዩት ፤
13 ከዚህም በኋላ እርሱ "አህያዬን ጫኑልኝ"

---

12፥28 ፦ ዘጸ. 32፥4 ። 12፥32-33 ፦ ዘሌ. 23፥33-34 ። 13፥2 ፦ 2ነገ. 23፥15-16 ።

ሁሉ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ ንጉሥ አሳ ከዚያ የተ
ገኘውን ድንጋይና እንጨት ሁሉ ወስዶ ምጽጳ
ንና በብንያም ግዛት ውስጥ የምትገኘውን የጌባ
ዕን ከተማ ምሽግ አድርጎ ሠራበት።
23 ንጉሥ አሳ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ፥
የጀግንነት ሥራውና የመሸጋቸውም ከተሞች
ጭምር በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ
ተመዝግቦ ይገኛል፤ ንጉሥ አሳ በዕድሜ በሸመ
ገለ ጊዜ ግን ከእግሩ ሕመም የተነሣ ሽባ ሆኖ
ነበር። 24 እርሱም ሞተ፤ በዳዊት ከተማ በሚገ
ኘው በነገሥታት መቃብር ተቀበረ፤ በእርሱም
እግር ተተክቶ ልጁ ኢዮሣፍጥ ነገሠ።

### የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ

25 አሳ በይሁዳ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ የእስራኤል ንጉሥ
ሆኖ ሁለት ዓመት ገዛ፤ 26 ከእርሱም በፊት እን
ደነበረው እንደ አባቱ ኃጢአት በመሥራት የእ
ስራኤልን ሕዝብ ወደ ኃጢአት መራ።
27 የይሳኮር ነገድ የሆነው የአኪያ ልጅ ባዕሻ
በናዳብ ላይ ዐምፆ ገደለው፤ በዚያም ጊዜ ናዳ
ብና ሠራዊቱ በፍልስጥኤም ግዛት የምትገኘ
ውን የጊብቶንን ከተማ በመክበብ ላይ ነበሩ።
28 ይህም የሆነው የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ
በሦስተኛው ዓመት ነው፤ በዚህ ዐይነት ሁኔታ
ባዕሻ በናዳብ እግር ተተክቶ የእስራኤል ንጉሥ
ሆነ። 29 ወዲያውኑም የኢዮርብዓምን ቤተሰብ
አባላት ሁሉ መፍጀት ጀመረ፤ እግዚአብሔር
የሴሎ ተወላጅ በሆነው በአገልጋዩ በነቢዩ
አኪያ አማካይነት በተናገረው ቃል መሠረት
የኢዮርብዓም ቤተሰብ በሙሉ ተገደሉ፤ በሕይ
ወት የተረፈ አንድም አልነበረም። 30 ይህም
የሆነበት ምክንያት ኢዮርብዓም ራሱ በሠራው
ኃጢአትና የእስራኤልም ሕዝብ ኃጢአት እንዲ
ሠሩ በማድረግ የእስራኤል አምላክ የሆነውን
የእግዚአብሔርን ቊጣ ስላነሣሣ ነው።
31 ናዳብ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእስራ
ኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገ
ኛል። 32 የይሁዳ ንጉሥ አሳ እና የእስራኤል
ንጉሥ ባዕሻ በሥልጣን በነበሩበት ዘመን ሁሉ
የማያቋርጥ የእርስበርስ ጦርነት ላይ ነበሩ።

### የእስራኤል ንጉሥ ባዕሻ

33 አሳ በይሁዳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት
የአኪያ ልጅ ባዕሻ በመላው እስራኤል ላይ
ነገሠ፤ መናገሪያውንም በቲርጻ በማድረግ ሃያ
አራት ዓመት ገዛ፤ 34 ከእርሱም በፊት እንደነበ
ረው እንደ ንጉሥ ኢዮርብዓም ባዕሻ ራሱ ኃጢ
አት በመሥራትና የእስራኤልንም ሕዝብ ወደ
ኃጢአት በመምራት እግዚአብሔርን አሳዘነ።

## ምዕራፍ 16

1 የሐናኒ ልጅ በሆነው በነቢዩ ዬሁ አማካይ
ነት እግዚአብሔር ስለ ባዕሻ የተናገረው ቃል
ይህ ነው፥ 2 "አንተ ኢምንት ነበርህ፤ እኔ ግን
ከትቢያ አንሥቼ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደ
ረግሁህ፤ ታዲያ አንተ እንደ ኢዮርብዓም ኃጢ
አት ሠራህ፤ ሕዝቤንም ወደ ኃጢአት መራህ፤
የኃጢአታቸውም ብዛት የእኔን ቊጣ አነሣሣቶ
አል፤ 3 ስለዚህም ኢዮርብዓምን እንዳስወገድሁ
አንተንና ቤተሰብህንም አስወግዳለሁ፤ 4 በከተማ
ይቱ ውስጥ የሚሞተውን ማንኛውንም የቤተሰ
ብህን አባል ውሾች ይበሉታል፤ በየገጠሩም
ሜዳ ላይ የሚሞተውን አሞራዎች ይበሉ
ታል።"
5 ባዕሻ ያደረገው ሌላው ነገርና የጀግንነት
ሥራዎቹም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ
መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል፤ 6 ባዕሻ ሞተ፤
በቲርጻም ተቀበረ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ
ልጁ ኤላ ነገሠ።
7 እግዚአብሔር በነቢዩ ዬሁ አማካይነት በባ
ዕሻና በቤተሰቡ ላይ ያን የትንቢት ቃል የተናገ
ረበት ምክንያት፥ ባዕሻ በፈጸመው ኃጢአት
እግዚአብሔርን ስላሳዘነ ነበር፤ ባዕሻ እግዚአብ
ሔርን ያስቈጣውም ከእርሱ ፊት የነበረው
ንጉሥ ባደረገው ዐይነት ስለ ሠራው ክፉ ነገር
ብቻ ሳይሆን የኢዮርብዓምንም ቤተሰብ ሁሉ
በመግደሉ ጭምር ነው።

### የእስራኤል ንጉሥ ኤላ

8 አሳ በይሁዳ በነገሠ በሃያ ስድስተኛው
ዓመት የባዕሻ ልጅ ኤላ የእስራኤል ንጉሥ
ሆነ፤ መናገሪያውንም በቲርጻ አድርጎ ሁለት
ዓመት ገዛ። 9 የሠረገላዎቹ እኩሌታ ኀላፊ የሆነ
ዚምሪ ተብሎ የሚጠራ ከጦር መኰንኖቹ አንዱ
በንጉሡ ላይ ዐመፀ፤ አንድ ቀን ኤላ በቲርጻ
ከተማ የቤተ መንግሥቱ ኀላፊ በሆነው አርጻ
ተብሎ በሚጠራው ባለሟሉ ቤት ብዙ መጠጥ
ጠጥቶ ሰክሮ ነበር፤ 10 በዚህን ጊዜ ዚምሪ ወደ
ዚያ ቤት ሰተት ብሎ ገብቶ ኤላን ገደለው፤
እርሱም በኤላ እግር ተተክቶ ነገሠ፤ ይህም የሆ
ነው የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው
ዓመት ነበር።
11 ዚምሪ እንደነገሠ ወዲያውኑ የባዕሻ ቤተ
ሰብ አባላት የሆኑትን በሙሉ ገደለ፤ የባዕሻ
ዘመድና ወዳጅ የሆነውን ወንድ ሁሉ በሞት
ቀጣ። 12 በዚህም ዐይነት ሁኔታ እግዚአብሔር
በነቢዩ ዬሁ አማካይነት በባዕሻ ላይ ባናገረው
ትንቢት መሠረት ዚምሪ የባዕሻን ቤተሰብ
በሙሉ ፈጀ። 13 ይህም የሆነበት ምክንያት
ባዕሻና ልጁ ኤላ ጣዖት በማምለካቸውና

15፥29 ፡- 1ነገ. 14፥10።

ሂድ ፤ እዚያም ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በሚ
ገኘው ከሪት ተብሎ በሚጠራው ወንዝ አጠገብ
ተሸሸግ ፤ 4 የምትጠጣውንም ውሃ ከዚያው
ወንዝ ታገኛለህ ፤ ቁራዎችም ምግብ እንዲያመ
ጡልህ አዝዣለሁ ።”
5 ኤልያስም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት
ሄዶ በከሪት ወንዝ አጠገብ ተቀመጠ ፤ 6 ከወን
ዙም ውሃ ጠጣ ፤ ቁራዎችም ዘወትር ጠዋትና
ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር ፤ 7 ዝናም
ጠፍቶ ድርቅ ከመሆኑ የተነሣ ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ያ ወንዝ ደረቀ ።

### ኤልያስና በስራፕታ ትኖር የነበረች መበለት

8 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ኤልያስን እን
ዲህ አለው ፦ 9 “እንግዲህ አሁን ከዚህ ተነሥ
ተህ ሄደህ በሲዶና አጠገብ በምትገኘው
በስራፕታ ከተማ ተቀመጥ ፤ እነሆ በዚያ የምት
ኖር አንዲት መበለት እንድትመግብህ አዝዣ
ለሁ” አለው ። 10 ስለዚህ ኤልያስ ወደ ስራፕታ
ሄደ ፤ ወደ ከተማይቱም ቅጽር በር በደረሰ ጊዜ
አንዲት መበለት እንጨት ስትለቅም አይቶ
“እባክሽ የምጠጣው ውሃ አምጪልኝ” አላት ።
11 ውሃም ልታመጣለት በመሄድ ላይ ሳለች ወዲ
ያውኑ ጠርቶ “እባክሽ በተጨማሪ ትንሽ እን
ጀራ አምጪልኝ” አላት ።
12 እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰችለት ፦
“ምንም እንጀራ እንደሌለኝ በአምላክህ በሕ
ያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ ፤ በዱቄት
ዕቃዬ ውስጥ ካለችው ከአንድ እፍኝ ዱቄትና
በማሰሮዬ ውስጥ ካለችው ከጥቂት የወይራ
ዘይት በቀር ምንም የለኝም ፤ ወደዚህ የመጣ
ሁት ትንሽ እንጨት ለቃቅሜ ወደ ቤቴ በመመ
ለስ ይህችኑ ያለችኝን ትንሽ ዱቄት ለልጄና
ለእኔ ለመጋገር ነው ፤ ይህችም የመጨረሻ ምግ
ባችን ናት ፤ ከዚያም በኋላ በረሀብ ከመሞት
አንተርፍም ።”
13 ኤልያስም እንዲህ አላት ፦ “አይዞሽ አት
ጨነቂ ፤ ሄደሽ ምግብሽን አዘጋጂ ፤ አስቀድመሽ
ግን ከዚያችው ካለችሽ ዱቄት ለእኔ ትንሽ
እንጐቻ ጋግረሽ አምጪልኝ ፤ የቀረውንም ለራ
ስሽና ለልጅሽ ጋግሪው ፤ 14 ምክንያቱም የእስራ
ኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ‘እኔ እግዚአ
ብሔር ዝናምን እስከማወርድ ድረስ ዱቄቱ ከማ
ኖሪያው ዕቃ ፥ ዘይቱም ከማሰሮው ከቶ አያል
ቅም’ ሲል ተናግሮአል ።”
15 መበለቲቱም ሄዳ ኤልያስ እንደነገራት
አደረገች ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ እርስዋ ፥
ቤተሰብዋና ኤልያስም ለብዙ ቀን የሚሆን በቂ
ምግብ አገኙ ። 16 እግዚአብሔር በኤልያስ አማ
ካይነት በሰጠው ተስፋ መሠረት ዱቄቱ ከማኖሪ
ያው ዕቃ ፥ ዘይቱም ከማሰሮው አላለቀም ።
17 ከጥቂት ጊዜም በኋላ የዚያች መበለት
ልጅ ታመመ ፤ ሕመሙም እየባሰበት ስለሄደ
በመጨረሻ ሞተ ፤ 18 መበለቲቱም ኤልያስን
“የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! ስለምን ይህን አደ
ረግህብኝ? ወደዚህ የመጣኸው ኃጢአቴን አስ
ታውሰህ ልጄ እንዲሞትብኝ ለማድረግ
ነውን?” ስትል ጠየቀችው ።
19 ኤልያስም “ልጅሽን ወደ እኔ አም
ጪው” አላት ። ልጁንም ከእቅፍዋ ወስዶ
እርሱ ወደሚኖርበት ሰገነት አውጥቶ በአልጋው
ላይ አጋደመው ፤ 20 ከዚህ በኋላ ኤልያስ ድም
ፁን ከፍ በማድረግ “እግዚአብሔር አምላኬ
ሆይ! ስለምን በዚህች መበለት ላይ ይህን የመ
ስለ አሠቃቂ ነገር አደረግህ? እርስዋ እኔን በማ
ስተናገድ ታላቅ ቸርነት አድርጋልኛለች ፤
ታዲያ አንተ ስለምን ልጅዋ እንዲሞት አደረ
ግህ?” ሲል ጸለየ ። 21 ከዚህ በኋላ ኤልያስ
በልጁ ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርሮ “እግዚአብሔር
አምላኬ ሆይ! እባክህ ይህን ልጅ ከሞት አስነ
ሣው!” ሲል ጸለየ ። 22 እግዚአብሔርም የኤል
ያስን ጸሎት ሰማ ፤ የልጁም እስትንፋስ እንደ
ገና ተመልሶለት ዳነ ።
23 ኤልያስ ልጁን ከሰገነት ወደ ምድር ቤት
አውርዶ ለእናቱ በመስጠት “ተመልከቺ! እነሆ
ልጅሽ ከሞት ወደ ሕይወት ተመልሶአል!”
አላት ።
24 እርስዋም “እነሆ አንተ የእግዚአብሔር
ሰው መሆንህንና እግዚአብሔርም በአንተ አማካ
ይነት መናገሩን አሁን አረጋገጥሁ” ስትል መለ
ሰችለት ።

## ምዕራፍ 18

### ኤልያስና ሐሰተኞቹ የባዓል ነቢያት

1 የድርቁ ዘመን ከተጀመረ ከሦስተኛው
ዓመት በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆየት ብሎ እግዚአብ
ሔር ኤልያስን “ሄደህ ራስህን ለንጉሥ አክአብ
ግለጥለት ፤ እኔም በምድር ላይ ዝናምን አዘንማ
ለሁ” አለው ፤ 2 ኤልያስም በታዘዘው መሠረት
ወደ አክአብ ሄደ ፤ በዚህ ጊዜ በሰማርያ ረሀብ
እጅግ ጸንቶ ነበር ። 3 ስለዚህም ንጉሥ አክአብ
የቤተ መንግሥቱም ኀላፊ የሆነውን ዖባድያን
ጠራ ፤ ዖባድያ እግዚአብሔርን የሚፈራ መንፈ
ሳዊ ሰው ነው ፤ 4 ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን
ነቢያት ታስገድል በነበረችበትም ጊዜ ዖባድያ
አንድ መቶ የሚሆኑትን የእግዚአብሔርን ነቢ
ያት ከሁለት ከፍሎ ኀምሳ ፥ ኀምሳውን በዋሻ
ዎች ከሸሸጋቸው በኋላ እህልና ውሃ በማቅረብ
ይመግባቸው ነበር ። 5 ስለዚህም አክአብ ዖባድ
ያን “ፈረሶችንና በቅሎዎችን ከሞት የምናድን
በት በቂ ሣር እናገኝ እንደሆን በምድሪቱ ወደ
ሚገኘው ምንጭና ወንዝ እስቲ ሂድና እይ ፤

17፥9 ፡- ሉቃ. 4፥25-26 ። 17፥21 ፡- 2ነገ. 4፥34-35 ።

30ከዚህ በኋላ ኤልያስ ሕዝቡን “ወደ እኔ
ቅረቡ” አላቸው፤ ሁሉም በዙሪያው ተሰበ
ሰቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር
መሠዊያ በማደስ ሠራው። 31እግዚአብሔር
ከዚያ በፊት “እስራኤል” ብሎ ከሰየመው ከያዕ
ቆብ በተወለዱት በዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ስም
ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ወሰደ፤ 32እነዚህንም
ድንጋዮች ረብርቦ እግዚአብሔር የሚመለክባ
ትን መሠዊያ እንደገና ሠራ፤ በዙሪያውም
ዐሥራ አራት ሊትር ውሃ የሚይዝ ጕድጓድ
ማሰ፤ 33እንጨቱንም በመሠዊያው ላይ በመረ
ብረብ ኮርማውን በብልት በብልቱ ቈራርጦ በእ
ንጨቱ ላይካኖረ በኋላ፥ 34“በአራት ጋን ውሃ
ሞልታችሁ በመሥዋዕቱና በእንጨቱ ላይ አፍስ
ሱት” አላቸው፤ እነርሱም እንዲሁ አደረጉ፤
“አሁንም ጨምሩበት” አላቸው፤ እነርሱም
እንዲሁ አደረጉ፤ እርሱም “አሁንም እንደገና
አንድ ጊዜ ጨምሩ” አላቸው፤ እነርሱም እን
ዲሁ አደረጉ፤ 35ውሃውም በመሠዊያው ዙሪያ
ፈሰሰ፤ ጕድጓዱንም ሞላው።

36ከቀትር በኋላ የሠርክ መሥዋዕት በሚቀር
ብበት ሰዓት ነቢዩ ኤልያስ ወደ መሠዊያው
ቀርቦ እንዲህ ሲል ጸለየ፥ “የአብርሃም፥ የይስ
ሐቅና የያዕቆብ አምላክ የሆንህ እግዚአብሔር
ሆይ! አንተ የእስራኤል አምላክ መሆንክን፥
እኔም የአንተ አገልጋይ መሆኔን፥ እኔም ይህን
ሁሉ ያደረግሁት በቃልህ መሠረት መሆኑን
አንተ ራስህ ግለጥ፤ 37አምላኬ ሆይ! ይህ
ሕዝብ አንተ እውነተኛ አምላክ መሆንክንና
ወደ አንተም ያቀረብከው አንተ ራስህ መሆን
ክን እንዲያውቅ እባክህ መልስ ስጠኝ፤ አምላክ
ሆይ! ስማኝ!”

38ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እሳትን ላከ፤
ያም እሳት መሥዋዕቱን፥ እንጨቱንና ድንጋዩን
አቃጠለ፤ ምድሩንም ለበለበ፤ በጕድጓዱ የነበረ
ውንም ውሃ አደረቀ፤ 39ሕዝቡም ይህን ባዩ
ጊዜ በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው በመ
ደነቅ “እግዚአብሔር አምላክ ነው! እውነተኛ
አምላክ እርሱ ብቻ ነው!” አሉ።

40ኤልያስም “የባዓልን ነቢያት ያዙ! አን
ድም ሰው እንዳያመልጥ!” ሲል አዘዘ። ሕዝ
ቡም በሙሉ ያዙአቸው፤ ኤልያስም ወደ
ቂሾን ወንዝ እየመራ ወስዶ በዚያ ሁሉንም ገደ
ላቸው።

### የድርቁ ዘመን አበቃ

41ከዚህ በኋላ ኤልያስ ንጉሥ አክአብን
“እንግዲህ ሄደህ እህልና ውሃ ቅመስ፤ ምክንያ
ቱም እኔ አሁን የከባድ ዝናም ነጐድጓድ ድምፅ
መቃረቡን እየሰማሁ ነው” አለው፤ 42አክአብ
እህልና ውሃ ለመቅመስ ሲሄድ፥ ኤልያስ ወደ
ቀርሜሎስ ተራራ ወጣ፤ እዚያም በሁለቱ ጕል
በቶቹ መካከል ራሱን ወደ መሬት ደፍቶ፥
43አገልጋዩን፥ “ሂድና ወደ ባሕሩ አቅጣጫ
ተመልከት” አለው።

አገልጋዩም ሄዶ ሲመለስ “ምንም ነገር አይ
ታየኝም” አለው፤ አገልጋዩ እየተመላለሰ ያይ
ዘንድ ኤልያስ ሰባት ጊዜ አዘዘው፤ 44በሰባተኛ
ውም ጊዜ አገልጋዩ ተመልሶ “ከአንድ ሰው
መዳፍ የማትበልጥ ትንሽ ደመና ከባሕር ስት
ወጣ አየሁ” አለው።

ኤልያስም “ወደ ንጉሥ አክአብ ሂድና
‘ዝናሙ ሳያቋርጥህ በፍጥነት ወደ ሠረገላህ ገብ
ተህ ወደ ቤትህ ተመልሰህ ሂድ’ ብለህ ንገ
ረው” ሲል አዘዘው።

45ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሰማዩ በጥቁር
ደመና ተሸፈነ፤ ነፋሱም ይነፍስ፥ ብርቱ ዝና
ምም ይዘንም ጀመረ፤ ንጉሥ አክአብም በሠረገ
ላው ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ፤ 46የእግ
ዚአብሔርም ኀይል በኤልያስ ላይ ወረደ፤ ኤል
ያስም ልብሱን በወገቡ ዙሪያ ጠበቅ አድርጎ
በመታጠቅ እስከ ኢይዝራኤል መግቢያ በር
ድረስ በአክአብ ፊት ቀድሞ ይሮጥ ነበር።

## ምዕራፍ 19

### ኤልያስ በሲና ተራራ

1ኤልያስ ያደረገውን ሁሉና የባዓልንም ነቢ
ያት በሙሉ በሞት እንዴት እንደቀጣ ንጉሥ
አክአብ ለሚስቱ ለኤልዛቤል ነገራት፤ 2ስለዚህ
እርስዋ “በእነዚያ ነቢያት ላይ ያደረግኸውን
እኔም ነገ ልክ በአሁኑ ሰዓት በአንተ ላይ ሳላደ
ርግብህ ብቀር አማልክት በሞት ይቅሠፉኝ”
ስትል ወደ ኤልያስ የዛቻ መልእክት ላከች።
3ኤልያስም ስለፈራ ሕይወቱን ለማትረፍ ከአገ
ልጋዩ ጋር በይሁዳ ወደምትገኘው ወደ ቤርሳ
ቤህ ከተማ ሄደ።

አገልጋዩንም በዚያ ትቶት፥ 4ኤልያስ
አንድ ቀን ሙሉ በበረሓ ተጓዘ፤ ከዚህ በኋላ
ጕዞውን ቆም አድርጎ፥ በአንድ የክትክታ ዛፍ
ጥላ ሥር ተቀመጠ፤ ሞቱንም በመመኘት
“እግዚአብሔር ሆይ! አሁንስ ይብቃኝ፤ ከቀ
ድሞ አባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ!”
ሲል ጸለየ።

5ከዚህ በኋላ በዛፉ ሥር ጋደም እንዳለ እን
ቅልፍ ወሰደው፤ በድንገትም አንድ መልአክ
መጥቶ በመዳሰስ ቀሰቀሰውና “ተነሥ ብላ!”
አለው፤ 6ኤልያስም ተነሥቶ ዙሪያውን በተመ
ለከተ ጊዜ በድንጋይ ሙቀት የበሰለ የዳቦ ሙል
ሙልና አንድ ገንቦ ውሃ በራስጌው ተቀምጦ
አየ፤ ከበላና ከጠጣም በኋላ ተመልሶ ተኛ፤
7የእግዚአብሔርም መልአክ ተመልሶ መጥቶ

18፥31 ፦ ዘፍ. 32፥28፤ 35፥10። 18፥42-24 ፦ ያዕ. 5፥18። 19፥4 ፦ ዮናስ 4፥3።

28 እግዚአብሔርም ነቢዩን ኤልያስን እንዲህ
አለው ፥ 29 “አክአብ በእኔ ፊት ራሱን እንዴት
እንዳዋረደ ተመልክተሃልን? ይህንን ስላደረገ
በሕይወቱ ሳለ መቅሠፍትን አላመጣበትም፤
የተባለውን መቅሠፍት በአክዓብ ቤተሰብ ላይ
የማመጣው በልጁ የሕይወት ዘመን ይሆናል ።”

## ምዕራፍ 22

### ነቢዩ ሚካያ ንጉሥ አክአብን አስጠነቀቀ
(2 ዜ.መ. 18፥2-27)

1 ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ
በእስራኤልና በሶርያ መካከል ጦርነት ተወግዶ
ሰላም ሰፍኖ ነበር፤ 2 ይሁን እንጂ በሦስተኛው
ዓመት የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ የእስራኤልን
ንጉሥ አክአብን ለመጐብኘት በሄደ ጊዜ ፥
3 አክአብ ባለሟሎቹ የሆኑትን ባለሥልጣኖች
“በገለዓድ የምትገኘውን ራሞትን ከሶርያ
ንጉሥ ለማስመለስ ምንም ዐይነት እርምጃ ያል
ወሰድነው ስለምንድን ነው? ራሞት እኮ የእኛ
ይዞታ ናት!” አላቸው፤ 4 ኢዮሣፍጥንም “በራ
ሞት ላይ አደጋ ለመጣል ከእኔ ጋር ለመዝመት
ትፈቅዳለህን?” ሲል ጠየቀው ።
ኢዮሣፍጥም “አንተ ከተዘጋጀህ እኔና ሠራ
ዊቴ ፈረሰኞቼም ጭምር ዝግጁዎች ነን፤
5 ነገር ግን መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ
እንጠይቅ” ሲል መለሰለት ።
6 ስለዚህ አክአብ አራት መቶ የሚሆኑትን
ነቢያቱን ጠርቶ “ወደ ራሞት ሄጄ አደጋ ልጣ
ልባት ወይስ ልተው?” ሲል ጠየቃቸው ።
እነርሱም “ሂደህ አደጋ ጣልባት፤ ጌታም
ድልን ያቀዳጅሃል” ሲሉ መለሱለት ።
7 ኢዮሣፍጥ ግን “የእግዚአብሔርን ፈቃድ
የምንጠይቅበት ሌላስ ነቢይ የለምን?” ሲል
ጠየቀ ።
8 አክአብም “የይምላ ልጅ የሆነ ሚካያ የተ
ባለ ሌላ ነቢይም አለ፤ ነገር ግን እኔ እርሱን
አልወድደውም፤ ምክንያቱም እርሱ ምን
ጊዜም ቢሆን ስለእኔ ክፉ እንጂ መልካም የትን
ቢት ቃል አይናገርም” ሲል መለሰለት ።
ኢዮሣፍጥም “ይህን ማለት አይገባህም”
አለው ።
9 ከዚህ በኋላ አክአብ ከቤተ መንግሥቱ
ባለሟሎች አንዱን ጠርቶ “ሚካያን ፈልገህ
በማግኘት በፍጥነት እንዲመጣ አድርግ” ሲል
አዘዘው ።
10 በዚህም ጊዜ ሁለቱ ነገሥታት ልብሰ መን
ግሥታቸውን ለብሰው በሰማርያ የቅጽር በር
አጠገብ በሚገኘው አውድማ በየዙፋናቸው ላይ
ተቀምጠው ነበር፤ ነቢያቱም ሁሉ በነገሥታቱ
ፊት ቀርበው ትንቢት ይናገሩ ነበር፤ 11 ከእነር
ሱም አንዱ ጼድቅያ ተብሎ የሚጠራው የከና
ዕና ልጅ ከብረት የተሠሩ ቀንዶችን ይዞ አክአ
ብን “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥ ‘ከብረት
በተሠሩ በእነዚህ ቀንዶች ሶርያውያንን ወግተህ
ፍጹም የሆነ ድልን ትቀዳጃለህ’” አለው ።
12 ሌሎቹም ነቢያት ይህንኑ ቃል በመደገፍ
“በራሞት ላይ ዝመት፤ ታሸንፋለህ፤ እግዚአብ
ሔርም ድልን ይሰጥሃል” አሉት ።
13 ሚካያን ለመጥራት ሄዶ የነበረው መልእ
ክተኛ በዚሁ ጊዜ ሚካያን “ሌሎቹ ነቢያት
በሙሉ ንጉሥ አክአብ ድል የሚያደርግ መሆ
ኑን የሚያረጋግጥ የትንቢት ቃል ተናግረዋል፤
ስለዚህም አንተም እንደእነርሱ ብታደርግ ይሻ
ልሃል” አለው ።
14 ሚካያ ግን “እግዚአብሔር የሚገልጥል
ኝን ቃል ብቻ እንደምናገር በሕያው እግዚአብ
ሔር ስም እምላለሁ!” ሲል መለሰለት ።
15 ሚካያም ወደ ንጉሥ አክአብ ፊት በቀረበ
ጊዜ ንጉሡ “ሚካያ ሆይ! ንጉሥ ኢዮሣፍጥና
እኔ ወደ ራሞት ሄደን አደጋ እንጣልባት ወይስ
እንተው?” ሲል ጠየቀው ።
ሚካያም “ዘምተህ አደጋ ጣልባት፤ በእርግ
ጥም ታሸንፋለህ፤ እግዚአብሔርም ድልን ያቀ
ዳጅሃል” ሲል መለሰለት ።
16 አክአብ ግን “አንተ በእግዚአብሔር ስም
የትንቢትን ቃል ስትነግረኝ እውነቱን ግለጥ!
ይህንንስ ስንት ጊዜ እነግርሃለሁ?” አለው ።
17 ሚካያም “መላው የእስራኤል ሠራዊት
ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች በኰረብታዎች ላይ
ተበታትነው አያለሁ፤ እግዚአብሔርም ‘እነዚህ
ሰዎች መሪ የላቸውም፤ ስለዚህ ወደየቤታቸው
በሰላም ይመለሱ ብሎአል’ ሲል መለሰለት ።”
18 አክአብም ኢዮሣፍጥን “እርሱ ዘወትር
ስለእኔ ክፉ እንጂ መልካም የትንቢት ቃል አይ
ናገርም ብዬህ አልነበረምን?” አለው ።
19 ሚካያም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ
አለ ፥ “እንግዲህ እግዚአብሔር የሚለውን ስማ!
እግዚአብሔር በሰማይ ባለው ዙፋኑ ላይ ተቀ
ምጦ ፥ መላእክቱም ሁሉ በቀኝና በግራው
ቆመው አየሁ፤ 20 እግዚአብሔርም ‘አክአብ
ወደ ራሞት ሄዶ በዚያ እንዲገደል ሊያሳስተው
የሚችል ማነው?’ አለ፤ ከመላእክቱም መካከል
አንዱ አንድ ነገር ፥ ሌላው ሌላ ነገር በመግለጥ
የተለያየ አሳብ ያቀርቡ ነበር፤ 21 በመጨረሻ
ግን አንድ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር ፊት
ቀርቦ ‘እኔ ላሳስተው እችላለሁ’ አለ፤ 22 እግዚ
አብሔርም ‘እንዴት አድርገህ ልታሳስተው
ትችላለህ?’ አለው ። መንፈሱም ‘ሄጄ የአክአብ
ነቢያት ሁሉ ሐሰት እንዲናገሩ አደርጋለሁ’
ሲል መለሰለት፤ እግዚአብሔርም ‘እንግዲያውስ
ሄደህ አሳስተው፤ ይከናወንልሃል’ አለው ።’”

22፥17 ፦ ዘኍ. 27፥17፤ ማቴ. 9፥36፤ ማር. 6፥34 ። 22፥19 ፦ ኢሳ. 6፥1፤ ኢዮብ 1፥6 ።

ኤልሳዕም “አዎ ዐውቃለሁ ፤ ነገር ግን ዝም
በሉ” ሲል መለሰላቸው ።
6 ከዚህም በኋላ ኤልያስ ኤልሳዕን “እነሆ
አንተ በዚህ ቆይ ፤ እኔ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እን
ድሄድ እግዚአብሔር አዝዞኛል” አለው ።
ኤልሳዕ ግን “እኔ በሕያው እግዚአብሔር
ስም እምልልሃለሁ ፤ ከቶ ከአንተ አልለይም”
ሲል መለሰለት ፤ ስለዚህም አብረው ጕዞአቸውን
ቀጠሉ ። 7 ከነቢያቱም ኀምሳው ተከትለዋቸው
ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ ፤ ኤልያስና ኤልሳዕም በዮር
ዳኖስ ወንዝ አጠገብ ቆሙ ፤ ኀምሳውም ነቢ
ያት ደግሞ ጥቂት ራቅ ብለው ቆመው ነበር ፤
8 ከዚህ በኋላ ኤልያስ ካባውን አውልቆ በመጠ
ቅለል ውሃውን መታው ፤ ውሃውም ከሁለት
ተከፍሎላቸው ኤልያስና ኤልሳዕ በደረቅ ምድር
ተሻገሩ ፤ 9 በዚያም ኤልያስ ኤልሳዕን “እኔ ከአ
ንተ ከመወሰዱ በፊት ምን እንዳደርግልህ እንደ
ምትፈልግ ንገረኝ” አለው ።
ኤልሳዕም “የአንተ ተተኪ እንድሆን የሚያ
ስችል መንፈስ በእጥፍ[2*] ስጠኝ” ሲል መለሰ
ለት ።
10 ኤልያስም “ያቀረብከው ጥያቄ ከባድ
ነው ፤ ነገር ግን እኔ ከአንተ ተለይቼ ወደ ሰማይ
ስወሰድ ብታየኝ ይህን የጠየቅኸውን ስጦታ
መቀበል ትችላለህ ፤ ባታየኝ ግን ልታገኘው
አትችልም” ሲል መለሰለት ።
11 እየተነጋገሩ እርምጃቸውን ቀጠሉ ፤ ከዚ
ያም በኋላ የእሳት ፈረሶች የሚስቡአቸው የእ
ሳት ሠረገላዎች ድንገት በመካከላቸው ገብተው
ሁለቱን ለዩአቸው ፤ ኤልያስም በሀውሎ ነፋስ
ወደ ሰማይ ተወሰደ ። 12 ኤልሳዕም ይህን ሁሉ
እያየ “አባቴ ሆይ! አባቴ ሆይ! የእስራኤል
መታመኛ የሆንህ ኃያል ሠራዊት! ተለይተህ ሄድ
ህን?” እያለ ወደ ኤልያስ ጮኸ ፤ ከዚያም
በኋላ ኤልያስን ዳግመኛ አላየውም ።
ኤልሳዕም ከሐዘኑ ብዛት የተነሣ ልብሱን
ቀደደ ፤ 13 ከዚህም በኋላ ከኤልያስ የወደቀውን
ካባ ከመሬት አንሥቶ ፤ ከዚያም ሄዶ በዮርዳኖስ
ወንዝ ዳርቻ ቆመ ። 14 ውሃውንም በኤልያስ ካባ
መትቶ “የኤልያስ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር
ወዴት ነው?” አለ ፤ ከዚያም በኋላ እንደገና
በመታው ጊዜ ውሃው ከሁለት ተከፍሎለት ወደ
ማዶ ተሻገረ ፤ 15 ከኢያሪኮ የመጡት ኀምሳው
ነቢያት እርሱን ባዩት ጊዜ “በኤልያስ ላይ
አድሮ የነበረው የመንፈስ ኀይል በኤልሳዕ ላይ
አርፏል!” አሉ ፤ ወደ እርሱም በመቅረብ ጐን
በስ ብለው እጅ ነሡትና እንዲህ አሉ ፤
16 “እነሆ በዚህ ጠንካሮች የሆንን ኀምሳ ሰዎች
አለን ፤ እንሂድና ጌታህን እንፈልገው ፤ ምናል
ባት የእግዚአብሔር መንፈስ አንሥቶ ወስዶ በአ
ንድ ተራራ ላይ ወይም ሸለቆ ውስጥ አሳርፎት
ይሆናል ።”
ኤልሳዕም “መሄድ አይገባችሁም” ሲል
መለሰ ።
17 እነርሱ ግን በአሳባቸው ጸንተው እንዲ
ሄዱ እስኪፈቅድላቸው ድረስ ደጋግመው ጠየ
ቁት ፤ ኀምሳውም ሰዎች ሄደው በደጋውም በቆ
ላውም ሦስት ቀን ሙሉ ኤልያስን ፈለጉት ፤
ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም ፤ 18 ከዚያም
በኋላ በኢያሪኮ ሆኖ ወደሚጠብቃቸው ወደ
ኤልሳዕ ተመለሱ ፤ ኤልሳዕም “እኔ ቀድሞውንስ
አትሂዱ ብያችሁ አልነበረምን?” አላቸው ።

### ኤልሳዕ ያደረጋቸው ተአምራት

19 ጥቂት ሰዎች ከኢያሪኮ ወደ ኤልሳዕ መጥ
ተው “ጌታችን አንተ እንደምታውቀው ይህች
ምድር መልካም ናት ፤ ውሃው ግን መጥፎ በመ
ሆኑ የአገሩ እርጉዞች እንዲጨነግፉ ያደርጋል”
አሉት ።
20 ኤልሳዕም “በአዲስ ሸክላ ድስት ውስጥ
ጨው ጨምራችሁ አምጡልኝ” ብሎ አዘዘ ።
እነርሱም እንዳዘዛቸው አድርገው አመጡለት ።
21 እርሱም ወደ ምንጩ ሄዶ ጨውን በውሃው
ውስጥ በመጨመር “እግዚአብሔር የሚለው
ይህ ነው ፤ ‘እኔ ይህን ውሃ በመፈወስ ንጹሕ
እንዲሆን አደርጋለሁ ፤ ከዚህም በኋላ ዳግመኛ
የሞትና የመጨንገፍ ምክንያት አይሆንም’ ”
ሲል ተናገረ ፤ 22 ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ኤልሳዕ
በተናገረው መሠረት ውሃው ንጹሕ ሆነ ።
23 ኤልሳዕም ወደ ቤትኤል ለመሄድ ከኢያ
ሪኮ ተነሣ ፤ በመንገድ ላይ ከከተማይቱ በርከት
ያሉ ልጆች ወጥተው ድምፃቸውን ከፍ በማድ
ረግ “አንተ ራሰ መላጣ ከዚህ ውጣ!” እያሉ
ጮኹበት ።
24 ኤልሳዕም መለስ ብሎ ዞሪያቸውን በመቃ
ኘት በአትኵረት ተመለከታቸውና በእግዚአብ
ሔር ስም ረገማቸው ፤ በዚህም ጊዜ ሁለት እን
ስት ድቦች ከጫካ ወጥተው ከእነዚያ ልጆች
መካከል አርባ ሁለቱን ሰባብረው ገደሉአቸው ።
25 ኤልሳዕም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣ ፤
ከዚያም ብሎ ግን ወደ ሰማርያ ተመለሰ ።

## ምዕራፍ 3

### በእስራኤልና በሞአብ መካከል የተደረገ ጦርነት

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ
ስምንተኛው ዓመት የአክአብ ልጅ ኢዮራም
በእስራኤል ላይ ነገሠ ፤ መኖሪያውንም በሰማርያ
አድርጎ ዐሥራ ሁለት ዓመት ገዛ ፤ 2 እርሱም
ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ ፤

[2*] 2፥9 እጥፍ ፦ “ለበኵር ልጅ እንደሚሰጥ እጥፍ ድርሻ” ማለት ነው ።
2፥9 ፦ ዘዳ. 21፥17 ። 2፥12 ፦ 2ነገ. 13፥14 ።

ምክንያቱም ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ዘንድ መሄድ
ይገባኛል፤ በተቻለም መጠን ፈጥኜ እመለሳ
ለሁ" አለችው።
23 ባልዋ ግን "ዛሬ ለምን ትሄጃለሽ? ለን
በት ወይም የጨረቃ በዓል የሚከበርበት ጊዜ
አይደለምን?" አላት።
እርስዋም "ግድ የለም፤ እንዳልኩህ አድ
ርግ" አለችው፤ 24 እርስዋም አህያው እንዲጫን
ሳት ካደረገች በኋላ አገልጋዩን "በሚቻል
መጠን አህያው እንዲፈጥን አድርግ፤ እኔም
ካልነገርሁህ በቀር ቀስ ብሎ እንዲሄድ ፋታ
አትስጠው" ስትል አዘዘችው። 25 እርስዋም
ከዚያ ተነሥታ ኤልሳዕ ወደነበረበት ወደ ቀርሜ
ሎስ ተራራ ወጣች።
ኤልሳዕም ገና በሩቅ ሳለች ወደ እርሱ ስት
መጣ አይቶ አገልጋዩን ጌሐዚን፦ "ተመልከት
ያች ሴት ከሹኔም ወደዚህ በመምጣት ላይ
ናት! 26 ፈጠን ብለህ ሂድና የእርስዋን የባልዋ
ንና የልጅዋን ደኅንነት ጠይቃት" አለው።
እርስዋም ጌሐዚን "ሁላችንም ደኅና ነን"
ስትል ነገረችው። 27 ወደ ኤልሳዕ በቀረበች ጊዜ
ግን ወደ መሬት ለጥ ብላ እጅ በመንሣት እግሮ
ቹን ያዘች፤ በዚህ ጊዜ ጌሐዚ ገፍቶ ሊያስወግዳት
ቃጣ፤ ኤልሳዕ ግን "ተዋት! ምን ያህል ጭንቀት
እንዳለባት አታይምን? እግዚአብሔርም ስለ እር
ስዋ ችግር የገለጠልኝ ነገር የለም" አለው።
28 ሴቲቱም "ልጅ እንድትሰጠኝ ጠይቄህ
ነበርን? 'የማይፈጸምስ የተስፋ ቃል አትስጠኝ'
ብዬ ነግሬህ አልነበረምን?" አለችው።
29 ኤልሳዕም ወደ ጌሐዚ መለስ ብሎ "በፍ
ጥነት ተነሥና እኔ የምመረኰዘውን በትር ይዘህ
ሂድ! ለአንድም ሰው ሰላምታ ለመስጠት እንኳ
በመንገድ አትቁም፤ ማንም ሰው ሰላምታ ቢሰ
ጥህ አጸፋውን ለመመለስ ጊዜ አታጥፋ፤ በቀ
ጥታ ወደ ቤት ሄደህ የእኔን በትር በልጁ ላይ
አኑር" አለው።
30 ሴትዮዋ ግን ኤልሳዕን "በምተማመንበት
በሕያው እግዚአብሔር ስምና በነፍስህ እምልል
ሃለሁ፤ ከቶ እንተን ትቼ አልሄድም" አለችው፤
ስለዚህ እርስዋን ተከትሎ ለመሄድ ተነሣ፤
31 ጌሐዚም ወደ ፊት ቀድሞአቸው ሄደና የኤ
ልሳዕን በትር በልጁ ላይ አኖረ፤ ነገር ግን ድም
ፅም ሆነ ሌላ የሕይወት ምልክት አልነበረም፤
ስለዚህም ተመልሶ ሄዶ ኤልሳዕን "ልጁ ሊነሣ
አልቻለም!" አለው።
32 ኤልሳዕም በደረሰ ጊዜ ብቻውን ወደ
ክፍሉ ገብቶ ልጁ ሞቶ በአልጋው ላይ መጋደ
ሙን አየ፤ 33 ከልጁ ጋር ብቻውን ሆኖ ከፍሉ
ንም ዘግቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ 34 ከዚህም
በኋላ አፉን ከአፉ፥ ዐይኖቹን ከዐይኖቹ፥ እጆ
ቹን ከእጆቹ ጋር ገጥሞ በልጁ ሬሳ ላይ ተጋ
ደመ፤ ኤልሳዕም ተዘርግቶ እንደተጋደመበት
የልጁ ሰውነት መሞቅ ጀመረ። 35 ኤልሳዕም
ተነሥቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ይመላ
ለስ ጀመር፤ እንደገናም ተመለሰና በመዘርጋት
በልጁ ላይ ተጋደመ፤ ልጁም ሰባት ጊዜ ካስነ
ጠሰው በኋላ ዐይኖቹን ከፈተ። 36 ኤልሳዕም
ጌሐዚን "የልጁን እናት ጥራ" አለው፤ እርስ
ዋም በመጣች ጊዜ ኤልሳዕ "ልጅሽ ይኸው
ልሽ!" አላት። 37 እርስዋም ወደ መሬት ለጥ
ብላ በኤልሳዕ ጫማ ላይ በመውደቅ እጅ
ነሣች፤ ከዚያም በኋላ ልጅዋን ይዛ ሄደች።

### ሌሎች ሁለት ተአምራት

38 በመላ አገሪቱ ረሀብ በነበረበት በአንድ
ወቅት ኤልሳዕ ወደ ጊልጋል ተመልሶ መጣ፤
በዚያም የነቢያትን ጉባኤ በማስተማር ላይ ሳለ
አገልጋዩን "ትልቅ ድስት ጥደህ ወጥ ሥራላ
ቸው" አለው። 39 ከነቢያቱም አንዱ ጎመን
የሚመስል ቅጠላ ቅጠል ለመልቀም ወደ ሜዳ
ሔደ፤ እርሱም በዱር ውስጥ የበቀለ የቅል
ሐረግ አገኘ፤ መሸከም የሚችለውን ያህል በር
ከት ያለ ቅል ቈርጦ አመጣ፤ የዚያንም ምንነት
ሳያውቅ ከትፎ ወጡ ውስጥ ጨመረው፤ 40 ነቢ
ያትም እንዲመገቡት የወጣላቸውን ወጥ ቀም
ሰው "በዚህ ወጥ ውስጥ የሚገድል መርዝ
አለ!" ብለው ወደ ኤልሳዕ ጮኹ፤ ሊመገቡ
ትም አልወደዱም፤ 41 ኤልሳዕም ዱቄት እንዲሰ
ጡት ጠይቆ በድስቱ ውስጥ ጨመረውና
"ወጡን እያወጣህ ጨምርላቸው!" ሲል
አዘዘ፤ ስለዚህም ጊዜ በወጡ ውስጥ ምንም ዐይ
ነት መራራነት አልነበረም።
42 ሌላም ጊዜ በዓልሻሊሻ ተብሎ ከሚጠ
ራው ስፍራ አንድ ሰው በመከር ጊዜ በመጀመ
ሪያ ከተወቃው ገብስ የተጋገሩ ሃያ የዳቦ ሙል
ሙሎችና አዲስ የተቈረጠ እሸት ለኤልሳዕ ይዞ
ለት መጣ፤ ኤልሳዕም "ለነቢያት ጉባኤ አቅር
ብላቸውና ይብሉ" ብሎ አገልጋዩን አዘዘው፤
43 አገልጋዩ ግን "ይህ ለመቶ ሰው የሚበቃ
ይመስልሃልን?" ሲል ጠየቀው።
ኤልሳዕም "እንዲበሉ አቅርብላቸው፤ ምክን
ያቱም በልተው መጥገብ ብቻ ሳይሆን እንደሚ
ተርፋቸውም እግዚአብሔር ተናግሮአል"
አለው። 44 ስለዚህም አገልጋዩ ምግቡን አቀረበ
ላቸው እግዚአብሔርም በተናገረው መሠረት
ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላም የተረፈ
ምግብ ነበር።

## ምዕራፍ 5

### ንዕማን ከአሠቃቂ የቆዳ በሽታ ዳነ

1 የሶርያ ጦር አዛዥ የነበረው ንዕማን በሶርያ
ንጉሥ ዘንድ እጅግ የተከበረና የተወደደ

4፥34-35 ፦ 1ነገ. 17፥21። 5፥1-14 ፦ ሉቃ. 4፥27።

ኮረብታ በደረሱ ጊዜ ጌሐዚ ሁለቱን ከረጢት
ተቀብሎ ወደ ቤት አስገባ፤ ከዚያም በኋላ የንዕ
ማንን አገልጋዮች አሰናብቶ፥ 25 ወደ ቤት ተመ
ልሶ ገባ፤ ኤልሳዕም "እስከ አሁን የት ነበ
ርክ?" ሲል ጠየቀው።

ጌሐዚም "ጌታዬ! ኧረ እኔ የትም አልሄ
ድሁ!" ሲል መለሰ።

26 ኤልሳዕም "ሰውየው ሊያነጋግርህ ከሠረገ
ላው ላይ ሲወርድ እኔ በመንፈስ ከአንተ ጋር
አልነበርኩምን? እነሆ አሁን ገንዘብና ልብስ፥
የወይራና የፍራፍሬዎችን ቦታ፥ በግና የቀንድ
ከብት ወይም አገልጋዮችን ለመቀበል ጊዜው
አይደለም፤ 27 ከዚህም የተነሣ እነሆ የንዕማን
አሠቃቂ የቆዳ በሽታ ወደ አንተ ይተላለፋል፤
አንተና ዘሮችህ ለዘላለም ከዚያ በሽታ አትነ
ጹም" አለው።

ጌሐዚም ወጥቶ ሲሄድ ያ በሽታ ስለተጋባ
በት ገላው እንደ በረዶ ነጭ ሆነ።

## ምዕራፍ 6

### ሰጥሞ የነበረው መጥረቢያ በተአምር ወጣ

1 በኤልሳዕ ኀላፊነት ሥር የነበሩት የነቢያት
ጉባኤ አባላት "የምንኖርበት ስፍራ ጠባብ
ነው፤ 2 ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄደን ዛፍ በመቍ
ረጥ የምንኖርበት ቤት እንድንሠራ ፍቀድልን"
አሉት።

ኤልሳዕም "እሺ መልካም ነው" አላቸው።

3 ከነቢያቱም አንዱ ኤልሳዕ አብሮአቸው እን
ዲሄድ ጠየቀው፤ ኤልሳዕም በጥያቄው ተስማ
ምቶ፥ 4 አብረው ሄዱ፤ ወደ ዮርዳኖስም በደ
ረሱ ጊዜ ዛፍ የመቍረጥ ተግባራቸውን
ጀመሩ፤ 5 ከእነርሱም አንዱ ዛፍ በመቍረጥ
ላይ ሳለ በድንገት መጥረቢያው ከዛቢያው ላይ
ወድቆ ውሃ ውስጥ ገባ፤ እርሱም ድምፁን ከፍ
አድርጎ በመጮኽ "ጌታዬ ሆይ! እንግዲህ ምን
እደርጋለሁ? መጥረቢያው የተውሶ ነው!" ሲል
ለኤልሳዕ ነገረው።

6 ኤልሳዕም "በየት በኩል ነው የወደቀው?"
ሲል ጠየቀው።

ሰውየውም መጥረቢያው የወደቀበትን ስፍራ
ባሳየው ጊዜ ኤልሳዕ አንድ እንጨት ቈርጦ ወደ
ውሃው ውስጥ በመጣል መጥረቢያው እንዲንሳ
ፈፍ አደረገው፤ 7 ከዚህም በኋላ ኤልሳዕ "አው
ጥተህ ውሰድ" አለው፤ ሰውየውም ጐንበስ
ብሎ አነሣው።

### የሶርያ የጦር ሠራዊት ድል መሆን

8 እነሆ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር በጦር
ነት ላይ ነበር፤ እርሱም ከጦር አዛዦቹ ጋር
ተማክሮ የሚሰፍሩበትን ቦታ መረጠ፤ 9 ኤልሳዕ
ግን "ሶርያውያን ደፈጣ አድርገው ስለሚጠብ
ቁህ ወደዚያ ስፍራ እትቅረብ" ሲል ነገረው፤
10 ስለዚህም የእስራኤል ንጉሥ በዚያ የሚኖሩ
ትን ወታደሮቹን ስላስጠነቀቃቸው ነቅተው
ይጠባበቁ ነበር፤ ይህም ድርጊት ብዙ ጊዜ በተ
ደጋጋሚ ተፈጸመ።

11 ከዚህም የተነሣ የሶርያው ንጉሥ እጅግ
ተበሳጨ፤ የጦር አዛዦቹንም ጠርቶ፥ "ከእና
ንተ መካከል ለእስራኤል ንጉሥ የእኛን ምስ
ጢር የሚገልጥለት ማን ነው?" ሲል ጠየቃ
ቸው።

12 ከእነርሱም አንዱ "ንጉሥ ሆይ! ከእኛ
መካከል ይህንን የሚያደርግ ማንም የለም፤
በመኝታ ክፍልህ እንኳ ሆነህ የምትናገረውን
ሁሉ ሳይቀር ለእስራኤል ንጉሥ ምስጢሩን
የሚገልጥለት ኤልሳዕ የተባለው ነቢይ ነው"
ሲል መለሰለት።

13 የሶርያም ንጉሥ "እርሱ የሚገኝበትን
ስፍራ ፈልጉ፤ እኔም በቀጥታ እማርከዋለሁ"
አላቸው።

በዚህም ጊዜ ኤልሳዕ በዶታን የሚኖር
መሆኑ ስለተነገረው፥ 14 ንጉሡ በፈረሶችና በሠ
ረገላዎች የተጠናከረ ሠራዊት ወደዚያ ላከ፤ እነ
ርሱም በሌሊት ደርሰው ከተማይቱን ከበቡ።
15 በማግሥቱም ማለዳ የኤልሳዕ አገልጋይ ከመ
ኝታው ተነሥቶ ከቤት ሲወጣ በፈረሶችና በሠረ
ገላዎች የታጀቡ የሶርያ ወታደሮች ከተማይቱን
መክበባቸውን አየ፤ ወደ ኤልሳዕም ተመልሶ
ድምፁን ከፍ በማድረግ "ጌታዬ! እነሆ ልን
ጠፋ ነው! ምን ማድረግ ይሻለናል?" ሲል ጠየ
ቀው።

16 ኤልሳዕም "አይዞህ አትፍራ! ከእነርሱ
ጋር ከተሰለፈው ይልቅ ከእኛ ጋር የተሰለፈው
ሠራዊት ይበልጣል" አለው፤ 17 ከዚህም በኋላ
ኤልሳዕ "እግዚአብሔር ሆይ! ማየት እንዲችል
ዐይኖቹን ክፈትለት!" ሲል ጸለየ፤ እግዚአብሔ
ርም ለጸሎቱ መልስ በመስጠት የኤልሳዕ አገል
ጋይ ዐይኖቹ እንዲከፈቱለት ስላደረገ በኮረብ
ታው ጐን ብዙ የእሳት ፈረሶችና ሠረገላዎች
በኤልሳዕ ዙሪያ ተሰልፈው የሚጠብቁት መሆና
ቸውን ተመለከተ።

18 ሶርያውያንም አደጋ መጣል በጀመሩ ጊዜ
ኤልሳዕ "እግዚአብሔር ሆይ! እነዚህ ሰዎች
እንዲታወሩ አድርግ!" ብሎ ጸለየ፤ እግዚአብ
ሔርም የኤልሳዕን ጸሎት በመስማት ዐይናቸው
እንዲታወር አደረገ። 19 ከዚህም በኋላ ኤልሳዕ
ወደ እነርሱ ቀረብ ብሎ "መንገድ ተሳስ
ታችኋል፤ የምትፈልጓት ከተማ ይህች አይደለ
ችም፤ ይልቅስ ወደምትፈልጉት ሰው እኔ ልመ
ራችሁ ስለምችል ተከተሉኝ" ብሎ ወደ ሰማ
ርያ መራቸው።

20 ወደ ከተማይቱም እንደገቡ ኤልሳዕ "እግ
ዚአብሔር ሆይ! ማየት እንዲችሉ ዐይናቸውን
ግለጥላቸው" ሲል ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎ
ቱን ሰምቶ ዐይናቸውን በከፈተላቸው ጊዜ በሰ
ማርያ ውስጥ መሆናቸውን ተረዱ።

21 የእስራኤልም ንጉሥ ሶርያውያንን ባያ
ቸው ጊዜ "ጌታዬ ሆይ! ልግደላቸውን? ልግደ
ላቸውን?" ሲል ኤልሳዕን ጠየቀው ።
22 ኤልሳዕም "አይሆንም! እንኳን እነዚህን፥
በሰይፍህና በቀስትህ የማረክሃቸውን ወታደሮች
መግደል አይገባህም፤ ይልቅስ የሚበሉትና የሚ
ጠጡትን ምግብ አቅርብላቸውና ወደ ንጉሣ
ቸው ተመልሰው እንዲሄዱ አድርግ" አለው ።
23 ስለዚህም የእስራኤል ንጉሥ ለእነርሱ ታላቅ
ግብዣ አደረገላቸው፤ ከበሉና ከጠጡም በኋላ
ወደ ሶርያ ንጉሥ መልሶ ላካቸው፤ ከዚያም
ጊዜ ጀምሮ ሶርያውያን በእስራኤል ምድር ላይ
ወረራ ማድረጋቸውን አቆሙ ።

### ሰማርያ ተከበበች

24 ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሶርያ ንጉሥ ቤንሀ
ዳድ መላ ሠራዊቱን በእስራኤል ላይ በማዝመት
የሰማርያን ከተማ ከበበ፤ 25 ከበባውም የምግብን
እጥረትና ብርቱ ረሀብን ከማስከተሉ የተነሣ፥
የአንድ አህያ ራስ ዋጋ እስከ ሰማኒያ ጥሬ ብር፥
ሁለት መቶ ግራም የሚያህል የርግብ ኩስ ዋጋ
ደግሞ አምስት ጥሬ ብር ማውጣት ጀመረ ።
26 አንድ ቀን የእስራኤል ንጉሥ በከተማይቱ
የቅጽር ግንብ ላይ በሚመላለስበት ጊዜ አንዲት
ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ "ንጉሥ ሆይ! እባ
ክህ እርዳኝ!" ስትል ጮኸች ።
27 ንጉሡም "እግዚአብሔር ሊረዳሽ ካልፈ
ቀደ እኔ ምን ዐይነት ዕርዳታ ልሰጥሽ እችላ
ለሁ? ስንዴ ወይስ የወይን ጠጅ? ምን ያስኸ
ይመስልሻል? 28 ለመሆኑ 'ችግርሽ ምንድን
ነው?'" ሲል ጠየቃት ።
እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰችለት፥ "ባለ
ፈው ቀን ይህች ሴት 'ዛሬ የአንቺን ልጅ እን
ብላ፥ በማግሥቱ ደግሞ የእኔን ልጅ እንበላለን'
ስትል አሳብ አቀረበች ። 29 ስለዚህም የእኔን
ልጅ ቀቅለን በላን፤ በማግሥቱም 'ልጅሽን
አምጪና እንብላ' ብዬ ጠየቅኋት፤ እርስዋ ግን
ደበቀችው ።"
30 ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ በሐዘን ልብ
ሱን ቀደደ፤ በግንቡ ላይ በመሆኑ በአቅራቢ
ያው የነበረው ሕዝብ ንጉሡ ከልብሱ በውስጥ
በኩል ማቅ ለብሶ እንደነበር አዩ ። 31 ንጉሡም
ድምፁን ከፍ በማድረግ "የዛሬይቱ ጀንበር ከመ
ጥለቅዋ በፊት የኤልሳዕ ራስ ሳይቈረጥ ቢያድር
እግዚአብሔር እኔን በሞት ይቅጣኝ!" ሲል
ተናገረ ። 32 ወዲያውኑም ኤልሳዕን ይዞ የሚ
መጣ መልእክተኛ ላከ ።
በዚህም ጊዜ ኤልሳዕ ሊጐበኙት ከመጡ
ጥቂት ሽማግሌዎች ጋር በቤት ውስጥ ነበር፤
የንጉሡ መልእክተኛ ከመድረሱም በፊት ኤል
ሳዕ ሽማግሌዎቹን "ያ ነፍሰ ገዳይ እኔን ለማስገ
ደል አንድ ሰው ልኮአል፤ እነሆ እርሱ እዚህ
በሚደርስበት ጊዜ በሩን ዝጉ፤ ወደ ውስጥም
እንዲገባ አትፍቀዱለት፤ ንጉሡም እርሱን ተከ
ትሎ መጥቶ በኋላው ይገኛል" አላቸው ።
33 ገና ይህን ተናግሮ ሳይጨርስ ንጉሡ** ድን
ገት ከተፍ ብሎ "ይህንን መከራ በእኛ ላይ
ያመጣብን እግዚአብሔር ነው! ታዲያ እርሱ
አንድ ነገር ያደርግ ዘንድ ከዚህ በላይ ምን ልጠ
ብቅ?" አለ ።

## ምዕራፍ 7

1 ኤልሳዕም "እግዚአብሔር የሚለውን ስማ!
ነገ ይህን ጊዜ በሰማርያ ሦስት ኪሎ ምርጥ
ስንዴ ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ በአንድ ጥሬ
ብር ይሸመታል" ሲል መለሰለት ።
2 በዚህ ጊዜ የንጉሡ የቅርብ ባለሟል የሆነ
አገልጋዩ ኤልሳዕን "እግዚአብሔር ራሱ የሰማይ
መስኮቶችን ከፍቶ እህልን እንደ ዝናም ቢያዘ
ንም እንኳ ይህ ሊሆን ከቶ አይችልም!" ሲል
በመጠራጠር ተናገረ ።
ኤልሳዕም "ያን እህል በዐይንህ ታያለህ!
ነገር ግን ከእርሱ ምንም ነገር አትቀምስም"
አለው ።

### የሶርያ ሠራዊት ሽሽት

3 ለሥጋቸው በአሠቃቂ የቆዳ በሽታ የነደደ
አራት ሰዎች ከሰማርያ ቅጽር በር ውጭ ነበሩ፤
እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፥
"እስከንሞት ድረስ ለምን በዚህ እንቆያለን?
4 ወደ ከተማይቱ መግባት ምንም ጥቅም የለ
ውም፤ ምክንያቱም እዚያ ከገባን በረሀብ እንሞ
ታለን፤ እዚህም ብንቀር ከመሞት አንድንም፤
ስለዚህ ተነሥተን ወደ ሶርያውያን ሰፈር እን
ሂድ፤ እነርሱም ቢሆኑ ከመግደል የከፋ ሌላ
ምንም ነገር ሊያደርጉብን አይችሉም፤ ምናልባ
ትም ሕይወታችንን ያተርፉ ይሆናል ።" 5 ከዚ
ህም በኋላ ቀኑ ሲመሽ ሲል ወደ ሶርያውያን
ሰፈር ሄዱ፤ ነገር ግን እዚያ ሲደርሱ ማንም ሰው
አልነበረም፤ 6 ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአ
ብሔር ሶርያውያንን በፈረሶችና በሠረገላዎች የታ
ጀበ የብዙ ሠራዊት ግሥጋሤ የሚመስል ድምፅ
አሰምቶአቸው ስለነበር ነው፤ ይኸውም ሶርያው
ያን እንዳሰቡት የእስራኤል ንጉሥ የሒታውያንና
የግብጽ ነገሥታትን ከነሠራዊቶቻቸው ቀጥሮ
አደጋ ሊጥልባቸው የመጣ መስሎአቸው ነበር ።
7 ስለዚህም በዚያን ቀን ምሽት ሶርያውያን ድንኳ
ኖቻቸውን፥ ፈረሶችና አህዮቻቸውን በጠቅላላም
ሰፈራቸውን ሁሉ እንዳለ ትተው ሕይወታቸውን
ለማትረፍ ሸሽተው ሄደዋል ።

** 6፥33 ንጉሡ ፦ ወይም "መልእክተኛው ።"
6፥29 ፦ ዘዳ. 18፥57፤ ሰ.ኤ. 4፥10 ።

8 እራቱ ሰዎች ወደ ሶርያውያን ሰፈር ዳርቻ
በደረሱ ጊዜ ወደ አንድ ድንኳን ውስጥ ገቡ፤
በዚያም ያገኙትን ነገር ሁሉ በልተውና ጠጥ
ተው ያገኙትን ብር፥ ወርቅና ልብስ ይዘው
ሄደው ደበቁ፤ እንደገናም ተመልሰው ወደ
ሌላ ድንኳን በመግባት እንደዚያው አደረጉ፤
9 ከዚህም በኋላ እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባ
ባሉ፤ "መልካም አላደረግንም፤ እነሆ ዛሬ
ታላቅ የምሥራች አግኝተናል፤ ይህንንም መል
ካም ዜና ደብቀን ልናስቀር አይገባንም፤ ይህንን
የምሥራች ሳንነግር እስኪነጋ ብንቆይ በእርግጥ
ቅጣት ይደርስብናል፤ ስለዚህም አሁኑኑ ሄደን
ለንጉሡ የጦር መኰንኖች እንንገር!" 10 ከዚ
ያም በኋላ ከሶርያውያን ሰፈር በመነሣት ወደ
ሰማርያ ተመልሰው ሄዱ፤ እዚያም እንደደረሱ
የከተማይቱን ቅጽር በር ዘበኞች ጠርተው
"ወደ ሶርያውያን ሰፈር ሄደን ነበር፤ ነገር ግን
ምንም ያየነው ሰው ወይም የሰማነው ድምፅ
እንኳ የለም፤ ፈረሶችና አህዮች እንደታሰሩ
ናቸው፤ ድንኳኖቹም ሶርያውያን ትተዋቸው
ስለሄዱ ባዶአቸውን ናቸው" ሲሉ ነገሩአቸው።
11 ዘብ ጠባቂዎቹም ወሬውን ለሰነዙት
እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ ተሰማ፤ 12 ጊዜ
ውም ገና ሌሊት ነበር፤ ንጉሡ ግን ከመኝ
ታው ተነሥቶ ባለሟሎቹ የሆኑትን ባለሥልጣ
ኖች እንዲህ አላቸው፥ "የሶርያውያንን ዕቅድ
ልንገራችሁ፤ እነርሱ በዚህ ስላለው ረሀብ
ያውቃሉ፤ ስለዚህ ሰፈራቸውን ለቅቀው በገ
ጠር ለመሸሸግ ሄደዋል፤ እኛም ምግብ ፍለጋ
ብንወጣ ከነሕይወታችን ማርከው ከተማችንን
ይወስዳሉ።"
13 ከባለሟሎቹም አንዱ "በዚህች ከተማ
ውስጥ የተረፈው ሕዝብ ከዚህ በፊት እንደሞ
ቱት ሰዎች ሁሉ ከሞት የሚያመልጥ አይደ
ለም፤ ስለዚህ የሆነውን ነገር ማወቅ እንድን
ችል ጥቂት ሰዎችን መርጠን ከሞት ከተረፉት
አምስት ፈረሶች ጋር እንላክ" ሲል አሳብ አቀ
ረበ። 14 እነርሱም ጥቂት ሰዎችን መረጡ፤ ንጉ
ሡም እነዚያን ሰዎች በሁለት ሠረገላዎች እን
ዲቀመጡ አድርጎ በሶርያውያን ሠራዊት ላይ
የደረሰውን ሁኔታ መርምረው እንዲመለሱ
መመሪያ በመስጠት ላካቸው። 15 ሰዎቹም
ከዚያ ተነሥተው እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ ድረስ
ዘልቀው ሄዱ፤ በየመንገዱም ሶርያውያን ሲሸሹ
ጥለውት የሄዱትን ልብስና መሣሪያ ሁሉ አዩ፤
ከዚያም በኋላ ተመልሰው መጥተው ይህን ሁሉ
ለንጉሡ ነገሩ። 16 ሕዝቡም በፍጥነት እየተራ
ወጠ ወጥቶ የሶርያን ሰፈር ዘረፈ፤ እግዚአብ
ሔር አስቀድሞ በተናገረውም መሠረት ሦስት
ኪሎ ምርጥ ስንዴ ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ
በአንድ ጥሬ ብር ተሸመተ።

17 በዚህም ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ የከተማ
ይቱ ቅጽር በር የቅርብ ባለሟሉ በሆነው አገል
ጋዩ ኀላፊነት ሥር እንዲጠበቅ አድርጎ ነበር፤
ነገር ግን ያንን አገልጋይ ሕዝቡ ስለረጋገጠው
በዚያ ሞተ፤ ይህም የሆነው ንጉሡ ኤልሳዕን
ለማነጋገር በሄደ ጊዜ ኤልሳዕ በዚያ አገልጋይ
ላይ የተናገረበት የትንቢት ቃል ስለተፈጸመ
ነው።
18 በዚያን ጊዜ ኤልሳዕ ለንጉሡ "በነገው
ዕለት በሰማርያ ከተማ ሦስት ኪሎ ምርጥ ስንዴ
ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ በአንድ ጥሬ ብር
ይሸመታል" ብሎ ነግሮት ነበር፤ 19 ለዚህም
ቃል ያ አገልጋዩ የሰጠው መልስ "እግዚአብ
ሔር ራሱ የሰማይ መስኮቶችን ከፍቶ እህልን
እንደዝናም ቢያዘንም እንኳ ይህ ሊሆን ከቶ
አይችልም" የሚል ነበር። ኤልሳዕም "ያን
እህል በዐይንህ ታያለህ፤ ነገር ግን ከእርሱ
ምንም ነገር አትቀምስም" ብሎት ነበር።
20 እንግዲህ ያ አገልጋይ በሰማርያ ከተማ ቅጽር
በር ላይ ሕዝብ ረጋግጦት ለመሞት የበቃው
ይህ ትንቢት ስለተፈጸመበት ነበር።

## ምዕራፍ 8

### የሹኔም ከተማ ነዋሪ የነበረችው ሴት ከስደት መመለስ

1 ልጅዋን ከሞት ያስነሣላትን፥ በሹኔም
ትኖር የነበረችውን ሴት እነሆ ኤልሳዕ አስቀ
ድሞ እንዲህ ሲል ነግሮአት ነበር፥ "እግዚአብ
ሔር እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ረሀብ በዚህች
ምድር ላይ ልኮአል፤ ከቤተሰብሽ ጋር በሕይ
ወት ለመትረፍ ከዚህ ተነሥተሽ ወደ ሌላ
ስፍራ ሂጂ።" 2 ስለዚህም የኤልሳዕን ምክር
ሰምታ ከነቤተሰብዋ ወደ ፍልስጥኤም አገር
በመሰደድ እስከ ሰባት ዓመት ቆይታ ነበር።
3 ከሰባቱም የረሀብ ዓመታት ፍጻሜ በኋላ
ወደ እስራኤል ተመለሰች፤ ወደ ንጉሡም
ቀርባ መኖሪያ ቤትዋና የእርሻ መሬትዋ እንዲ
መለስላት ጠየቀች። 4 ንጉሡንም የኤልሳዕ አገ
ልጋይ ከሆነው ከጌሐዚ ጋር ሲነጋገር አገኘ
ችው፤ ንጉሡ ከጌሐዚ ጋር የሚነጋገረውም
ኤልሳዕ ስላደረጋቸው ተአምራት ለማወቅ ፈልጎ
ነበር፤ 5 ኤልሳዕ የሞተ ሰው ማስነሣቱን ጌሐዚ
ለንጉሡ በሚነግርበት ጊዜ ሴቲቱ መጥታ አቤ
ቱታዋን ለንጉሡ አቀረበች፤ ጌሐዚም "ንጉሥ
ሆይ! ሴትዮዋ እነሆ ይህች ናት! ኤልሳዕ
ከሞት ያስነሣውም ልጅዋ ይኸ ነው!" በማ
ለት ለንጉሡ አስረዳ። 6 ጌሐዚ ለንጉሡ የሰጠ
ውን መልስ ሴትዮዋ ለንጉሡ እውነት መሆኑን
አረጋገጠችለት፤ ስለዚህም ንጉሡ አንድ ባለሥ
ልጣን ጠርቶ የእርስዋ የሆነው ማናቸውም ነገ
ርና እንዲሁም የእርሻ መሬትዋ በሰባት ዓመት

8፥1 ፦ 2ነገ. 4፥8-37።

ጊዜ ውስጥ ያስገኘው የእህል ሰብል ድርሻዋ
ጭምር እንዲመለስላት ትእዛዝ ሰጠላት ።

### ኤልሳዕና የሶርያ ንጉሥ ቤንሀዳድ

7 የሶርያ ንጉሥ ቤንሀዳድ በታመመ ጊዜ
ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ ሄደ ፤ ንጉሡም የኤልሳዕን
መምጣት ሰምቶ ፥ 8 ባለሟሎቹ ከሆኑት ባለሥ
ልጣኖች አንዱ የሆነውን ሐዛኤልን ጠርቶ "በን
ቢዩ ስጦታ ይዘህ ሂድና እኔ ከዚህ በሽታ እድን
ወይም አልድን እንደሆነ እግዚአብሔርን እንዲ
ጠይቅልኝ ለምነው" አለው ። 9 ስለዚህም ሐዛ
ኤል በደማስቆ ከሚገኘው ምርጥ የምድር በረ
ከት ሁሉ በአርባ ግመሎች ጭኖ ወደ ኤልሳዕ
ሄደ ፤ ሐዛኤልም ኤልሳዕን ባገኘው ጊዜ "አገል
ጋይህ ንጉሥ ቤንሀዳድ ከሕመሙ ይድን ወይም
አይድን እንደሆን እንድትነግረው እጠይቅህ
ዘንድ ልኮኛል" አለው ።
10 ኤልሳዕም "ቤንሀዳድ እንደሚሞት እግዚ
አብሔር ገልጦልኛል ፤ አንተ ግን ትድናለህ
ብለህ ንገረው" አለው ፤ 11 ከዚህ በኋላ ኤልሳዕ
ፊቱን በማጥቈር በሚያስፈራ ሁኔታ ሐዛኤልን
ተመለከተው ፤ ከዚህም የተነሣ ሐዛኤል ተጨ
ነቀ ፤ ወዲያውም ኤልሳዕ እንባውን ማፍሰስ
ጀመረ ፤ 12 ሐዛኤልም "ጌታዬ ስለምን ታለቅሳ
ለህ?" ሲል ጠየቀው ።
ኤልሳዕም "በእስራኤል ሕዝብ ላይ የምትፈ
ጽመውን አሠቃቂ ነገር ስለማውቅ ነው ፤ ምሽጉ
ቻቸውን በእሳት ታቃጥላለህ ፤ ምርጥ የሆኑ ወጣ
ቶቻቸውን ታርዳለህ ፤ ሕፃናቶቻቸውን በድንጋይ
ላይ ትፈጠፍጣለህ ፤ እርጉዞች የሆኑ ሴቶቻቸው
ንም ሆድ ትሰነጥቃለህ" ሲል መለሰለት ።
13 ሐዛኤልም "እኔ ለምንም የማልጠቅም
ኢምንት ነኝ ፤ ታዲያ ይህን ሁሉ ለማድረግ
የሚያስችለውን ኀይል ከቶ ከየት አገኛለሁ?"
ሲል ጠየቀ ።
ኤልሳዕም "አንተ የሶርያ ንጉሥ እንደምት
ሆን እግዚአብሔር ገልጦልኛል" ሲል መለሰ
ለት ።
14 ከዚህም በኋላ ሐዛኤል ተመልሶ ሲመጣ
"ኤልሳዕ ምን አለህ?" ሲል ቤንሀዳድ ጠየቀው ።
ሐዛኤልም "አንተ በእርግጥ እንደምትድን
ነግሮኛል" ሲል መለሰለት ። 15 ነገር ግን በማግ
ሥቱ ሐዛኤል ብርድልብስ ወስዶ ውሃ ውስጥ
ነከረ ፤ በዚያም ንጉሡን አፍኖ ገደለው ።
ሐዛኤልም በቤንሀዳድ እግር ተተክቶ የሶርያ
ንጉሥ ሆነ ።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም
(2 ዜ.መ. 21፥1-20)

16 የእስራኤል ንጉሥ የአክአብ ልጅ ኢዮ
ራም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የኢዮሣፍጥ
ልጅ ኢዮራም በይሁዳ ላይ ነገሠ ፤ 17 እርሱም
በነገሠ ጊዜ ሠላሳ ሁለት ዓመቱ ነበር ፤ መኖሪያ
ውንም በኢየሩሳሌም አድርጎ ስምንት ዓመት
ገዛ ። 18 ሚስቱም የአክአብ ልጅ ስለነበረች
እንደ አክአብ ቤተሰብ የእስራኤል ነገሥታት
ይፈጽሙት የነበረውን የክፋት መንገድ ተከ
ተለ ፤ በደል በመሥራትም እግዚአብሔርን አሳ
ዘነ ፤ 19 እግዚአብሔር ግን ከዘርያዎቹ መንግሥ
ትን እንደማያጠፋ ለአገልጋዩ ለዳዊት ተስፋ
ሰጥቶት ስለነበር ይሁዳን መደምሰስ አልፈለ
ገም ።
20 በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ኤዶም በይ
ሁዳ ላይ ዐመፀ ፤ የራሱንም ነፃ መንግሥት
ዐወጀ ፤ 21 ስለዚህም ኢዮራም ሠረገላዎቹን
በመላ አሰልፎ ወደ ጻዒር ዘመተ ፤ የኤዶም
ሠራዊትም ከበባቸው ፤ በሌሊትም እርሱና የሠ
ረገላዎቹ አዛዦዎች ከበባውን ጥሰው ሲያመ
ልጡ ፥ ወታደሮቹ ወደየቤታቸው ተበታተኑ ፤
22 ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ኤዶም ከይሁዳ ተገኝ
ነት ነፃ ወጣች ፤ በዚያኑ ጊዜም የሊብና ከተማ
ዐመፀች ።
23 ኢዮራም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገ
ኛል ፤ 24 ኢዮራም ሞተ ፤ በዳዊት ከተማ ውስጥ
በሚገኘው የነገሥታት መካነ መቃብር ተቀ
በረ ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ ልጁ አካዝያስ
ነገሠ ።

### የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ
(2 ዜ.መ. 22፥1-6)

25 የእስራኤል ንጉሥ የአክአብ ልጅ ኢዮ
ራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት የኢዮ
ራም ልጅ አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ ፤ 26 በነ
ገሠም ጊዜ የሃያ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረ ፤
መኖሪያውንም በኢየሩሳሌም አድርጎ አንድ
ዓመት ብቻ ገዛ ፤ እናቱ ሀታልያ ተብላ የምትጠ
ራው የአክአብ ልጅ የእስራኤል ንጉሥ የነበ
ረው የዖምሪ የልጅ ልጅ ነበረች ፤ 27 አካዝያስ
የንጉሥ አክአብ ዐማች ከመሆኑ የተነሣ ልክ
እንደ አክአብ ቤተሰብ ኃጢአት በመሥራት
እግዚአብሔርን አሳዘነ ።
28 በሶርያው ንጉሥ ሐዛኤል ላይ በታወጀው
ጦርነት ፥ ንጉሥ አካዝያስ የእስራኤል ንጉሥ
ዮራም ተባባሪ በመሆን ዘመተ ፤ የሁለቱም ነገ
ሥታት ሠራዊት ከሶርያውያን ሠራዊት ጋር በገ
ለዓድ በምትገኘው በራሞት ጦርነት በገጠመ
ጊዜ ኢዮራም በውጊያው ላይ ቈሰለ ፤ 29 ከቊስ
ሉም ለመፈወስ ተመልሶ ወደ ኢይዝራኤል
ከተማ ሄደ ፤ አካዝያስም ዮራምን ለመጠየቅ
ወደዚያ ሄደ ።

---

8፥13 ፦ 1ነገ. 19፥15 ። 8፥19 ፦ 1ነገ. 11፥36 ። 8፥20 ፦ ዘፍ. 27፥40 ።

## ምዕራፍ 9

### ዩሁ በእስራኤል ላይ ተቀብቶ ነገሠ

[1] በዚያን ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ ደቀ መዛሙርቱ
ከሆኑት ነቢያት አንዱን ጠርቶ እንዲህ አለ፤
"በገለዓድ ወደምትገኘው ወደ ራሞት ለመሄድ
ተዘጋጅ፤ ይህንንም የዘይት ማሰሮ ያዝ፤ [2] እዚ
ያም በደረስህ ጊዜ የኢዮሳፍጥ ልጅ፥ የኒምሺ
የልጅ ልጅ የሆነውን ዩሁን ፈልግ፤ እርሱንም
ከጓደኞቹ በማስገለል ወደ ልዩ ክፍል አስገብ
ተህ፥ [3] ይህን የወይራ ዘይት በራሱ ላይ አፍስስ
በት፤ 'አንተ ተቀብተህ በእስራኤል ላይ እንድ
ትነግሥ እግዚአብሔር አዝዞአል' ብለህም ንገ
ረው፤ ከዚህም በኋላ በሩን በመክፈት በተቻለ
ፍጥነት ከዚያ ሰፍራ ተነሥተህ ሂድ።"

[4] ስለዚህም ወጣቱ ነቢይ ወደ ራሞት ሄደ፤
[5] እዚያም እንደደረሰ የጦር መኰንኖች ተቀም
ጠው ሲወያዩ አግኝቶ "ጌታዬ ለአንተ የምሰጥህ
መልእክት አለኝ" አለው።

ዩሁም "ከእኛ መካከል ለማንኛችን ነው
የምትናገረው?" ሲል ጠየቀው።

ነቢዩም "የምናገረው ለአንተው ነው" ሲል
መለሰ። [6] ከዚህ በኋላ ሁለቱ ወደ ቤት ውስጥ
ገብተው ወጣቱ ነቢይ የወይራውን ዘይት በዩሁ
ራስ ላይ አፈሰሰበትና እንዲህ አለው፥ "የእስራ
ኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር የሚናገረው
ይህ ነው፥ 'በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ተቀብተህ
እንድትነግሥ አድርጌሃለሁ፤ [7] አንተም የአከ
አብ ልጅ የሆነውን ጌታህን ንጉሡን መግደል
አለብህ፤ በዚህም ዐይነት ነቢያቶቼንና ሌሎች
ንም አገልጋዮቼን የገደለችውን ኤልዛቤልን እበ
ቀላታለሁ፤ [8] መላው የአክአብ ቤተሰብና ዝር
ያው ሁሉ መሞት አለባቸው፤ እኔ ከእርሱ ቤተ
ሰብ ወንድ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ወጣቱ
ንም ሽማግሌውንም እስወግዳለሁ። [9] የእስራ
ኤል ነገሥታት በነበሩት በኢዮርብዓምና በበዕሻ
ቤተሰቦች ላይ ያደረግሁትን ሁሉ በአክአብ ቤተ
ሰብ ላይ አፈጽማለሁ። [10] ኤልዛቤል የመቀበር
ዕድል እንኳ አታገኝም፤ የአርስዋም ሬሳ በኢይ
ዝራኤል ግዛት ውሾች ይበሉታል፤'" ይህን
ሁሉ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ወጣቱ ነቢይ በሩን
በመክፈት ከዚያ ክፍል ወጥቶ ሸሸ።

[11] ዩሁም ጓደኞቹ ወደሆኑት ወደ ጦር
መኰንኖቹ በመጣ ጊዜ "ሁሉ ነገር ሰላም
ነውን? ለመሆኑ ይህ እብድ መሳይ ሰው ከአንተ
ምን ይፈልጋል?" ቢሉ ጠየቁት።

ዩሁም "ሰውየውንም ሆነ እርሱ የሚናገረ
ውን እናንተ ታውቁታላችሁ" አላቸው።

[12] እነርሱም "እረ እኛ አናውቅም! ምን
እንደተናገረ አስረዳን" ሲሉ መለሱለት።

ዩሁም "'በእስራኤል ላይ ተቀብተህ እንድ
ትነግሥ እግዚአብሔር አዝዞአል' አለኝ" ሲል
አስረዳቸው።

[13] የዩሁ ጓደኞች የነበሩት የጦር መኰንኖች
ልብሳቸውን እያወለቁ ዩሁ በሚራመድበት
ደረጃ ላይ አነጠፉ፤ በዚያም ላይ እንዲቆም
አድርገው መለከት ነፉ፤ ድምፃቸውንም ከፍ
አድርገው "ዩሁ ነግሦአል" ሲሉ ጮኹ።

### የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ተገደለ

[14-15] ከዚያም በኋላ ዩሁ በንጉሥ ኢዮራም
ላይ ሤራ ማካሄድ ጀመረ፤ ኢዮራም ከሶርያ
ንጉሥ ሐዛኤል ጋር በራሞት በተደረገው ጦር
ነት ላይ ስለቈሰለ በዚያን ጊዜ በኢይዝራኤል
ውስጥ በማገገም ላይ ነበር፤ ስለዚህም ዩሁ ጓደ
ኞቹ የሆኑትን የጦር መኰንኖች "እናንተ በእር
ግጥ ከእኔ ጋር ከሆናችሁ በኢይዝራኤል የሚኖረ
ውን ሕዝብ ለማስጠንቀቅ አንድ ወሬ ነጋሪ
እንኳ ከራሞት ወጥቶ እንዳያመልጥ አድርጉ"
አላቸው። [16] ከዚህም በኋላ ዩሁ በሠረገላው
ላይ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ገሠገሠ፤ በዚህ
ጊዜ ኢዮራም ገና ከቊስሉ አልዳነም ነበር፤
የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስም ሊጠይቀው መጥቶ
በዚያ ይገኝ ነበር።

[17] በኢይዝራኤል ከተማ መጠበቂያ ግንብ
ላይ የነበረው ቃፊር ዩሁና ተከታዩ ጭፍራ
ሲመጡ መቃረባቸውን አይቶ "ሰዎች እየጋለቡ
ሲመጡ አያለሁ!" ሲል የጥሪ ድምፅ አሰማ።

ኢዮራምም "አንድ ፈረሰኛ ልከህ የሚመ
ጡት ሰዎች በወዳጅነት ወይም በጠላትነት
መሆኑን አረጋግጥ" አለው።

[18] መልእክተኛውም ጋልቦ ሄዶ ዩሁን
"ንጉሡ አመጣጥህ በወዳጅነት እንደሆነ ማወቅ
ይፈልጋል" ሲል ጠየቀው።

ዩሁም "ይህ አንተን የሚመለከት ጕዳይ
አይደለም፤ ይልቅስ ወደ ኋላ አልፈህ ተከተ
ለኝ!" ሲል መለሰለት።

በከተማይቱም መጠበቂያ ግንብ ላይ የነበ
ረው ዘብ "መልእክተኛው በመምጣት ላይ ወዳ
ለው ጭፍራ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አል
መጣም" ሲል አስረዳ፤ [19] ሌላም መልእክተኛ
ተልኮ ያንኑ ተመሳሳይ ጥያቄ ለዩሁ አቀረበ
ለት፤ ዩሁም እንደገና "ይህ አንተን የሚመለ
ከት ጕዳይ አይደለም፤ ይልቅስ ወደ ኋላ አል
ፈህ ተከተለኝ" ሲል መለሰለት።

[20] "ዘበኛውም እንደገና መልእክተኛው በመ
ምጣት ላይ ወዳለው ጭፍራ ደርሶአል፤ ነገር
ግን ተመልሶ አልመጣም" ካለ በኋላ "የጭፍ
ራው መሪ ሠረገላ አነዳዱ እንደ እብድ ሰው
ነው፤ እንዲያውም ልክ ዩሁን ይመስላል" ሲል

---

9፥6 ፦ 1ነገ. 19፥16 ። 9፥10 ፦ 1ነገ. 21፥23 ።

ተናገረ። 21 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ኢዮራም “ሠረገ
ላዬን አዘጋጅልኝ!” ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤ ሠረገላ
ውም ተዘጋጅቶለት እርሱና ንጉሥ አካዝያስ
በየግል ሠረገላቸው እየጋለቡ ዩሁን ሊገናኙት
ወጡ፤ እነርሱም ዩሁን ቀድሞ የናቡቴ ርስት
በነበረው እርሻ ላይ አገኙት። 22 ኢዮራምም
“ዩሁ ሆይ! አመጣጥህ በሰላም ነውን?” ሲል
ጠየቀ።

ዩሁም “እናትህ ኤልዛቤል ባመጣችው አስ
ማትና የጣዖት አምልኮ ውስጥ ተነከረን እስካ
ለን ድረስ ምን ሰላም አለ?” ሲል መለሰለት።

23 ኢዮራምም ድምፁን ከፍ በማድረግ “አካ
ዝያስ ሆይ! ይህ እኮ ዐመፅ ነው!” ካለ በኋላ
ሠረገላውን መልሶ ሸሸ። 24 ዩሁ ቀስቱን ስቦ
ባለው ኀይል በመጠቀም ፍላጻውን ባስፈነጠረ
ጊዜ የኢዮራምን ጀርባ ወግቶ እስከ ልቡ
ዘለቀ፤ ኢዮራምም ሞቶ በሠረገላው ውስጥ
ወደቀ። 25 ዩሁም ቢድቃር ተብሎ የሚጠራ
ውን የቅርብ ረዳቱን “ሬሳውን አንሥተህ የና
ቡቴ ርስት በነበረው እርሻ ላይ ወርውረህ
ጣለው፤ እኔና አንተ የንጉሥ ኢዮራም አባት
ከነበረው ከአክአብ በስተኋላ እየጋለብን ስንሄድ
እግዚአብሔር በአክአብ ላይ የተናገረውን ቃል
አስታውስ፤ ቃሉም፥ 26 ‘ትናንትና የናቡቴንና
የልጆቹን መገደል አየሁ፤ በዚሁ እርሻ ላይ
እንደምቀጣህ እምላለሁ’ የሚል ነበር።” ስለ
ዚህ ዩሁ “እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይፈ
ጸም ዘንድ የኢዮራምን ሬሳ አንሥተህ የናቡቴ
ርስት በነበረው እርሻ ላይ በመወርወር
ጣለው!” ሲል የቅርብ ረዳቱን አዘዘ።

### የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ ተገደለ

27 ንጉሥ አካዝያስ የሆነውን ነገር ሁሉ በተ
መለከተ ጊዜ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ወደ
ቤትሀጋን ከተማ ሸሽቶ ሄደ፤ ዩሁም ተከታ
ትሎ እያሳደደው “እርሱንም ግደሉት!” ሲል
ለወታደሮቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም አካዝያስን
ተከታትለው ዪብልዓም ከተማ አጠገብ በምትገ
ኘው በጉር የአቀበት መንገድ ላይ በሠረገላው
ሲበር መትተው አቈሰሉት፤ እርሱ ግን እንደም
ንም ጨክኖ መጊዶ ከተማ እስኪደርስ ተጓዘ፤
በዚያም ሞተ፤ 28 ባለሟሎቹ የሆኑ ባለሥልጣና
ችም ሬሳውን በሠረገላ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰ
ደው በዳዊት ከተማ በሚገኘው የነገሥታት
መካነ መቃብር ቀበሩት።

29 አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ የሆነው የእስራ
ኤል ንጉሥ የአክአብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐ
ሥራ አንደኛው ዓመት ነበር።

### ንግሥት ኤልዛቤል ተገደለች

30 በዚህም ጊዜ ዩሁ ወደ ኢይዝራኤል
ደረሰ፤ ኤልዛቤልም ይህን የሆነውን ነገር
ሰምታ ዐይንዋን ተኳለች፤ ጠጕርዋንም ተሠ
ርታ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ በመስኮት
አዘንብላ ቍልቍል መንገዱን ትመለከት ነበር።
31 ዩሁ የቅጽሩን በር አልፎ ሲገባ “አንተ
ዚምሪ![5*] አንተ የጌታህ ገዳይ! ደግሞ እዚህ
ምን አመጣህ?” ስትል ጮኸችበት።

32 ዩሁም ቀና ብሎ ወደ ላይ በመመልከት
ድምፁን ከፍ አድርጎ “ከእኔ ጋር የሚተባበር
ማን ነው?” ሲል ጮኸ፤ ቍጥራቸው ከሁለት
እስከ ሦስት የሆነ የቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣ
ኖች በመስኮት ብቅ ብለው ወደ እርሱ ተመለ
ከቱ፤ 33 ዩሁም “ኤልዛቤልን ወደታች ወርው
ሩአት!” አላቸው፤ እነርሱም አንሥተው በወረ
ወሩአት ጊዜ ደምዋ በግንቡና በፈረሶች ላይ
ተረጨ፤ ዩሁም በሬሳዋ ላይ ፈረሶቹንና ሠረገላ
ውን ነዳበት፤ 34 ወደ ቤተ መንግሥቱም ገብቶ
ተመገበ፤ ከዚህም በኋላ “ምንም ቢሆን የን
ጉሥ ልጅ ነችና ያችን የተረገመች ሴት ወስዳ
ችሁ ቅበሩ!” አለ። 35 ሊቀብሩአት የሄዱ
ሰዎች ግን ከራስ ቅልዋ፥ ከእግሮችዋና ከእጆ
ችዋ አጥንት በቀር ምንም አላገኙም፤ 36 ይህን
ንም ሁሉ ለዩሁ በነገሩት ጊዜ ዩሁ እንዲህ
አለ፥ “ይህ ሁሉ የተፈጸመው እግዚአብሔር
በአገልጋዩ በኤልያስ አማካይነት አስቀድሞ በተ
ናገረው መሠረት ነው፤ ይኸውም ‘የኤልዛቤ
ልም ሬሳ በኢይዝራኤል ግዛት ውሾች ይበሉ
ታል፤ 37 ከሬሳውም የሚተርፈው እንደፍግ
በዚያ ይበተናል፤ ስለዚህም ማንም እርስዋነት
ዋን ለይቶ በማወቅ፦ ይህች ኤልዛቤል ናት፥
ሊል አይችልም’ ያለው ነው።”

## ምዕራፍ 10

### የአክአብ ዘርያዎች ሁሉ ተገደሉ

1 ብዛታቸው ሰባ የሚሆን የአክአብ ዘርያ
ዎች በሰማርያ ከተማ ይኖሩ ነበር፤ ዩሁ ደብ
ዳቤ ጽፎ የደብዳቤውን አንዳንድ ቅጂ ለከተማ
ይቱ ገዥዎች፥ ለታወቁ የአገር ሽማግሌዎችና
የአክአብን ዘርያዎች ለሚያሳድጉ ሞግዚቶች
ሁሉ ላከ፤ የደብዳቤውም ቃል፥ 2 “እናንተ
ለንጉሡ ዘርያዎች ኀላፊዎች ናችሁ፤ ፈረሶችና
ሠረገላዎች የጦር መሣሪያዎችና የተመሸጉ ከተ
ሞች ሁሉ በእናንተ እጅ ይገኛሉ፤ እንግዲህ
ይህ ደብዳቤ እንደደረሳችሁ ወዲያውኑ፥ 3 ከን
ጉሡ ዘርያዎች የተሻለውን አንዱን መርጣችሁ
አንግሡት፤ ለእርሱም በመከላከል ተዋጉለት”
የሚል ነበር።

---

5* 9፥31 ዚምሪ፦ በ1 ነገ. 16፥8-12 ሌላ ንጉሥ የገደለ የጦር አዛዥ ነው።

9፥26 ፦ 1ነገ. 21፥19። 9፥36 ፦ 1ነገ. 21፥23።

4 ከዚህም የተነሣ የሰማርያ ገዥዎች በፍር
ሃት ተሸብረው “ንጉሥ ኢዮራምና ንጉሥ አካ
ዝያስ ሊቋቋሙ ያልቻሉትን እኛ እንዴት
ዒሁን ልንቋቋመው እንችላለን?” አሉ ። 5 ስለዚ
ህም የቤተ መንግሥቱ ኀላፊና የከተማይቱ ገዥ
ከታወቁ የአገር ሽማግሌዎችና ከአሳዳጊ ሞግዚ
ቶች ጋር በመተባበር ለዒሁ “እኛ አገልጋዮችህ
ነን፤ አንተ የምታዝዘንን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ
ዎች ነን፤ እኛ ማንንም አናነግሥም፤ አንተ
መልካም መስሎ የታየህን አድርግ” ሲሉ መል
እክት ላኩ ።

6 ዒሁም “እናንተ ከእኔ ጋር ከተባበራችሁና
ትእዛዜንም ለመፈጸም ዝግጁዎች ከሆናችሁ፥
ነገ በዚህ ጊዜ የንጉሥ አክአብን ዝርያዎች
ሁሉ ራሶቻቸውን ቈርጣችሁ ይዛችሁልኝ ኑ”
ሲል ሌላ ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

ሰባው የንጉሥ አክአብ ዝርያዎች በሰማርያ
አሳዳጊዎቻቸው በሆኑ በታወቁ የአገር ሽማግሌ
ዎች ጥበቃ ሥር ነበሩ፤ 7 የዒሁ ደብዳቤ እንደ
ደረሳቸው የሰማርያ መሪዎች ሰባውንም የአከ
አብ ዝርያዎች በሙሉ ገደሉ፤ ራሶቻቸውንም
በመቅረጫ በቅርጫት ሞልተው በኢይዝራኤል
ወደ ነበረው ወደ ዒሁ ላኩለት ።

8 ዒሁ የአክአብ ዝርያዎች ራሶች ተቈርጠው
መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ በከተማይቱ ቅጽር
በር በሁለት ረድፍ ተከምረው እስከ ተከታዩ
ቀን ጠዋት ድረስ እንዲቆዩ ትእዛዝ ሰጠ፤ 9 በማ
ግሥቱም ማለዳ ወደ ከተማይቱ ቅጽር በር ሄዶ
በዚያ ለተሰበሰቡት ሕዝብ እንዲህ ሲል ተና
ገረ፥ “በንጉሥ ኢዮራም ላይ በማሤር የገደል
ኩት እኔ ነበርሁ፤ ስለዚህም እናንተ በዚያ
ጕዳይ አትጠየቁበትም፤ ነገር ግን እነዚህን
ሁሉ የገደለ ማን ነው? 10 ይህም ሁሉ እግዚአ
ብሔር ስለ አክአብ ዝርያዎች የተናገረው ቃል
እውነት መሆኑን ያስረዳል፤ እግዚአብሔር በነ
ቢዩ በኤልያስ አማካይነት የተናገረውን ቃል
ፈጽሞታል ።” 11 ከዚህም በኋላ ዒሁ በኢይዝራ
ኤል የሚኖሩትን ሌሎቹን የአክአብን ዘመዶች፥
ባለሟሎቹ የነበሩትን ባለሥልጣኖች እንዲሁም
የቅርብ ወዳጆቹንና ካህናቱን አንድም ሳይቀር
ሁሉንም ገደለ ።

### የንጉሥ አካዝያስ ዘመዶች በሙሉ ተገደሉ

12 ዒሁ ከኢይዝራኤል ተነሥቶ ወደ ሰማርያ
ሄደ፤ በመንገድ ሳለም “የእረኞች ሰፈር”
ተብሎ በሚጠራው ቦታ ሲደርስ፥ 13 ከሟቹ
የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ ዘመዶች መካከል ጥቂ
ቶቹን አግኝቶ “እናንተ እነማን ናችሁ?” ሲል
ጠየቀ ።

እነርሱም “እኛ የአካዝያስ ዘመዶች ነን፤
አሁንም የንግሥት ኤልዛቤልን ልጆችና የቀሩት
ንም ንጉሣውያን ቤተሰብ እጅ ለመንሣት ወደ
ኢይዝራኤል መሄዳችን ነው” ሲሉ መለሱለት ።
14 ዒሁም “እነዚህን ሰዎች ያዙአቸው!” ሲል
ለጭፍሮቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ ጭፍሮቹም ያዙአቸ
ውና ዒሁ በዚያው በውሃ ጕድጓድ አጠገብ ገደ
ላቸው ። ብዛታቸውም በሙሉ አርባ ሁለት
ሲሆን፥ ከእነርሱ አንድ እንኳ በሕይወት አልተ
ረፈም ።

### የቀሩት የአክአብ ዘመዶች
### በሙሉ ተገደሉ

15 ዒሁ ተነሥቶ እንደገና ጕዞ ቀጠለ፤ በመ
ንገድ ሳለም የሬካብን ልጅ ኢዮናዳብን አገኘ፤
ዒሁም ሰላምታ ከሰጠው በኋላ “እኔና አንተ
በአሳብ አንድ ነን፤ ታዲያ ከእኔ ጋር ትተባበራ
ለህን?” ሲል ጠየቀው ።

ኢዮናዳብም “አዎ እተባበርሃለሁ” ሲል
መለሰ ።

ዒሁም “እንግዲያውስ ጨብጠኝ” ሲል መለ
ሰለት፤ እጅ ለእጅ ተያይዘው ዒሁ ደግፎት በሠ
ረገላው ላይ አስቀመጠውና፥ 16 “ከእኔ ጋር
ሆነህ እኔ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ታማኝ
እንደሆንሁ ራስህ ተመልከት” አለው፤ አብረ
ውም እየጋለቡ ወደ ሰማርያ ሄዱ ። 17 እዚያም
በደረሱ ጊዜ ዒሁ አንድም ሳያስቀር የአክአብን
ዘመዶች በሙሉ ፈጀ፤ ይህም ሁሉ የሆነው
እግዚአብሔር በነቢዩ በኤልያስ አማካይነት በተ
ናገረው ቃል መሠረት ነበር ።

### ባዓል ተብሎ የሚጠራውን
### ጣዖት የሚያመልኩ ተገደሉ

18 ዒሁ የሰማርያን ሕዝብ በአንድነት ጠርቶ
እንዲህ አላቸው፥ “ንጉሥ አክአብ ባዓልን ያገ
ለገለው በመጠኑ ነበር፤ እኔ ግን ከእርሱ ይበ
ልጥ ላገለግለው እፈልጋለሁ፤ 19 ስለዚህም የባዓ
ልን ነቢያት በሙሉ፥ ባዓልን የሚያመልኩት
ንና ካህናቱን ጭምር በአንድነት ጠርታችሁ
በብሰቡልኝ፤ በምንም ምክንያት የሚቀር አይ
ኑር፤ ምክንያቱም እኔ ለባዓል ታላቅ መሥዋ
ዕት ስለማቀርብ በዚያ የማይገኝ ማንም ሰው
ቢኖር በሞት ይቀጣል ።” ይህም ሁሉ ባዓልን
የሚያመልኩትን ሁሉ ለመግደል ዒሁ የፈጠ
ረው የተንኰል ዘዴ ነበር ። 20 ከዚህም በኋላ
ዒሁ “ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ጣዖት የአንድ
ቀን ክብረ በዓል ይደረግ!” ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤
ይህም በዐዋጅ ተነገረ፤ 21 ዒሁም በእስራኤል
ምድር ሁሉ መልእክት አስተላለፈ፤ ባዓልን
የሚያመልኩ ሁሉ ተሰበሰቡ፤ አንድም እንኳ
የቀረ ሰው አልነበረም፤ ሁሉም ወደ ባዓል ቤተ
መቅደስ ገብተው ዳር እስከ ዳር ሞሉት፤
22 ከዚህም በኋላ ዒሁ የተቀደሱ አባላት ኀላፊ

10፥11 ፦ ሆሴዕ 1፥4 ።

የሆነውን ካህን አልባሳቱን ሁሉ አውጥቶ ለባዓል
አምላኪዎች ያጐናጽፋቸው ዘንድ አዘዘ። 23ከዚ
ህም በኋላ ዬሁ ራሱ የሬካብ ልጅ ከሆነው ከኢ
ዮናዳብ ጋር አብሮ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ፤ በዚ
ያም ለሕዝቡ "እንግዲህ በዚህ የሚገኙት የባዓል
አምላኪዎች ብቻ መሆናቸውንና እግዚአብሔ
ርን የሚያመልክ አንድም አለመኖሩን በሚገባ
አረጋግጡ" ሲል ተናገረ፤ 24ወዲያውም እርሱና
ኢዮናዳብ ለባዓል የሚቃጠል መሥዋዕትና
ሌላም ልዩ ልዩ መሥዋዕት ለማቅረብ ገቡ፤ ከዚ
ህም ቀደም ብሎ ዬሁ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ
ሰማኒያ ወታደሮች በማሰለፍ "እነዚህን ሁሉ
ሕዝብ እንድትገድሉ! ከእነርሱ አንድ ሰው
እንኳ እንዲያመልጥ የሚያደርግ ማንም ሰው
ቢኖር በዚያ ሰው ምትክ እርሱ ራሱ ይገደላል!"
ሲል መመሪያ ሰጥቶአቸው ነበር።
25ዬሁ መሥዋዕቱን አቅርቦ እንዳበቃ ወዲያ
ውኑ ለዘብ ጠባቂዎችና ለጦር መኰንኖች "ገብ
ታችሁ እነዚህን ሁሉ ግደሉ፤ አንድም ሰው
እንዳያመልጥ!" ሲል አዘዛቸው፤ እነርሱም
ሰይፍ ሰይፋቸውን በመምዘዝ ገብተው ሁሉንም
ገደሉ፤ ሬሳቸውንም ሁሉ እየጐተቱ ወደ
ውጭ አወጡት፤ ከዚህም በኋላ ወደ ቤተ መቅ
ደሱ ውስጠኛ ክፍል ገብተው፥ 26በዚያ ያመል
ኩት የነበረውን የድንጋይ ዐምድ ወደ ውጭ
አውጥተው በእሳት አቃጠሉት፤ 27በዚህም ዐይ
ነት ሁኔታ የተቀደሰውን የድንጋይ ዐምድና
ቤተ መቅደሱን አፈራረሱ፤ ቤተ መቅደሱንም
መጸዳጃ አደረጉት፤ ዛሬም በዚሁ ዐይነት ይገ
ኛል። 28ዬሁ በእስራኤል የነበረውን የባዓልን
ጣዖታዊ አምልኮ ያስወገደው በዚህ ዐይነት ዘዴ
ነበር፤ 29ነገር ግን ዬሁ እስራኤልን ወደ ኃጢ
አት የመራውን የንጉሥ ኢዮርብዓምን የኃጢ
አት መንገድ ከመከተል አልተገታም፤ ምክንያ
ቱም ዬሁ ራሱ ቀደም ሲል ኢዮርብዓም በቤት
ኤልና በዳን ላቆማቸው የወርቅ ጥጃ ምስሎች
መስገዱ አልቀረም። 30ይሁን እንጂ እግዚአብ
ሔር ዬሁን "በአክአብ ዘሮች ሁሉ ላይ
ልታደርግ የሚገባህን ባዘዝኩህ መሠረት ፈጽመ
ሃል፤ ከዚህም የተነሣ የአንተ ዝርያዎች እስከ
አራት ትውልድ ድረስ በእስራኤል ላይ እንደሚ
ነግሡ የተስፋ ቃል እሰጥሃለሁ" አለው።
31ዬሁ ግን የእስራኤል አምላክ ለሆነው ለእግዚ
አብሔር ሕግ በፍጹም ልቡ ታዛዥ ሆኖ አልተ
ገኘም፤ ይህን በማድረግ ፈንታ እስራኤልን ወደ
ኃጢአት የመራቸውን የኢዮርብዓምን ክፉ አር
አያነት ተከተለ።

### የዬሁ መሞት

32በዚያም ዘመን እግዚአብሔር የእስራኤል
ግዛት ስፋቱ እንዲቀነስ ማድረግ ጀመረ፤ የሶርያ
ንጉሥ ሐዛኤል እስራኤልን ድል ነሥቶ የእስራ
ኤልን ግዛት ሁሉ ያዘ። 33እርሱም የያዘው
ግዛት፥ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ፥
በስተ ደቡብ በኩል ከአርኖን ወንዝ በላይ እስከ
ምትገኘው እስከ ዓሮዔር ከተማ የሚደርስ
ሲሆን፥ ይህም የጋድ፥ የሮቤልና በምሥራቅ
የሚገኘው የምናሴ ነገድ እኩሌታ ይኖሩባቸው
የነበሩትን የገለዓድንና የባሳንን ግዛቶች ያጠቃል
ላል።
34ዬሁ ያደረገው ሌላው ነገርና የጀግንነት
ሥራውም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ
መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል፤ 35ከዚህም በኋላ
ዬሁ ሞተ፤ በሰማርያም ተቀበረ፤ በእርሱም
እግር ተተክቶ ልጁ ኢዮአካዝ ነገሠ፤ 36ዬሁ
መኖሪያውን በሰማርያ በማድረግ በእስራኤል
ላይ የነገሠበት ዘመን ሃያ ስምንት ዓመት
ነበር።

## ምዕራፍ 11

### የይሁዳ ንግሥት ዐታልያ (ጎቶሊያ)
(2 ዜ.መ. 22፥10-23፥15)

1የንጉሥ አካዝያስ እናት ዐታልያ የልጅዋን
መገደል እንደሰማች ወዲያውኑ የይሁዳ ንጉሣ
ውያን ቤተሰብ አባላት በሙሉ እንዲገደሉ ትእ
ዛዝ ሰጠች። 2ከእርስዋም እጅ ማምለጥ የቻለ
የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ ብቻ ነበር፤ እርሱም
እንኳ ከሌሎቹ ጋር እንዲገደል ተመክሮበት
ነበር፤ ነገር ግን አክስቱ የነበረችው በእባትዋ
በኩል የንጉሥ አካዝያስ እኅት የሆነችው፥ የን
ጉሥ ኢዮራም ልጅ ይሆሼባዕ በመደበቅ ከሞት
ታደገችው፤ እርስዋም እርሱንና ሞግዚቱን
ወስዳ በቤተ መቅደስ ውስጠኛ መኝታ ክፍል
ውስጥ ስለደበቀችው በዐታልያ እጅ ሳይገደል
ቀረ። 3ዐታልያ በነገሠችበትም ስድስት ዓመት
ጊዜ ውስጥ፥ ይሆሼባዕ ሕፃኑን ኢዮአስን በመከ
ባከብ አሳደገችው።
4ነገር ግን በሰባተኛው ዓመት ካህኑ ዮዳሄ
ስንጉሡ ክብር ዘቦችና ለቤተ መንግሥቱ ጠባቂ
ዎች ሁሉ ኀላፊዎች ወደሆኑት የጦር መኰን
ኖች ሁሉ ልኮ ወደ ቤተ መቅደስ እንዲመጡ
አስጠራቸው፤ በዚያም ሊያደርገው ያቀደውን
ይስማሙበት ዘንድ በመሐላ እንዲያረጋግጡለት
አደረገ፤ ከዚያም በኋላ የአካዝያስን ልጅ ኢዮአ
ስን አሳያቸውና፥ 5የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጣ
ቸው፥ "በሰንበት ቀን ለዘብ ጥበቃ በምትሠማሩ
በት ጊዜ ከእናንተ ከሦስት እንዱ እጅ ቤተ
መንግሥቱን ይጠብቅ፤ 6ሌላው አንድ ሦስተኛ
እጅ የሱርን የቅጽር በር ይጠብቅ፤ የቀረው ሦስ
ተኛ እጅ ደግሞ ከሌሎቹ ዘቦች በስተኋላ ያለ
ውን ቅጽር በር ይጠብቅ። 7በሰንበት ቀን ከዘብ
ጥበቃ ነፃ የሆኑት ሁለቱ ቡድኖች ግን ለንጉሡ

10፥29 ፦ 1ነገ. 12፥28-30።

የምትቀበሉትን ገንዘብ መያዝ የለባችሁም ፤
ለቤተ መቅደሱ እድሳት ይውል ዘንድ ገንዘቡን
አስረክቡ” አላቸው ። 8 ካህናቱም በዚህ ተስማ
ምተው ቤተ መቅደሱን ለማደስ የነበራቸውን
ተግባር አቆሙ ።
9 ከዚህ በኋላ ዮዳሄ አንድ ሣጥን ወስዶ በመ
ክደኛው ላይ ቀዳዳ አበጀ ፤ ሣጥኑንም ወስዶ
ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ በስተ ቀኝ በሚገኘው
መሠዊያ አጠገብ አኖረው ፤ የየዕለቱ ተረኞች
የነበሩትም ካህናት ለስግደት የሚመጡት
ሕዝብ የሚሰጡትን የገንዘብ መባ እየተቀበሉ
በሣጥኑ ውስጥ ያስገቡት ነበር ፤ 10 ሣጥኑም
በሚሞላበት ጊዜ የቤተ መንግሥቱ ጸሐፊና
ሊቀ ካህናቱ እየመጡ ብሩን በመቍጠር በከረ
ጢት እያሰሩ ያኖሩት ነበር ። 11 ትክክለኛው
ንም ሒሳብ አጣርተው ከመዘገቡ በኋላ ለቤተ
መቅደሱ እድሳት ሥራ ኀላፊዎች ያስረክቡ
ነበር ፤ እነርሱም ገንዘቡን ተረክበው ለአናጢ
ዎች ፥ ለግንበኞች ፥ 12 ለድንጋይ ጠራቢዎች ፥
ለማደሻ አገልግሎት የሚውል እንጨትና ድን
ጋይ ለሚገዙና እንዲሁም ለልዩ ልዩ አስፈላጊ
ነገሮች ለሚውል ተግባር ሁሉ ይከፍሉ ነበር ።
13 ሆኖም ከብር ለሚሠሩ ጽዋዎች ፥ ድስቶችና
መስኮቶች ወይም ለመብራት መኮስተሪያዎች
ወይም ደግሞ ከብርም ሆነ ከወርቅ ለሚሠሩ
ንዋያተ ቅድሳት ከዚያ ገንዘብ ላይ ተነሥቶ
የሚከፈል ሒሳብ አልነበረም ። 14 ያ ገንዘብ
በሙሉ በቤተ መቅደሱ እድሳት ተግባር ላይ
ለተሠማሩት ሠራተኞችና ለልዩ ልዩ ዕቃዎች
መግዣ ብቻ የሚውል ነበር ። 15 ለሥራው
ኀላፊነት የተመረጡትም ሰዎች ፍጹም ታማ
ኞች ስለነበሩ ፥ ስለ ገንዘቡ አወጣጥ ቍጥጥር
ማድረግ አስፈላጊ አልነበረም ። 16 ስለ በደልና
ስለ ኃጢአት መሥዋዕት የሚከፈለው ገንዘብ
ግን ለካህናቱ ጥቅም የሚውል እንጂ ወደ ቤተ
መቅደሱ እድሳት ሣጥን ውስጥ አይገባም
ነበር ።
17 በዚያን ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ሐዛኤል በጋት
ከተማ ላይ አደጋ ጥሎ ያዛት ፤ ቀጥሎም በኢየሩ
ሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል ወሰነ ። 18 የይሁዳ
ንጉሥ ኢዮአስም ከእርሱ በፊት የነበሩትን ነገ
ሥታት ፥ ማለትም ኢዮሣፍጥ ፥ ኢዮራምና አካ
ዝያስ ለእግዚአብሔር ለይተው ያኖሩትን መባና
የራሱን መባ ጨምሮ በቤተ መቅደስና በቤተ
መንግሥት ግምጃ ቤቶች የነበረውን ወርቅ ሁሉ
በመሰብሰብ ገጸ በረከት አድርጎ ለንጉሥ ሐዛ
ኤል ላከለት ፤ ሐዛኤልም ይህን ተቀብሎ ሠራዊ
ቱን ከኢየሩሳሌም መለሰ ።
19 ንጉሥ ኢዮአስ ያደረገው ሌላው ነገር
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ
ተመዝግቦ ይገኛል ።
20-21 ከዚህ በኋላ የንጉሥ ኢዮአስ ባለሟ
ሎች የሆኑ ባለሥልጣኖች አደሙበት ፤ ከእነር
ሱም ሁለቱ የሺምዓት ልጅ ዮዛካርና የሾሜር
ልጅ ይሆዛባድ ወደ ሲላ በሚወስደው ከኢየሩሳ
ሌም በስተ ምሥራቅ በሚገኘው በተደለደለ
መሬት ላይ በተሠራው ቤት ገደሉት ፤ ኢዮአ
ስም በዳዊት ከተማ በሚገኘው በነገሥታት
መካነ መቃብር ተቀበረ ፤ በእርሱም እግር ተተ
ክቶ ልጁ አሜስያስ ነገሠ ።

## ምዕራፍ 13

### የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ

1 የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በይሁዳ በነገሠ
በሃያ ሦስተኛው ዓመት የዩሁ ልጅ ኢዮአካዝ
የእስራኤል ንጉሥ ሆነ ፤ መኖሪያውንም በሰማ
ርያ አድርጎ ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ ፤ 2 እር
ሱም ከእርሱ በፊት እንደነበረው እንደ ንጉሥ
ኢዮርብዓም ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔ
ርን አሳዘነ ፤ እስራኤልንም ወደ ኃጢአት
መራ ፤ ከክፉ ሥራውም ከቶ አልተገታም ።
3 ስለዚህም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቈ
ጥቶ የሶርያ ንጉሥ ሐዛኤልና የእርሱ ልጅ ቤን
ሀዳድ በየጊዜው ተነሥተው በተከታታይ ድል
እንዲነሡአቸው ፈቀደ ። 4 ከዚህ በኋላ ኢዮአ
ካዝ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም
የሶርያ ንጉሥ በእስራኤላውያን ላይ የፈጸመባ
ቸው ግፍ እጅግ ከባድ መሆኑን ተመልክቶ የኢ
ዮአካዝን ጸሎት ሰማ ። 5 ስለዚህም እግዚአብ
ሔር እስራኤልን ከሶርያውያን እጅ ነፃ የሚያወ
ጣቸው መሪ ላከላቸው ፤ እነርሱም ከዚያ በፊት
በነበረው ዐይነት በሰላም ኖሩ ። 6 ይህም ሁሉ
ሆኖ ንጉሥ ኢዮርብዓም እስራኤልን ወደ ኃጢ
አት ከመራበት ከበደል ሥራቸው አልተመለ
ሱም ፤ ይህን በማድረግ ፈንታ በኃጢአታቸው
ጸንተው አሼራ ተብላ የምትጠራውን የሴት
አምላክ ምስል በሰማርያ ማምለክ ቀጠሉ ።
7 ንጉሥ ኢዮአካዝ ከኀምሳ ፈረሰኞች ፥ ከዐ
ሥር ሠረገላዎችና ከዐሥር ሺ ወታደሮች በቀር
ሌላ የተደራጀ የጦር ኀይል አልነበረውም ፤
ይህም የሆነበት ምክንያት ሌላውን ሠራዊቱን
የሶርያ ንጉሥ እንደ ትቢያ ረግጦ ስለደመሰሰ
በት ነው ።
8 ንጉሥ ኢዮአካዝ የፈጸመው ሌላው ተግባ
ርና የጀግንነት ሥራው ሁሉ በእስራኤል ነገሥ
ታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል ፤
9 ኢዮአካዝ ሞተ ፤ በሰማርያም ተቀበረ ፤ በእር
ሱም እግር ተተክቶ ዮአስ ነገሠ ።

### የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ

10 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ በነገሠ በሠላሳ ሰባ
ተኛው ዓመት የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ የእስራኤል

12፥15 ፡- 2ነገ. 22፥7 ። 12፥16 ፡- ዘሌ. 7፥7 ።

ንጉሥ ሆነ ፤ መኖሪያውንም በሰማርያ አድርጎ
ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ ። 11 እርሱም እስራኤ
ልን ወደ ኃጢአት የመራ የንጉሥ ኢዮርብዓምን
መጥፎ ምሳሌነት በመከተል ኃጢአት በመሥራቱ
እግዚአብሔርን አሳዘነ ። 12 ዮአስ የፈጸመው
ሌላው ነገር ሁሉ እንዲሁም በይሁዳ ንጉሥ አሜ
ስያስ ላይ ባደረገው ጦርነት የፈጸመው ጀግንነት
ጭምር በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ
ተመዝግቦ ይገኛል ። 13 ከዚህ በኋላ ዮአስ ሞተ ፤
በሰማርያም በሚገኘው መካነ መቃብር ተቀበረ ፤
በእርሱም እግር ተተክቶ ልጁ ዳግማዊ ኢዮርብ
ዓም ነገሠ ።

### የኤልሳዕ መሞት

14 ነቢዩ ኤልሳዕ በብርቱ ደዌ ታሞ ነበር ፤
ተኝቶም ሊሞት በሚያጣጥርበት ጊዜ የእስራ
ኤል ንጉሥ ዮአስ ሊጠይቀው ሄዶ ፤ ድምፁን
ከፍ በማድረግ “አቤቱ ሆይ! አቤቱ ሆይ!
አንተ እኮ የእስራኤል ሕዝብ ኀይላቸውና ጋሻ
መከታቸው ነህ!” እያለ አለቀሰለት ።
15 ኤልሳዕም ንጉሡን “አንድ ቀስትና ፍላጻ
ዎች አምጣ” ሲል አዘዘው ፤ ዮአስም እንደታዘ
ዘው አመጣ ፤ 16 ኤልሳዕም “ፍላጻዎቹን ለማስ
ፈንጠር ተዘጋጅ!” አለው ፤ ንጉሡም እንደታዘ
ዘው አደረገ ፤ ኤልሳዕም እጆቹን በንጉሡ እጆች
ላይ አኖረ ፤ 17 ከዚያም በኋላ ንጉሡ የኤልሳዕን
መመሪያ በመከተል ወደ ሶርያ አቅጣጫ የሚያ
ሳየውን መስኮት ከፈተ ፤ ኤልሳዕም “ፍላጻውን
አስፈንጥር!” አለው ፤ ንጉሡም በፍጥነት ፍላጻ
ውን እንዳስፈነጠረ ወዲያውኑ ኤልሳዕ “አንተ
የእግዚአብሔር ፍላጻ ነህ! በአንተም አማካይ
ነት እግዚአብሔር ሶርያውያንን ድል ያደር
ጋል ፤ ሶርያውያንን ድል እስከትነሣቸው ድረስ
በአፌቅ ከተማ ትወጋቸዋለህ ።”
18 ከዚህም በኋላ ኤልሳዕ ንጉሡን “ሌሎቹ
ንም ፍላጻዎች አንሥተህ በእነርሱ ምድርን
ምታ!” አለው ። ንጉሡም ምድርን ሦስት ጊዜ
መትቶ አቆመ ፤ 19 ይህም ኤልሳዕን አስቈጣው ፤
ስለዚህም ንጉሡን “አምስት ወይም ስድስት
ጊዜ መትተህ ቢሆን ኖሮ በሶርያውያን ላይ
ፍጹም ድልን ትቀዳጅ ነበር ፤ አሁን ግን ሦስት
ጊዜ ብቻ ድል ትነሣቸዋለህ አለው ።”
20 ኤልሳዕም ሞተ ፤ ተቀበረም ።
ከሞአብ የሚመጡ አደጋ ጣዮች በየዓመቱ
የእስራኤልን ምድር ይወርሩ ነበር ፤ 21 አንድ
ጊዜ ሥርዓተ ቀብር በሚፈጽምበት ሰዓት ከእነ
ዚያ አደጋ ጣዮች መካከል አንድ ቡድን ሲመጣ
ስለታየ ፥ የሚቀበረውን ሬሳ ወደ ኤልሳዕ መቃ
ብር ውስጥ በመወርወር ጥለውት ሸሹ ፤ ያም
ሬሳ ከኤልሳዕ አስከሬን ጋር በተገናኘበት ቅጽ
በት ወዲያውኑ ከሞት ተነሥቶ ቆመ ።

### በእስራኤልና በሶርያ መካከል የተደረገ ጦርነት

22 ኢዮአካዝ በነገሠበት ዘመን ሁሉ የሶርያ
ንጉሥ ሐዛኤል እስራኤላውያንን በመጨቈን
ያስጨንቃቸው ነበር ፤ 23 እግዚአብሔር ግን
በቸርነቱ ምሕረትን በማድረግ ረዳቸው እንጂ
እንዲደመሰሱ አልፈቀደም ፤ ይህንንም ያደረገ
በት ምክንያት ለአብርሃም ፥ ለይስሐቅና ለያዕ
ቆብ የሰጠውን ቃል ኪዳን በማስብ ሕዝቡን ስላ
ልረሳቸው ነው ።
24 የሶርያ ንጉሥ ሐዛኤል በሞተ ጊዜ ፥ በእ
ርሱ እግር ተተክቶ ልጁ ቤንሀዳድ ነገሠ ።
25 ከዚህም በኋላ የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ቤንሀ
ዳድን ሦስት ጊዜ ድል ነሥቶ በአባቱ በኢዮአ
ካዝ ዘመነ መንግሥት ቤንሀዳድ ይዞአቸው የነበ
ሩትን ከተሞች አስመለሰ ።

## ምዕራፍ 14

### የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ
(2 ዜ.መ. 25፥1-24)

1 የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በእስራኤል ላይ በነ
ገሠ በሁለተኛው ዓመት የኢዮአስ ልጅ አሜስ
ያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ ፤ 2 በነገሠም ጊዜ ዕድ
ሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር ፤ መኖሪያው
ንም በኢየሩሳሌም አድርጎ ሃያ ዘጠኝ ዓመት
ገዛ ፤ እናቱም ይሆዓዲን ተብላ የምትጠራ የኢየ
ሩሳሌም ሴት ነበረች ። 3 አሜስያስ እግዚአብሔ
ርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርቶአል ፤ ይሁን
እንጂ እንደ ቀድሞ አያቱ እንደ ንጉሥ ዳዊት
አልነበረም ፤ እንደ ዳዊት በመሆን ፈንታ የአባ
ቱን የኢዮአስን ፈለግ ተከተለ ። 4 ይኸውም በየ
ኮረብታዎች ላይ የተሠሩትን አረማውያን ማምለ
ኪያዎችን አላፈረሰም ፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ
በየኮረብታዎቹ መሥዋዕት ማቅረባቸውንና
ዕጣን ማጠናቸውን እንደቀጠሉ ነበር ።
5 አሜስያስ መንግሥቱን አደላድሎ እንደያዘ
ወዲያውኑ ፥ ቀደም ሲል ንጉሥ የነበረውን አባ
ቱን የገደሉትን ባለሥልጣኖች በሞት ቀጣ ፤
6 ይሁን እንጂ ልጆቻቸውን አልገደለም ፤ ይልቁ
ንም በሙሴ ሕግ እግዚአብሔር “ልጆቻቸው
በፈጸሙት ኃጢአት ወላጆች በሞት አይቀጡበ
ትም ፤ ወላጆችም በፈጸሙት ኃጢአት ልጆች
በሞት አይቀጡበትም ፤ እያንዳንዱ ሰው ራሱ
በፈጸመው ወንጀል ብቻ በሞት ይቀጣ” ሲል
የሰጠውን ትእዛዝ ፈጽሞአል ።
7 አሜስያስ “የጨው ሸለቆ” እየተባለ በሚ
ጠራው ስፍራ ዐሥር ሺ የሚሆኑ የኤዶም ወታ
ደሮችን ፈጀ ፤ ሴላዕ ተብላ የምትጠራውንም
ከተማ ይዞ “ዮቅትኤል” ብሎ ጠራት ፤ እስከ
አሁንም በዚሁ ስም ትጠራለች ።

13፥14 ፦ 2ነገ. 2፥12 ። 14፥6 ፦ ዘዳ. 24፥16 ።

ዓመት ገዛ ፤ እናቱም ይኮልያ ተብላ የምትጠራ
የኢየሩሳሌም ተወላጅ ነበረች ። 3 እርሱም የአባ
ቱን መልካም አርአያነት በመከተል እግዚአብ
ሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠራ ፤ 4 ነገር ግን
በየኮረብታዎች ላይ የነበሩትን አረማውያን የማ
ምለኪያ ቦታዎች አልደመሰሰም ፤ ስለዚህም
ሕዝቡ በየኮረብታዎች ላይ መሥዋዕት ማቅረባ
ቸውንና ዕጣን ማጠናቸውን እንደቀጠሉ ነበር ፤
5 በኋላም እግዚአብሔር በዖዝያን ላይ አሠቃቂ
የሆነ የቆዳ በሽታ አሳደረበት ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ
ድረስ ይህ በሽታ ስላልለቀቀው ከሥራው ሁሉ
ተገልሎ በተለየ ቤት ውስጥ ለብቻው ይኖር
ነበር ፤ በዚህም ጊዜ መንግሥቱን ሲመራ የቆ
የው ልጁ ኢዮአታም ነበር ።
6 ንጉሥ ዖዝያን ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ
ተመዝግቦ ይገኛል ። 7 ዖዝያን ሞተ ፤ በዳዊት
ከተማ በሚገኘው በቀድሞ አባቶቹ መካነ መቃ
ብር ተቀበረ ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ ልጁ
ኢዮአታም ነገሠ ።

### የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ

8 ዖዝያን በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ ስምንተ
ኛው ዓመት የዳግማዊ ኢዮርብዓም ልጅ ዘካር
ያስ በእስራኤል ነገሠ ፤ መኖሪያውንም በሰማርያ
አድርጎ ስድስት ወር ገዛ ፤ 9 እርሱም ከእርሱ
በፊት እንደነበሩት ነገሥታት ሁሉ ኃጢአት
በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ ፤ እንዲሁም
እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የናባጥ ልጅ
የንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአያነት ተከ
ተለ ፤ 10 ሻሉም ተብሎ የሚጠራው የያቤሽ
ልጅ ሤራ በማድረግ ዩብለዓም ተብላ በምትጠ
ራው ስፍራ ንጉሥ ዘካርያስን ገድሎ በእርሱ
እግር ነገሠ ።
11 ንጉሥ ዘካርያስ ያደረገው ሌላው ነገር
ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ
ተመዝግቦ ይገኛል ።
12 በዚህም ዐይነት ሁኔታ እግዚአብሔር ለን
ጉሥ ዩሁ "ዘርያዎችህ እስከ አራት ትውልድ
በእስራኤል ይነግሣሉ" ሲል የተናገረው የተስፋ
ቃል ተፈጸመ ።

### የእስራኤል ንጉሥ ሻሉም

13 ዖዝያን በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው
ዓመት የያቤሽ ልጅ ሻሉም የእስራኤል ንጉሥ
ሆነ ፤ መኖሪያውንም በሰማርያ አድርጎ አንድ
ወር ብቻ ገዛ ።
14 ምናሔም ተብሎ የሚጠራው የጋዲ ልጅ
ከቲርጻ ተነሥቶ ወደ ሰማርያ ሄደ ፤ ሻሉምንም
ገድሎ በእርሱ እግር ነገሠ ። 15 ሻሉም ያደረ
ገው ሌላው ነገር ሁሉ ፥ እንዲሁም እርሱ የጠነ
ሰሰው ሤራ ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ
መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል ። 16 ምናሔም ከቲ
ርጻ ተነሥቶ በሚያልፍበት ጊዜ እግረ መንገ
ዱን የቲፍሳሕን ከተማ ፥ ነዋሪዎችዋንና በዙሪ
ያዋ የነበረውን ግዛት ሁሉ ደመሰሰ ፤ ይህንንም
ያደረገበት ምክንያት የከተማይቱ ነዋሪዎች ለእ
ርሱ እጃቸውን ለመስጠት ባለማፍቀዳቸው
ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ ነፍሰ ጡሮችን እንኳ
ሳይምር ሆዳቸውን ቀደደ ።

### የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም

17 ዖዝያን በይሁዳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው
ዓመት የጋዲ ልጅ ምናሔም በእስራኤል ነገሠ ፤
መኖሪያውን በሰማርያ አድርጎ ዐሥር ዓመት
ገዛ ። 18 እስከ ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ እስራኤ
ልን ወደ ኃጢአት የመራ የናባጥ ልጅ ኢዮርብ
ዓምን መጥፎ አርአያነት በመከተል ኃጢአት
በመሥራቱም እግዚአብሔርን አሳዘነ ። 19 የአ
ሦር ንጉሥ ነገሥት ቲግላት ፐሌሴር እስራኤ
ልን ወረረ ፤ ምናሔም በአገሩ መንግሥት ላይ
ሥልጣኑን እንዲያጸናለትና እንዲደግፈው ለመ
ማጸን ሠላሳ አራት ሺ ኪሎ የሚመዝን ብር
እጅ መንሻ አድርጎ ለቲግላት ፐሌሴር ሰጠው ።
20 ምናሔም ገንዘቡን የሰበሰበው የእስራኤል ክበ
ርቴዎች እያንዳንዳቸው ኀምሳ ጥሬ ብር አዋጥ
ተው እንዲሰጡ በማስገደድ ነበር ። በዚህም ዐይ
ነት ሁኔታ ቲግላት ፐሌሴር በሰላም ወደ አገሩ
ተመልሶ ሄደ ።
21 ምናሔም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእ
ስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ
ይገኛል ፤ 22 ምናሔም ሞተ ፤ ተቀበረም ፤ በእር
ሱም እግር ተተክቶ ልጁ ፈቃሕያ ነገሠ ።

### የእስራኤል ንጉሥ ፈቃሕያ

23 ዖዝያን በይሁዳ በነገሠ በኀምሳኛው
ዓመት የምናሔም ልጅ ፈቃሕያ በእስራኤል
ነገሠ ፤ መኖርያውንም በሰማርያ አድርጎ ሁለት
ዓመት ገዛ ፤ 24 እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ
የናባጥ ልጅ ንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ አርአ
ያነት በመከተል ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔ
ርን አሳዘነ ። 25 ከፈቃሕያ ሠራዊት መካከል
ሩቁሔ ተብሎ የሚጠራ የረማልያ ልጅ የሆነ
አንድ የጦር መኰንን ከኀምሳ የገለዓድ ሰዎች
ጋር ሆኖ ሤራ ጠንስስ ፤ በሰማርያ በቤተ መንግ
ሥቱ ውስጥ በሚገኘው ምሽግ ውስጥ ዘልቆ
በመግባትም ፈቃሕያን ከአርጎብና ከሃርዬ ጋር
ገድሎ በፈቃሕያ እግር ተተክቶ ነገሠ ።
26 ፈቃሕያ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በእ
ስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ
ይገኛል ።

15፥7 ፡- ኢሳ. 6፥1 ። 15፥12 ፡- 2ነገ. 10፡30 ።

### የእስራኤል ንጉሥ ፈቁሒ

27 ዖዝያን በይሁዳ በነገሠ በኀምሳ ሁለተ
ኛው ዓመት የረማልያ ልጅ ፈቁሒ በእስራኤል
ነገሠ፤ መኖርያውንም በሰማርያ አድርጎ ሃያ
ዓመት ገዛ። 28 እስራኤልን ወደ ኃጢአት
የመራ የነባጥ ልጅ ንጉሥ ኢዮርብዓምን መጥፎ
አርአያነትን በመከተል ኃጢአት በመሥራት እግዚ
አብሔርን አሳዘነ።
29 የአሦር ንጉሥ ነገሥት ቲግላት ፐሌሴር
ዒዮን፥ አቤልቤትማዕካ፥ ያኖሐ፥ ቄዴሽና
ሐጾር ተብለው የሚጠሩትን ከተሞች፥ እንዲ
ሁም የገለዓድን፥ የገሊላንና የንፍታሌምን ግዛ
ቶች በመውረር ሕዝቡን ወደ አሦር ማርኮ የወ
ሰደውም ፋቁሒ በነገሠበት ዘመን
ነበር።
30 የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም በይሁዳ በነገሠ
በሃያኛው ዓመት የኤላ ልጅ ሆሴዕ በንጉሥ
ፋቁሒ ላይ ሤራ ጠንስሶ፤ እርሱንም ገድሎ በእ
ስራኤል ላይ ነገሠ፤ 31 ፈቁሒ ያደረገው ሌላው
ነገር ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽ
ሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም
(2 ዜ.መ. 27፥1-9)

32 የረማልያ ልጅ ፋቁሒ በእስራኤል በነገሠ
በሁለተኛው ዓመት የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም
የይሁዳ ንጉሥ ሆነ፤ 33 በነገሠም ጊዜ ዕድሜው
ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤ መኖርያውንም በኢ
የሩሳሌም አድርጎ ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ፤
እናቱም የሩሻ ተብላ የምትጠራ የጻዶቅ ልጅ
ነበረች። 34 የአባቱንም የዖዝያን መልካም አርአ
ያነት በመከተል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
ሥራ ሠራ፤ 35 ነገር ግን በየኮረብታዎች ላይ የነ
በሩትን አረማውያን መሠዊያዎችን አላስወገ
ደም፤ ሕዝቡም መሥዋዕት ማቅረባቸውንና
ዕጣን ማጠናቸውን እንደቀጠሉ ነበር፤ የቤተ
መቅደሱን ሰሜናዊ ቅጽር በር ያሠራ ይኸው
ኢዮአታም ነበር።
36 ኢዮአታም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ
ይገኛል። 37 እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሶርያ
ንጉሥ ረጺን፥ ቀጥሎም የእስራኤል ንጉሥ
ፋቁሒ በይሁዳ ላይ አደጋ እንዲጥሉባት የላካ
ቸው ይኸው ኢዮአታም በይሁዳ በነገሠበት
ዘመን ነበር፤ 38 ኢዮአታም ሞተ፤ በዳዊት
ከተማ በሚገኘው የነገሥታት መካነ መቃብር
ተቀበረ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ ልጁ አካዝ
ነገሠ።

## ምዕራፍ 16

### የይሁዳ ንጉሥ አካዝ
(2 ዜ.መ. 28፥1-27)

1 የረማልያ ልጅ ፋቁሒ በእስራኤል በነገሠ
በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት የኢዮአታም ልጅ
አካዝ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ፤ 2 በነገሠም ጊዜ ዕድ
ሜው ሃያ ዓመት ነበር፤ እርሱም መኖሪያውን
በኢየሩሳሌም አድርጎ ዐሥራ ስድስት ዓመት
ገዛ፤ እርሱም የቀድሞ አባቱን የንጉሥ ዳዊትን
መልካም አርአያነት አልተከተለም፤ ይህን በማ
ድረግ ፈንታ አምላኩን እግዚአብሔርን ደስ የማ
ያሰኝ ሥራ ሠራ፤ 3 የእስራኤልንም ነገሥታት
መጥፎ አርአያነት ተከተለ፤ የገዛ ልጁን እንኳ
ሳይቀር ለጣዖታት የሚቃጠል መሥዋዕት አድ
ርጎ አቀረበ፤ ይህንንም የፈጸመው የእስራኤል
ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ አገር ለመግባት ወደፊት
እየገፋ በመጡ ጊዜ እግዚአብሔር ከዚያች
ምድር ነቃቅሎ ያስወገዳቸው አረማውያን
ሕዝብ ይሠሩት የነበረውን አስጸያፊ ድርጊት
በመከተል ነው። 4 አካዝ በየኮረብታዎች ላይ
በተሠሩት አረማውያን ማምለኪያ ስፍራዎችና
በእያንዳንዱም ዛፍ ሥር መሥዋዕት በማቅረብ
ዕጣን አጠነ።
5 የሶርያ ንጉሥ ረጺንና የእስራኤል ንጉሥ
ፋቁሒ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ በመጣል ከበቡ
አት፤ ነገር ግን አካዝን ድል ሊያደርጉት አል
ቻሉም። 6 በዚያን ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ረጺን
የኤላትን ከተማ አስመልሶ በቍጥጥሩ ሥር በማ
ድረግ በዚያ የነበሩትን አይሁዳውያን አስወጣ፤
ያን ጊዜ በኤላት የሰፈሩት ኤዶማውያን እስከ
አሁን በዚያ ይገኛሉ። 7 ከዚህም የተነሣ ንጉሥ
አካዝ ወደ አሦር ንጉሠ ነገሥት ወደ ቲግላት
ፐሌሴር “እኔ ለአንተ ታማኝ አገልጋይህ ነኝ፤
ስለዚህም ወደ እኔ መጥተህ አደጋ ከጣሉብኝ
ከሶርያና ከእስራኤል ነገሥታት እጅ በመታደግ
አድነኝ” የሚል ጥያቄ የያዙ መልእክተኞች
ላከ። 8 ከዚህም በቀር አካዝ በቤተ መቅደስና
በቤተ መንግሥቱ ዕቃ ግምጃ ቤት ሰብስቦ
ለዚሁ ለአሦር ንጉሥ ገጸ በረከት በማድረግ ላከ
ለት። 9 የአካዝን ጥያቄ በመቀበል ቲግላት ፐሌ
ሴር ወዲያውኑ ዘምቶ ደማስቆን በቍጥጥሩ
ሥር አደረገ፤ ንጉሥ ረጺንንም ገደለ፤ ሕዝቡ
ንም ማርኮ ቂር ተብላ ወደምትጠራው ስፍራ
ወሰዳቸው።
10 ንጉሥ አካዝ ወደ ደማስቆ ሄዶ ከንጉሠ
ነገሥት ቲግላት ፐሌሴር ጋር በተገናኘ ጊዜ
በዚያ አንድ መሠዊያ አየ፤ ያንን መሠዊያ በተ
መሳሳይ ሁኔታ መሥራት የሚያስችለውን ቅርጽ
አዘጋጅቶ ለካህኑ ለኡሪያ ላከለት፤ 11 ስለዚህም
ኡሪያ ንጉሥ አካዝ ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት

---

16፥3 ፦ ዘዳ. 12፥31። 16፥5 ፦ ኢሳ. 7፥1።

ል፡ ያንኑ የሚመስል መሠዊያ ሠራ ፤ [12]አካ
ዝም ከደማስቆ በተመለሰ ጊዜ ያ መሠዊያ በት
ክክል መሠራቱን አይቶ በሥነ ሥርዓት በመቅ
ረብ በመሠዊያው ላይ ወጣ ፤ [13]እንዲሁም
በዚያ መሠዊያ ላይ የእንስሳት መሥዋዕትና የእ
ህል መባ አቀረበ ፤ የመጠጡን ወይን ጠጅና ለደ
ኅንነት የሚቀርበውንም የኅብረት መሥዋዕት
ደም አፈሰሰበት ። [14]ከነሐስ ተሠርቶ ለእግዚአ
ብሔር የተለየውም መሠዊያ በዚያ አዲስ መሠ
ዊያና በቤተ መቅደሱ መካከል ነበር ፤ አካዝም
ያንን መሠዊያ አስነሥቶ እርሱ ባሠራው በአ
ዲሱ መሠዊያ በስተ ሰሜን በኩል አኖረው ፤
[15]ከዚህ በኋላ ኡሪያን እንዲህ ሲል አዘዘው ፤
"ይህንን የአኔን ታላቅ መሠዊያ ማለዳ ለሚቀር
በው የሚቃጠል መሥዋዕት ፥ በምሽት ለሚቀር
በውም የእህል መባ ስለ ንጉሡና ስለ ሕዝቡ
የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል
መባ የሚቀርብበትና የሕዝቡ የወይን ጠጅ መባ
የሚፈስበት እንዲሆን አድርግ ፤ የሚሠውትንም
የእንስሳት ደም ሁሉ በእርሱ ላይ አፍስስ ፤ ከነ
ሐስ የተሠራው መሠዊያ ግን እኔ ራሴ የምፈልገ
ውን ነገር የምጠይቅበት እንዲሆን አድርግ ።"
[16]ኡሪያም ንጉሡ እንዳዘዘው አደረገ ።

[17]ንጉሥ አካዝ በቤተ መቅደስ ውስጥ መገ
ልገያ የነበሩትን ከነሐስ የተሠሩ መንኰራኵሮች
ቈርጦ አስወገደ ፤ በእነርሱ ላይ የነበሩትንም
የመታጠቢያ ሳሕኖች ወሰደ ፤ ከነሐስ የተሠራ
ውን የውሃ ማጠራቀሚያ በርሜል ከታች በኩል
ተሸክመውት ከነበሩት ከነሐስ ከተሠሩት ከዐ
ሥራ ሁለት የኮርማ ቅርጾች ጀርባ ላይ አንሥቶ
ከድንጋይ በተሠራ መሠረት ላይ አኖረው ።
[18]አካዝ የአሦርን ንጉሥ ነገሥት ለማስደሰት
ሲል ንጉሣዊ ዙፋን የሚዘረጋበትን ሉዓላዊ
ሰፍራ አስወገደ ፤ ከዚያ በፊት የነበረ ማንኛ
ውም ንጉሥ ወደ ቤተ መቅደስ ይገባበት የነበረ
ውንም ልዩ በር ዘጋ ።

[19]ንጉሥ አካዝ ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ
ይገኛል ፤ [20]አካዝ ሞተ ፤ በዳዊት ከተማ በሚገ
ኘው በነገሥታት መካነ መቃብር ተቀበረ ፤ በእ
ርሱም እግር ተተክቶ ልጁ ሕዝቅያስ ነገሠ ።

## ምዕራፍ 17

### የእስራኤል ንጉሥ ሆሴዕ

[1]አካዝ በይሁዳ በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው
ዓመት የኤላ ልጅ ሆሴዕ በእስራኤል ንጉሥ
ሆነ ፤ መኖሪያውንም በሰማርያ አድርጎ ዘጠኝ
ዓመት ገዛ ፤ [2]እርሱም ኃጢአት በመሥራት
እግዚአብሔርን አሳዘነ ፤ ይሁን እንጂ የእርሱ
በደል ከእርሱ በፊት የነበሩት የእስራኤል ነገሥ
ታት የፈጸሙትን ያህል አልነበረም ፤ [3]የአሦር
ንጉሥ ሻልማንኤሴር ጦርነት በገጠመው ጊዜ
ተሸንፎ እጁን በመስጠት በየዓመቱ ይገብርለት
ጀመረ ። [4]ነገር ግን ከጥቂት ዓመታት በኋላ
ንጉሥ ሆሴዕ ፥ ሶእ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ
ግብጽ ንጉሥ መልእክተኞች በመላክ ይረዳው
ዘንድ ጠየቀ ፤ በየዓመቱ ለአሦር ንጉሥ ይሰ
ጠው የነበረውንም ግብር አቆመ ፤ ሻልማንኤ
ሴር ይህን በሰማ ጊዜ ሆሴዕን አስይዞ ወህኒ ቤት
አስገባው ።

### ሰማርያ ወደቀች

[5]ከዚህ በኋላ ሻልማንኤሴር እስራኤልን በመ
ውረር ሰማርያን ከበበ ፤ ከከበባውም ሦስት
ዓመት በኋላ ፥ [6]ይኸውም ሆሴዕ በነገሠ በዘጠነ
ኛው ዓመት ሻልማንኤሴር ድል አድርጎ ሰማር
ያን ያዘ ፤ እስራኤላውያንንም ማርኮ በእስረኛ
ነት ወደ አሦር ወሰዳቸው ፤ ከእነርሱም ጥቂ
ቶቹ በሐላሕ ከተማ ፥ ጥቂቶቹ በጎዛን አውራጃ
ውስጥ በሚገኘው በሐቦር ወንዝ አጠገብ ፥ እን
ዲሁም ሌሎቹ በሜዶን ከተሞች እንዲሰፍሩ
አደረገ ።

[7]ሰማርያ ወደቀች ፤ ይህም የሆነበት ምክን
ያት እስራኤላውያን በሠሩት ኃጢአት ከግብጽ
ንጉሥ እጅ በመታደግ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ
ምድር የመራቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔ
ርን በማሳዘናቸው ነበር ፤ ይኸውም ለባዕዳን
አማልክት ሰገዱ ፤ [8]ሕዝቡ ወደ ፊት እየገፉ
በመጡ ጊዜ ከፊታቸው ነቃቅሎ ያጠፋላቸውን
የአረማውያን ሕዝብ መጥፎ ልማድ ተከተሉ ፤
እንዲሁም የእስራኤል ነገሥታት ያሰራጩትን
መጥፎ ልማድ ተቀባዮች ሆኑ ። [9]እስራኤላው
ያን አምላካቸው እግዚአብሔር የሚጠላውን
ነገር ሁሉ አደረጉ ፤ ከትንሽ መንደር አንሥቶ
እስከ ትልቅ ከተማ ድረስ በገጠር ከተሞቻቸው
ሁሉ በየኮረብታዎቹ አረማውያን ማምለኪያ
ስፍራዎችን ሠሩ ፤ [10]በኮረብታዎች ሁሉ ላይና
በየዛፉ ጥላ ሥር የድንጋይ ዐምዶችንና አሼራ
ተብላ የምትጠራውን የሴት አምላክ ምስሎች
አቆሙ ፤ [11]እግዚአብሔር ከምድሪቱ ነቃቅሎ
ያስወጣቸውን የአረማውያን ሕዝብ ልማድ በመ
ከተል በአረማውያን መሠዊያዎች ሁሉ ላይ
ዕጣን አጠኑ ፤ በዚህም ክፉ ሥራቸው ሁሉ የእ
ግዚአብሔርን ቊጣ አነሣሡ ፤ [12]እግዚአብሔር
ለጣዖት እንዳይሰግዱ ያዘዛቸውንም ሕግ ሁሉ
አፈረሱ ።

[13]እግዚአብሔርም እስራኤልንና ይሁዳን
የሚያስጠነቅቁ መልእክተኞችንና ነቢያትን
በመላክ "ከክፉ መንገዳችሁ ሁሉ ተመለሱ ፤

16፥14 ፦ ዘጸ. 27፥1-2 ፤ 2ዜ.መ. 4፥1 ። 16፥17 ፦ 1ነገ. 7፥23-39 ፤ 2ዜ.መ. 4፥2-6 ። 16፥20 ፦ ኢሳ. 14፥28 ።
17፥10 ፦ 1ነገ. 14፥23 ።

17 ይህ በዚህ እንዳለ የአሦር ንጉሠ ነገሥት እን
ደገና የተጠናከረ ታላቅ ሠራዊት ከላኪሽ ተንቀ
ሳቅሶ ወደ ኢየሩሳሌም በመዝመት በሕዝቅያስ
ላይ አደጋ እንዲጥልበት አዘዘ፤ ያም ሠራዊት
ከፍተኛ ሥልጣን ባላቸው ሦስት የጦር አዛዥ
ዎቹ የሚመራ ነበር፤ እነርሱም ወደ ኢየሩሳ
ሌም እንደደረሱ ከላይኛው ኵሬ ውሃ በሚተላለ
ፋበት ቦይ አጠገብ ወደ ልብስ አጣቢዎች
መስክ የሚወስደውን መንገድ ያዙ፤ 18 ከዚያም
በኋላ ወደ ሕዝቅያስ መልእክት ላኩበት፤ ሕዝ
ቅያስም ባለሟሎቹ የሆኑ ሦስት ባለሥልጣኖች
ሄደው እንዲገናኙአቸው አዘዘ፤ እነርሱም
የቤተ መንግሥቱ ኀላፊ የሆነ የሒልቂያ ልጅ
ኤልያቄም፥ እንዲሁም የቤተመንግሥት ጸሐፊ
የሆነው ሼብናና የቤተ መዛግብት ኀላፊ የሆ
ነው የአሳፍ ልጅ ዮአሕ ነበሩ፤ 19 ከአሦር
የጦር አዛዥዎች አንዱ እንዲህ አላቸው፥ "ለን
ጉሥ ሕዝቅያስ 'ይህን ያህል የተማመንክበት
ኀይል ምንድን ነው? 20 የቃላት ጋጋታ የጦርነ
ትን ስልትና ኀይል የሚተካ ይመስልሃልን?
ማን ይረዳኛል ብለህ ነው በአሦር ላይ ለማመፅ
ያሰብከው? 21 የግብጽ ንጉሥ ይረዳኛል ብለህ
አስበህ ከሆነ፥ የተቀጠቀጠ ሸምበቆ እንደሚመ
ረኰዝ ሰው መሆንህ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ
ተሰብሮ በንጣሪው እጅህን ያቈስልሃል፤ እንግ
ዲህ የግብጽ ንጉሥ በሚተማመኑበት ሁሉ እን
ዲሁ ነው' ሲል የአሦር ንጉሠ ነገሥት ይጠይቅ
ሃል።"

22 የአሦር የጦር አዛዥ ንግግሩን በመቀጠል
እንደገና እንዲህ አለ፥ "እምላክህ እግዚአብ
ሔር እንደሚረዳህ አድርገህ ታስባለህን? ይህማ
እንዳይሆን፥ አንተ የእግዚአብሔርን የተቀደሱ
ስፍራዎችንና መሠዊያዎችን ደምስሰህ 'የይሁ
ዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ማምለክ የሚገባቸው
ኢየሩሳሌም ውስጥ በሚገኘው በአንድ መሠዊያ
ብቻ ነው' ብለህ ወስነሃል። 23 አሁንም በንጉሠ
ነገሥቱ ስም ለፍልሚያ እጠይቅሃለሁ፤ መጋ
ለብ የሚችሉ በቂ ሰዎች ታገኝ እንደሆን እስቲ
ሁለት ሺ ፈረሶች ልስጥህ! 24 አንተ እኮ እጅግ
በጣም ዝቅተኛ ከሆነው ከአሦር ተራ የጦር
መኰንን ጋር እንኳ መወዳደር አትችልም፤
ግብጻውያን ሠረገላዎችንና ፈረሶችን ይልኩል
ኛል ብለህ የምትጠባበቀውም በዚሁ ምክንያት
ነው። 25 እኔ በአንተ አገር ላይ አደጋ የጣልሁባ
ትና የደመሰስኋት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ
ይመስልሃልን? እግዚአብሔር ራሱ በዚህች
አገር ላይ አደጋ እንድጥልባትና እንድደመስሳት
አዝዞኛል።"

26 ከዚህም በኋላ ኤልያቄምና፥ ሼብና እንዲ
ሁም ዮአሕ ይህን የጦር አዛዥ "ፍቹን ስለምና
ውቅ በሶርያ ቋንቋ እንድትነግረን እንለምንሃ
ለን፤ በቅጽር ላይ ያሉት ሕዝብ ሁሉ በሚሰ
ሙት በዕብራይስጥ ቋንቋ አትናገረን" አሉት።

27 እርሱም "የአሦር ንጉሠ ነገሥት ይህን
ሁሉ ለእናንተና ለንጉሣችሁ ብቻ እንድናገር
የላከኝ መሰላችሁን? ከቶ አይደለም፤ ልክ እንደ
እናንተ ኩሳቸውን ለመብላትና ሽንታቸውን
ለመጠጣት የሚገደዱ ሕዝቡም ጭምር ስለ
ሆኑ፥ እኔ የምናገረውን በቅጽሩ ላይ ያሉት
ሕዝብ ሁሉ እንዲሰሙት ነው" ሲል መለሰላ
ቸው።

28 ከዚህም በኋላ ያ የአሦር ባለሥልጣን
ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመ፤ ድምፁንም
ከፍ አድርጎ በዕብራይስጥ ቋንቋ እንዲህ
እያለ መናገር ጀመረ፥ "የአሦር ንጉሠ ነገ
ሥት የሚነግራችሁን ስሙ፥ 29 በሕዝቅያስ
አትታለሉ፤ እርሱ ሊያድናችሁ ከቶ አይች
ልም፤ 30 ሕዝቅያስ 'በእግዚአብሔር ታመኑ፤
እርሱ ያድናችኋል! ከተማችንም በአሦርያው
ያን ሠራዊት እጅ እንዳትገባ ይከላከልልናል'
እያለ የሚሰብካችሁን አትስሙ፤ 31 ሕዝቅያስ
የሚላችሁን አታዳምጡ፤ የአሦር ንጉሠ ነገ
ሥት ከከተማችሁ ወጥታችሁ እጃችሁን እን
ድትሰጡ አዝዞአችኋል፤ ይህን ብታደርጉ
ሁላችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የወይን ተክሎቻች
ሁን ዘለላና የበለስ ዛፎቻችሁን ፍሬ ትበላላ
ችሁ፤ ከጕድጓዶቻችሁም ውሃ ትጠጣላችሁ፤
32 ይህም ሁሉ የሚሆነው ንጉሠ ነገሥቱ የእ
ናንተን አገር ወደምትመስል ምድር ወስዶ
እስከሚያሰፍራችሁ ድረስ ነው፤ በዚያችም
ምድር ወይን ጠጅ የሚገኝባቸው የወይን
ተክል ቦታዎችና በቂ የእንጀራ እህል የሚመ
ረትባቸው እርሻዎች አሉ፤ ምድሪቱም የወ
ይራ ፍሬና የወይራ ዘይት እንዲሁም ማር
የሞላባት ናት፤ ንጉሠ ነገሥቱ የሚያዛችሁን
ብትፈጽሙ በሕይወት ትኖራላችሁ እንጂ
አትሞቱም፤ ስለዚህ ሕዝቅያስ 'እግዚአብሔር
ይታደጋችኋል' እያለ በመስበክ አያሞኛችሁ፤
33 ለመሆኑ ከሌሎች ሕዝቦች አማልክት
አንዱ እንኳ ከአሦር ንጉሠ ነገሥት እጅ አገ
ሩን ያዳነ ይገኛልን? 34 ታዲያ ይዞ ከሆነ
የሐማትና የአርፋድ አማልክት የት አሉ?
የሰፋርዋይም የሄናዕና የዒዋ አማልክትስ የት
ደረሱ? ከእነርሱ አንዱ እንኳ ሰማርያን
ከእጄ ማዳን ችሎአልን? 35 የእነዚህ ሁሉ
አገሮች አማልክት ከንጉሠ ነገሥታችን እጅ
አገሮቻቸውን ለማዳን የቻሉበት ጊዜ አለን?
ታዲያ እንግዲህ እናንተ 'እግዚአብሔር ኢየሩ
ሳሌምን ያድናታል!' ብላችሁ የምታስቡት
እንዴት ነው?"

36 ሕዝቡም ቀደም ሲል ንጉሥ ሕዝቅያስ
ባዘዛቸው መሠረት አንዲት ቃል ሳይናገሩ ዝም
አሉ፤ 37 ከዚህ በኋላ ኤልያቄምና ሼብና እንዲ
ሁም ዮአሕ በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ወደ
ንጉሥ ሕዝቅያስ ቀርበው የአሦራውያን ባለሥ
ልጣን የተናገረውን አስረዱት።

### ከባቢሎን የመጡ መልእክተኞች
(ኢሳ. 39፥1-8)

12 በዚያኑ ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የባላዳን
ልጅ መሮዳክ ባላዳን ፥ ንጉሥ ሕዝቅያስ ታሞ
መዳኑን ሰማ ፤ ስለዚህም ከገጸ በረከት ጋር ደብ
ዳቤ ላከለት ፤ 13 ሕዝቅያስም መልእክተኞቹን
በደስታ ተቀበላቸው ፤ በቤተ መንግሥቱም
የዕቃ ግምጃ ቤት ያለውን ሀብት በሙሉ ፥ ብሩ
ንና ወርቁን ፥ ቅመማ ቅመሙንና ሽቶውን ፥
የጦር መሣሪያውንም ሁሉ አሳያቸው ፤ በቤተ
መንግሥቱ ግምጃ ቤትም ሆነ በመንግሥቱ በማ
ንኛውም ስፍራ ካለው ሀብት ሁሉ ሕዝቅያስ
ያላሳያቸው አንድም አልነበረም ። 14 በዚያን
ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ሄዶ
"እነዚህ ሰዎች ከወዴት መጡ? ምንስ ነገ
ሩህ?" ብሎ ጠየቀው ።
ሕዝቅያስም "እነርሱ የመጡት ባቢሎን
ከሚባል ከሩቅ አገር ነው" ሲል መለሰለት ።
15 ኢሳይያስም "በቤተ መንግሥቱ ምን
አዩ" ሲል ጠየቀው ።
ሕዝቅያስም "ሁሉን ነገር አይተዋል ፤ በግ
ምጃ ቤቱ ካለው ሀብት ሁሉ ስእነርሱ ያላሳየኋ
ቸው አንድም ነገር የለም" አለ ።
16 ኢሳይያስም ንጉሡን እንዲህ አለው ፥
"ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥
17 'የቀድሞ አባቶችህ እስከዚህች ቀን ያከማቹት
በቤተ መንግሥትህ ያለው ሀብት ሁሉ ተጠራ
ርጎ ወደ ባቢሎን የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል ፤
ምንም ነገር አይቀርም ፤ 18 ከአንተም ዘርያዎች
አንዳንዶቹ ወደ ባቢሎን ተማርከው በመሄድ
በባቢሎን ቤተ መንግሥት ጃንደርባዎች ሆነው
እንዲያገለግሉ ይደረጋል ።' "
19 ንጉሥ ሕዝቅያስም በተለይ በእርሱ ዘመን
በሰላም የመኖር ዋስትና እንዳለ ስለተረዳ "ከእ
ግዚአብሔር ተልከህ የተናገርከኝ ቃል መልካም
ነው" ሲል መለሰ ።

### የንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ
(2 ዜ.መ. 32፥32-33)

20 ንጉሥ ሕዝቅያስ ያደረገው ሌላው ነገር
ሁሉ የጀግንነት ሥራው ጭምር ፥ እንዲሁም
የውሃ ማጠራቀሚያ ግድብ እንዴት እንደሠራና
ወደ ከተማይቱ ውሃ ለማምጣት ያስቈፈረው
የመሬት ውስጥ በይ አሠራር ሁሉ በይሁዳ ነገ
ሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል ፤
21 ሕዝቅያስም ሞተ ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ
ልጁ ምናሴ ነገሠ ።

## ምዕራፍ 21

### የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ
(2 ዜ.መ. 33፥1-20)

1 ምናሴ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር ፤ መኖሪያውንም በኢ
የሩሳሌም አድርጎ ኀምሳ አምስት ዓመት ገዛ ፤
እናቱም ሔፍጺባ ተብላ የምትጠራ ነበረች ፤
2 የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ አገር በሚገ
ቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ከፊታቸው ነቃቅሎ
ያጠፋቸውን የአሕዛብን አሳፋሪ ልማድ በመከ
ተል ምናሴ የሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርን
አሳዘነ ፤ 3 ምናሴ አባቱ ሕዝቅያስ ደምስሶአቸው
የነበሩትን አረማውያን መስገጃ ስፍራዎች እንደ
ገና እንዲሠሩ አደረገ ፤ የእስራኤል ንጉሥ አክ
አብ ባደረገውም ሀይነት ባዓል ተብሎ ለሚጠ
ራው ባዕድ አምላክ መሠዊያዎችን ፥ አሼራ
ተብላ የምትጠራውን ሴት አምላክ ምስልን
ሠራ ፤ የሰማይ ከዋክብትንም አመለከ ። 4 እግዚ
አብሔር እንዲመለክበት ባዘዘው ስፍራ ማለትም
በቤተ መቅደስ ውስጥ አረማዊ መሠዊያዎችን
አቆመ ። 5 በሁለቱም የቤተ መቅደሱ አደባባ
ዮች የሰማይ ከዋክብት የሚመለኩባቸውን መሠ
ዊያዎች ሠራ ፤ 6 የገዛ ልጁንም መሥዋዕት አድ
ርጎ አቀረበ ፤ እርሱም ራሱ ሟርተኛና አስማ
ተኛ ሆኖ ከጠንቋዮችና ከሙታን ጠሪዎች ምክ
ርን ይጠይቅ ነበር ፤ በዚህም ሁሉ አድራጎቱ
ታላቅ ኃጢአት በመሥራቱ የእግዚአብሔርን
ቍጣ አነሣሣ ። 7 በቤተ መቅደሱም ውስጥ የአ
ሼራን ምስል አኖረ ፤ ይህም ቤተ መቅደስ እንግ
ዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰሎሞን "ይህ
በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ እኔ ለዘላ
ለም እመለክበት ዘንድ ከዐሥራ ሁለቱ የእስራ
ኤል ነገዶች ግዛት ሁሉ የመረጥሁት የተቀደሰ
ስፍራ ነው ። 8 የእስራኤል ሕዝብ ትእዛዛቴን
ሲጠብቁና ለአገልጋዬ ለሙሴ የሰጠሁትንም
ሕግ ቢፈጽሙ ፥ ለቀድሞ አባቶቻቸው ከሰጠኋ
ቸው ከዚህች ምድር ተነቃቅለው እንዲጠፉ
አላደርግም" ሲል ነግሮአቸው የነበረው ነው ፤
9 የይሁዳ ሕዝብ ግን ለእግዚአብሔር ቃል ታዛ
ዥዎች ሆነው አልተገኙም ፤ ይልቁንም ምናሴ
የእስራኤል ሕዝብ ወደፊት እየገፉ ሲመጡ እግ
ዚአብሔር ከፊታቸው ነቃቅሎ ያጠፋላቸው
አረማውያን ይፈጽሙት ከነበረው ይበልጥ ወደ
ከፋ ኃጢአት መራቸው ።
10 እግዚአብሔርም በአገልጋዮቹ በነቢያት
አማካይነት እንዲህ ሲል ተናገረ ፥ 11 "ምናሴ
ይህን ሁሉ አሳፋሪ ነገር አደረገ ፤ ይኸውም
ቀድሞ ከነዓናውያን ይፈጽሙት ከነበረው ሁሉ
የከፋ ነው ፤ በሠራቸውም ጣዖታት የይሁዳን

---

20፥17 ፦ 2ነገ. 24፥13 ፤ 2ዜ.መ. 36፥10 ። 20፥18 ፦ 2ነገ. 24፥14-15 ፤ ዳን. 1፥1-7 ። 21፥2 ፦ ኤር. 15፥4 ።
21፥4 ፦ 2ሳሙ. 7፥13 ። 21፥7-8 ፦ 1ነገ. 9፥3-5 ፤ 2ዜ.መ. 7፥12-18 ።

መድበዋቸው የነበሩትን ፈረሶች ሁሉ አስወ
ገደ ፤ ለዚሁ አምልኮ የሚያገለግሉ የነበሩትን
ሠረገላዎች አቃጠለ ፤ እነዚህ ሁሉ ቀደም ሲል
በቤተ መቅደሱ አደባባይ ታላቁ ባለሥልጣን
ናታን ሜሌክ በሚኖርባቸው ክፍሎች የቅጽር
በር አጠገብ ይገኙ ነበር ፤ [12]ንጉሥ አካዝ ባሠ
ራቸው መኖሪያ ክፍሎች ጣራ ላይ በሚገኘው
ቤተንጉሥ የይሁዳ ነገሥታት አሠርተዋቸው
የነበሩትን መሠዊያዎችና በቤተ መቅደሱ
ሁለት አደባባዮች ንጉሥ ምናሴ አሠርቶአቸው
የነበሩትን መሠዊያዎች ሁሉ ኢዮስያስ ደመሰሳ
ቸው ፤ መሠዊያዎቹንም አንከታክቶ ወደ ቄድ
ሮን ሸለቆ ወስዶ ጣላቸው ። [13]እንዲሁም ከኢየ
ሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ከደብረ ዘይትም[6*]
በስተ ደቡብ ዐስታሮት ተብላ ለምትጠራው
ለሲዶና አምላክ ፥ ከሞሽ ተብሎ ለሚጠራው
ለሞአብ አምላክና ሞሌክ ተብሎ ለሚጠራው
ለዐሞን አምላክ ንጉሥ ስሎሞን አሠርቶአቸው
የነበሩት አስጸያፊዎች ምስሎች ሁሉ የረከሱ
መሆናቸውን አስገነዘበ ። [14]ንጉሥ ኢዮስያስ
የድንጋይ ዐምዶችን ሁሉ ሰባበረ ፤ አሼራ ተብላ
የምትጠራውንም የሴት አምላክ ምስሎች እንከ
ታክቶ ጣለ ፤ እነርሱ ቆመውበት የነበረውንም
ስፍራ የሙታን አጥንት ሞላበት ።
[15]እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ የነባጥ
ልጅ ኢዮርብዓም በቤትኤል አሠርቶት የነበረውን
የማምለኪያ ቦታ ኢዮስያስ አፈራርሶ ጣለ ፤ መሠ
ዊያውን ነቅሎ ፤ የተሠራበትን ድንጋይ ሁሉ ሰባ
ብሮ በማድቀቅ እንደ ትቢያ አደረገው ፤ የአሼራ
ንም ምስል በእሳት አቃጠለ ፤ [16]ከዚህም በኋላ
ኢዮስያስ ዙሪያውን ሲመለከት በኮረብታዎች ላይ
የተሠሩ መቃብሮችን አየ ፤ በእነዚያም መቃብ
ሮች ውስጥ የነበረውን ዐፅም ሁሉ አስወጥቶ በእ
ሳት አቃጠለው ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ መሠዊ
ያው የረከሰ መሆኑን አስገነዘበ ፤ ኢዮስያስ ይህንን
ሁሉ በማድረጉ ከብዙ ጊዜ በፊት በተደረገ የእም
ልኮ በዓል ላይ ንጉሥ ኢዮርብዓም በመሠዊያው
አጠገብ ቆሞ ሳለ ነቢዩ የተናገረው የትንቢት ቃል
ተፈጸመ ፤ ንጉሥ ኢዮስያስ ዙሪያውን ሲመለከት
ይህን ትንቢት ተናግሮ የነበረው ነቢይ የተቀበረበ
ትን መካነ መቃብር አይቶ ፤ [17]“ያ መቃብር
የማን ነው?” ቢል ጠየቀ ።
የቤትኤልም ሕዝብ “ከይሁዳ መጥቶ በዚህ
መሠዊያ ላይ ይህን አንተ ያደረግኸው ነገር
ሁሉ እንዲፈጽምበት ተናግሮ የነበረው የነቢዩ
መቃብር ነው” ሲሉ መለሱለት ።
[18]ኢዮስያስም “እንዳለ ይኑር! ተዉት! የእ
ርሱ ዐፅም ከዚህ መንቀሳቀስ የለበትም!” ሲል
መለሰ ።
ስለዚህም የእርሱም ሆነ የሰማርያው ነቢይ
ሀፅሞች ከዚያ እንዲነሡ አልተደረገም ።
[19]ንጉሥ ኢዮስያስ በማንኛይቱም የእስራ
ኤል ከተማ የእስራኤል ነገሥታት አሠርተዋ
ቸው የነበሩትን የእግዚአብሔርን ቊጣ ለማነሣ
ሣት ምክንያት የሆኑትን የአረማውያን ማምለ
ኪያ ስፍራዎችን ሁሉ አፈራረሰ ፤ በቤትኤል
ያደረገውን ሁሉ በእነዚያ መሠዊያዎች ላይ
ፈጸመ ፤ [20]በእነዚያ መሠዊያዎች ላይ ያገለግሉ
የነበሩትንም አረማውያን ካህናትን ገደለ ፤ በመ
ሠዊያዎቹም ላይ አጥንት አቃጠለባቸው ፡ ይህን
ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ።

### ኢዮስያስ የፋሲካን በዓል አከበረ
(2 ዜ.መ. 35፥1-19)

[21]ንጉሥ ኢዮስያስ በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ
በተጻፈው መሠረት ለአምላካቸው ለእግዚአብ
ሔር የፋሲካን በዓል ያከብሩ ዘንድ ሕዝቡን
አዘዘ ። [22]መሳፍንት የሕዝቡ ገዥዎች ከነበሩ
በት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን በማንኛዎቹም
የእስራኤል ወይም የይሁዳ ነገሥታት አማካይ
ነት ይህን የመሰለ የፋሲካ በዓል ተከብሮ አያው
ቅም ። [23]ይሁን እንጂ ኢዮስያስ በነገሠ በሀሥራ
ስምንተኛው ዓመት የፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም
ተከበረ ።

### ኢዮስያስ ያደረገው ሌላው ለውጥ

[24]ሊቀ ካህናቱ ሒልቂያ በቤተ መቅደስ ባገ
ኘው መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ሕግ ሁሉ
ተፈጻሚነት እንዲኖረው በማሰብ ንጉሥ ኢዮስ
ያስ ከኢየሩሳሌምና ከሌላውም የይሁዳ ከተማ
ሁሉ አስማተኞችንና ጠንቋዮችን ሁሉ የቤተ
ሰብ አማልክትን ፥ ጣዖታትንና ሌሎችንም አረ
ማዊ የአምልኮ መፈጸሚያ ዕቃዎችን ሁሉ አስ
ወገደ ። [25]ለሙሴ ሕግ በመታዘዝ በፍጹም
ልቡ ፥ በፍጹም ነፍሱና በፍጹም ኀይሉ እግዚ
አብሔርን ያገለገለ እንደ ኢዮስያስ ያለ ንጉሥ
ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ ወዲህ ከቶ አልነበ
ረም ።
[26]ነገር ግን ይህም ሁሉ ሆኖ ንጉሥ ምናሴ
ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት በይሁዳ ላይ የነ
ደደው አስፈሪ የእግዚአብሔር ቊጣ አስከ
አሁን ድረስ ገና አልበረደም ነበር ። [27]ስለዚ
ህም እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤ “በእስራኤል
ያደረግሁትን ነገር ሁሉ በይሁዳም ላይ አደርጋ
ለሁ ፤ ይኸውም የይሁዳን ሕዝብ ከፊቴ አስወግ
ዳለሁ ፤ የመረጥኋትን ከተማ ኢየሩሳሌምንና
እመለክበታለሁ ብዬ የነበረውንም ቤተ መቅደስ
እተዋለሁ ።”

---

[6*] 23፥13 ደብረ ዘይት ፦ ወይም “የርኩሰት ተራራ ።”
23፥12 ፦ 2ነገ. 21፥5 ፤ 2ዜ.መ. 33፥5 ። 23፥13 ፦ 1ነገ. 11፥7 ። 23፥15 ፦ 1ነገ. 12፥33 ። 23፥16 ፦ 1ነገ. 13፥2 ።
23፥17 ፦ 1ነገ. 13፥30-32 ።

### የኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ
(2 ዜ.መ. 35፥20-36፥1)

[28] ንጉሥ ኢዮስያስ ያደረገው ሌላው ነገር
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመ
ዝግቦ ይገኛል ፤ [29] በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት
ኒኮ የተባለው የግብጽ ንጉሥ የአሦርን ንጉሠ
ነገሥት ለመርዳት ሠራዊቱን እየመራ ወደ ኤፍ
ራጥስ ወንዝ ተጓዘ ፤ ንጉሥ ኢዮስያስም መጊዶ
ላይ የግብጽን ሠራዊት ለማገድ ጦርነት ገጥሞ
በዚያ ውጊያ ላይ ተገደለ ፤ [30] ባለሟሎቹ የሆኑ
ባለሥልጣኖችም ሬሳውን በሠረገላ ወደ ኢየሩሳ
ሌም አምጥተው እዚያ በነገሥታት መካነ መቃ
ብር ተቀበረ ።
የይሁዳም ሕዝብ የኢዮስያስን ልጅ ኢዮአሐ
ዝን መረጡ ፤ ቀብተውም አነገሡት ።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአሐዝ
(2 ዜ.መ. 36፥2-4)

[31] ኢዮአሐዝ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ ሦስት ዓመት ነበር ፤ መኖሪያውንም በኢየሩ
ሳሌም አድርጎ ሦስት ወር ገዛ ፤ እናቱም ሐሙ
ጣል ተብላ የምትጠራ የሊብና ከተማ ተወላጅ
የሆነው የኤርምያስ ልጅ ነበረች ፤ [32] ኢዮአሐዝ
የቀድሞ አባቶቹን መጥፎ አርአያነት ተከትሎ
ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ ።
[33] እርሱንም ኒኮ ተብሎ የሚጠራው የግብጽ
ንጉሥ በሐማት ምድር በምትገኘው በሪብላ
ማርኮ እስረኛ በማድረግ፥ ይሁዳ ሦስት ሺ
አራት መቶ ኪሎ ብር፥ ሠላሳ አራት ኪሎ
ወርቅ ግብር እንድትከፍል ባደረገው ጊዜ የኢዮ
አሐዝ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ሆነ ። [34] ንጉሥ
ኒኮ የኢዮስያስ ልጅ ኤልያቄም በአባቱ በኢዮስ
ያስ እግር ተተክቶ በይሁዳ እንዲነግሥ አደረገ ፤
ስሙንም በመለወጥ ኢዮአቄም ብሎ ጠራው ፤
ኢዮአሐዝም በንጉሥ ኒኮ ተማርኮ ወደ ግብጽ
ተወሰደ ፤ በዚያም ሞተ ።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም
(2 ዜ.መ. 36፥5-8)

[35] ንጉሥ ኢዮአቄም የግብጽ ንጉሥ የጠየቀ
ውን ግብር ለመክፈል ሕዝቡ በሚያገኙት ገቢ
መጠን ገንዘብ እንዲከፍሉ አደረገ ።
[36] ኢዮአቄም በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ አምስት ዓመት ነበር ፤ መኖርያውንም በኢየ
ሩሳሌም አድርጎ ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ ፤ እና
ቱም ዘቢዳ ተብላ የምትጠራ የሩማ ከተማ ተወ
ላጅ የሆነው የፐዳያ ልጅ ነበረች ። [37] ኢዮአቄም
የቀድሞ አባቶቹን መጥፎ አርአያነት ተከትሎ
ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ ።

## ምዕራፍ 24

[1] ኢዮአቄም በነገሠ ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ
ናቡከደነፆር ይሁዳን ወረረ ፤ ኢዮአቄምም
ሦስት ዓመት ከገበረለት በኋላ እንደገና ዐመፀ ፤
[2] እግዚአብሔር ባገልጋዮቹ በነቢያት አማካይ
ነት ይሁዳን ለማጥፋት የተናገረው ትንቢት
እንዲፈጸም ባቢሎናውያንን፥ ሶርያውያንን፥
ሞአባውያንንና ዐሞናውያንን በኢዮአቄም ላይ
አስነሣበት ። [3] ይህም ሁሉ የሆነው ንጉሥ
ምናሴ ስለ ፈጸመው ኃጢአት ምክንያት የይሁ
ዳን ሕዝብ ከፊቱ ለማስወገድ እግዚአብሔር ባዘ
ዘው መሠረት ነው ፤ [4] በተለይም ምናሴ የንጹ
ሓን ሰዎችን ደም በማፍሰሱና ኢየሩሳሌምንም
በንጹሓን ደም በመሙላቱ ምክንያት ይህ ሁሉ
ሊፈጸም ችሎአል ፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብ
ሔር ለምናሴ ምሕረት ሊያደርግለት አልፈቀ
ደም ።
[5] ኢዮአቄም ያደረገው ሌላው ነገር ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገ
ኛል ፤ [6] ኢዮአቄም ሞተ ፤ በእርሱም እግር ተተ
ክቶ ልጁ ዮአኪን ነገሠ ።
[7] የግብጽ ንጉሥና ሠራዊቱ ከዚያን በኋላ
ከግብጽ ውጭ በመቻ አላደረጉም ፤ ምክንያቱም
የባቢሎን ንጉሥ ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብጽ
ሰሜናዊ ጠረፍ ድረስ የግብጽ ይዞታ የነበረውን
ሁሉ በቊጥጥሩ ሥር አድርጎአል ።

### የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን
(2 ዜ.መ. 36፥9-10)

[8] ዮአኪን በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ዐሥራ ስምንት ዓመት ነበር ፤ መኖሪያውንም
በኢየሩሳሌም አድርጎ ሦስት ወር ገዛ ፤ እናቱም
ነሑሽታ ተብላ የምትጠራ የኢየሩሳሌም ተወ
ላጅ የሆነው የኤልናታን ልጅ ነበረች ። [9] ዮአ
ኪን የአባቱን መጥፎ አርአያነት ተከትሎ ኃጢ
አት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ ።
[10] በናቡከደነፆር የጦር አዛዦች የሚመ
ራው የባቢሎን ሠራዊት በኢየሩሳሌም ላይ
ዘምቶ የከበባትም በዚሁ በዮአኪን ዘመነ መንግ
ሥት ነበር ። [11] በከበባውም ጊዜ ናቡከደነፆር
ራሱ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ፤ [12] ንጉሥ ዮአኪን
ከእናቱ፥ ከልዑላን መሳፍንቱ፥ ከጦር አዛዦ
ቹና በለሟሎቹ ከሆኑት ባለሥጣኖች ጋር ቀርቦ
ለባቢሎናውያን እጁን ሰጠ ፤ ናቡከደነፆር በነገሠ
በስምንተኛው ዓመት ዮአኪንን እስረኛ አድርጎ
በመያዝ፥ [13] በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት
የነበረውን ሀብት ሁሉ ጠራርጎ ወደ ባቢሎን
ወሰደ ። ቀደም ሲል እግዚአብሔር በተናገረውም
ቃል መሠረት ንጉሥ ሰሎሞን ከወርቅ አሠርቶት

23፥34 ፡- ኤር. 22፥11-12 ። 23፥36 ፡- ኤር. 22፥18-19 ፤ 26፥1-6 ፤ 35፥1-19 ። 24፥1 ፡- ኤር. 25፥1-38 ፤ ዳን. 1፥1-2 ።
24፥12 ፡- ኤር. 22፥24-30 ፤ 24፥1-10 ፤ 29፥1-2 ።

ሁሉ ፥ ታናናሽ ወጭቶችንና የእሳት ፍም መያ
ዥያ ዕቃዎችን ጭምር ወሰዱ ። 16 ንጉሥ ሰሎ
ሞን ለቤተ መቅደስ መገልገያ ከነሐስ ያሠራቸ
ውን ንዋያተ ቅድሳት ማለትም ሁለቱን ዐም
ዶች ፥ ባለመንኰራኵር የዕቃ ማስቀመጫዎችና
ታላቁን የውሃ ማጠራቀሚያ በርሜል ፥ በከብደ
ታቸው ምክንያት ሊመዝኑአቸው አልቻሉም ።
17 ሁለቱ ዐምዶች ተመሳሳይ ሲሆኑ እያንዳንዳ
ቸው ስምንት ሜትር ቁመት ነበራቸው ፤ በአና
ታቸውም ላይ አንድ ሜትር ከሠላሳ ሳንቲ
ሜትር ቁመት ያለው ከነሐስ የተሠራ ጒልላት
ነበራቸው ። በእያንዳንዱም ጒልላት ዙሪያ በሮ
ማን ቅርጽ ከነሐስ የተሠራ ጌጠኛ ፈርጥ ተቀር
ጾበት ነበር ።

የይሁዳ ሕዝብ ተማርከው
ወደ ባቢሎን ተወሰዱ
(ኤር. 52፥24-27)

18 ከዚህም ሁሉ ጋር የሠራዊቱ አዛዥ ናቡዛ
ራዳን ሊቀ ካህናቱን ሤራያን በማዕርግ የእርሱ
ምክትል የሆነውን ካህኑን ጸፎንያና ሌሎችንም
ሦስት የቤተ መቅደስ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች
እስር ወሰደ ፤ 19 ከከተማይቱም የወታደሮች
አዛዥ የሆነው አንድ ባለሥልጣን ፥ እስከዚያ
ጊዜ ድረስ በከተማይቱ የነበሩትን አምስቱን የን
ጉሥ አማካሪዎች ፥ የአገሩን ሕዝብ ለወታደር
ነት ይመለምል የነበረውን የጦር አዛዡን ረዳ
ትና ሌሎችንም ስልሳ ታላላቅ ሰዎችን ወሰደ ፤
20 ናቡዛራዳን እነዚህን ሁሉ ይዞ በሐማት ግዛት
በምትገኘው በሪብላ ከተማ ወደነበረው ወደ
ባቢሎን ንጉሥ ወሰዳቸው ፤ 21 ንጉሡም በዚያ
እነርሱን አስደብድቦ በማሠቃየት በሞት ቀጣ
ቸው ።
በዚህም ዐይነት ሁኔታ የይሁዳ ሕዝብ ከአገ
ራቸው ተማርከው ተወሰዱ ።

ገዳልያ የይሁዳ ገዥ ሆነ
(ኤር. 40፥7-9፤ 41፥1-3)

22 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የሳፋን
የልጅ ልጅ የአሒቃም ልጅ ገዳልያን ወደ ባቢ
ሎን ተማርከው ሳይወሰዱ ለቀሩት ሰዎች ሁሉ
ኀላፊ ይሆን ዘንድ የይሁዳ ገዥ አድርጎ
ሾመው ። 23 እጃቸውን ያልሰጡ የይሁዳ የጦር
መኰንኖችና ወታደሮች ይህን በሰሙ ጊዜ ወደ
ምጽጳ ሄደው ከገዳልያ ጋር ተባበሩ ፤ እነዚህም
የጦር መኰንኖች የነታንያ ልጅ እስማኤል ፥
የቃሬሐ ልጅ ዮሐናን ፥ የነጦፋ ከተማ ተወላጅ
የሆነው የታንሑሜት ልጅ ሠራያና የማዕካ ተወ
ላጅ የሆነው የዛንያ ነበሩ ፤ 24 ገዳልያም እነርሱ
ንና ወታደሮቻቸውን እንዲህ አላቸው ፥ “ከባቢ
ሎናውያን ባለሥልጣኖች የተነሣ ምንም ዐይ
ነት ፍርሃት ሊያድርባችሁ እንደማይገባ ቃል
እገባላችኋለሁ ፤ በዚህች ምድር ኑሮአችሁን
መሥርቱ ፤ ለባቢሎን ንጉሥ ገብሩ ፤ ይህን ብታ
ደርጉ ሁሉ ነገር ይቃናላችኋል ።”
25 ነገር ግን በዚያው ዓመት በሰባተኛው
ወር ንጉሣዊ ዝርያ የነበረውና የኤሊሻማዕ
የልጅ ልጅ የሆነው የነታንያ ልጅ እስማኤል
ከዐሥር ሰዎች ጋር ሆኖ ወደ ምጽጳ ሄደ ፤ በዚ
ያም አደጋ ጥሎ ገዳልያን ገደለው ፤ እንዲሁም
ከእርሱ ጋር የተገኙትን እስራኤላውያንንና ባቢ
ሎናውያንን ሁሉ ገደለ ፤ 26 ከዚህም የተነሣ
ባቢሎናውያንን ስለፈሩ እስራኤላውያን ሀብታሞ
ችም ድኾችም ከጦር ሠራዊት መኰንኖች ጋር
በአንድነት ተነሥተው ወደ ግብጽ ሸሹ ።

ዮአኪን ከእስራት ተፈታ
(ኤር. 52፥31-34)

27 ኤዊልመሮዳክ በነገሠበት ዓመት የይሁዳን
ንጉሥ ዮአኪንን ከእስራት በመፍታት ምሕረት
አደረገለት ፤ ይህም የሆነው ዮአኪን በእስረኛ
ነት ተማርኮ በሄደ በሠላሳ ሰባት ዓመቱ በዐ
ሥራ ሁለተኛው ወር በሃያ ሰባተኛው ቀን
ነው ። 28 ኤዊልመሮዳክ ለዮአኪን መልካም
ነገር አደረገለት ፤ እንደ እርሱ ተማርከው በባቢ
ሎን በስደት ከሚኖሩ ነገሥታት ሁሉ የላቀ የክ
ብር ማዕርግ ሰጠው ፤ 29 ስለዚህም ዮአኪን በእ
ስር ቤት የነበረውን ልብስ ለውጦ እስከ ዕድ
ሜው ፍጻሜ ድረስ ከንጉሡ ማእድ እንዲመገብ
ተፈቀደለት ፤ 30 በኖረበት ዘመን ሁሉ በየቀኑ
ለማናቸውም ለሚያስፈልገው ነገር ያውለው
ዘንድ የዘወትር ቀለብ ይሰጠው ነበር ።

25፥26 ፦ ኤር. 43፥5-7 ።